
ካንሰርን - በአሸናፊነት
ገጽ 16

አባት ወይስ ጠላት
ገጽ 11

የመስኖ ልማቱ የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ
ገጽ 17

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 306 ሐምሌ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ
The Children's Heart Fund of Ethiopia

# እስከ ሦስት ዓመታት የሚጠብቁት የልብ ሕክምና ወረፋ

**መስከረም ሰይፉ**

ሕጻን ሐዋርያ ንጉሤ የአራት አመት ታዳጊ ሲሆን ከስድስት ወር እድሜው ጀምሮ የኢትዮጵያ የሕጻናት ልብ ሕክምና ማዕከል ተመላላሽ ታካሚ ሆኖ ቆይቷል፡፡

የሕጻን ሐዋርያ ንጉሤ ታላቅ እህት ገነት ንጉሤ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረገችው ቆይታ እንደተናገረችው ሐዋርያ በተወለደ በስድስት ወሩ ቤተሰቦቹ ልጃቸው የልብ ክፍተት ሕመም እንዳለበት ይነገራቸዋል፡፡ ይህ ቢያስደነግጣቸውም ነገሩን ይበልጥ ከባድ ያደረገባቸው ሕክምናው በሀገር ውስጥ እንደማይሰጥና ልጃቸው ወደ ውጭ ሄዶ መታከም እንዳለበት መስማታቸው ነበር፡፡

ልጃቸውን ወደ ውጭ ወስዶ ለማሳከም አቅማቸው የማይፈቅደው ቤተሰቦችም ይህንን ሕክምና በነፃ ይሰጣል ወደ ተባለው የኢትዮጵያ ልብ

እስከ ሦስት ዓመታት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## በ2016 በጀት ዓመት ከ2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተችሏል

- 175 ሺህ 627 አመራርና ሠራተኞች ሀብት አስመዝግበዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ 2 ቢሊዮን 810 ሚሊዮን 235 ሺህ 799 ብር ከሙስና ምዝበራ ማዳን መቻሉን የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ። በበጀት ዓመቱ 175 ሺህ 627 አመራሮች፣ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብት ማስመዝገባቸውንም አስታውቋል፡፡

በ2016 በጀት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በገበያ ማዕከላቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ግብይት ፈጽመዋል

- የኮልፌ እና የለሚኩራ የገበያ ማዕከላት ለ3ተኛ ወገን ተላልፈዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ወራት በመዲናዋ መግቢያ በሮች በሚገኙ የገበያ ማዕከላት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ግብይት መፈጸማቸውን የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው በከተማ አስተዳደሩ የተገነቡትን የኮልፌና የለሚኩራ የገበያ ማዕከላትን ለሦስተኛ ወገን አስተላልፏል።

በገበያ ማዕከላቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን መዛባት ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች

**አዲሱ ገረመው**


ኢትዮጵያ ከውጭ የምትቀበላቸው ምርቶች ከምትልካቸው ምርቶች የላቀ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ይህ የሀገሪቷ ቀጣይነት ያለው የንግድ ሚዛን አለመመጣጠን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶችን ሊፈጥር እንደሚችልም ይነሳል፡፡

በኢትዮጵያ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ጀማል መሐመድ (ዶ/ር) ስለ ሁኔታው እንደገለጹት፤ አወንታዊ ሚዛን (የንግድ ትርፍ) በመባል የሚታወቀው ሀገር ከምታስገባው



የኢትዮጵያ የንግድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር)

## የመጠባበቂያ ክምችት አቅምን ወደ 47 በመቶ የሚያሳድጉ ዘመናዊ የክምችት መጋዘኖች እየተገነቡ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሀገር አቀፍ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ክምችት አቅምን ከ23 በመቶ ወደ 47 በመቶ የሚያሳድጉ ዘመናዊ የክምችት መጋዘኖች እየተገነቡ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ የመፈጸም አቅምን በማሳደግ ሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን በሚል ስኬታማ የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

የተረጅነት አስተሳሰብ፤ ስንፍና እንዲስፋፋ በማድረግ ፈጠራን የሚያቀጭጭ እና ታታሪነትን የሚጎዳ መሆኑን የገለጹት አምባሳደር ሽፈራው፤ ይህም ከኢትዮጵያዊነት ባሕልና ማንነት ያፈነገጠ ድርጊት መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ መነሻነት በአዲስ መልክ ሥራ የዋለው የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ የዜጎችን የምርታማነት አስተሳሰብ ልዕልና በማጎናጸፍ የተረጂነት ባሕልን ለመሻገር መሠረት እንደሚሆን አንስተዋል።

በመጠባበቂያ ፈንድ የገቢ አቅምን በማሳደግ መንግሥት ከሚመድበው ሃብት ባሻገር ኅብረተሰቡ ሚናውን የሚወጣበት የአሠራር ሥርዓት መሆኑን ገልጸዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጋዘን ክምችት አቅም 23 በመቶ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በአማራ እና በሶማሌ ክልሎች ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ የክምችት መጋዘኖች እየተገነቡ ነው ብለዋል።

በሆሳዕና፣ ፍኖተ-ሠላምና ቀብሪ-ደሃር ከተሞች በግንባታ ሂደት የሚገኙት ዘመናዊ የክምችት መጋዘኖች ሲጠናቀቁም የስትራቴጂክ መጠባበቂያን የመያዝ አቅም ወደ 47 በመቶ ማድረስ እንደሚያስችሉ ገልጸዋል።

በሥራ ላይ የዋለው ፖሊሲም የሀገርን ሉዓላዊ ነፃነት እና የዜጎችን ክብር በማስጠበቅ አደጋን በራስ አቅም ምላሽ በመስጠት የክምችትና የመጠባበቂያ ፈንድ አቅምን ማጎልበት የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

በመጠባበቂያ ፈንድ በቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እና ከአደጋ በኋላ ለሚሠሩ ሥራዎች በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ለችግር ምላሽ የሚሰጥበት ሃብት የመፍጠሪያ መንገድ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለይም የማኅበረሰብን የመረዳዳት ባሕል በማጎልበት በቅድመ አደጋ፣ በአደጋ እና ከአደጋ በኋላ ለሚሠሩ ተግባራት ከ500 ሺህ በላይ ሜትሪክ ቶን የስትራቴጂክ መጠባበቂያ አቅም ለመፍጠር እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዚህም በፌደራል ደረጃ 150ሺህ ሜትሪክ ቶን የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ሃብት በማከማቸት ቀሪውን ክልሎች እንደየ አካባቢያቸው ጸጋ ማልማት የሚችሉበትን ሥርዓት እየተፈጠረ መሆኑን ተናግረዋል።

የአደጋ ስጋት ተጋላጭነትን በመቋቋም በትብብርና ትስስር ላይ የተመሠረተ የአይበገሬነት ግንባታም ሌላኛው በተቋሙ አደጋን በራስ አቅም ምላሽ የመስጠት ወሳኝ የትኩረት መስክ መሆኑን ገልጸዋል።

# ጥናትና ምርምሮቹ ለፖሊሲ አውጭዎች እና ለአስፈጻሚዎች በግብዓትነት እያገለገሉ ናቸው

**ዘላለም ግዛው**



ወንድወሰን ታምራት (ዶ/ር)

አዲስ አበባ:- በተመራማሪዎች ተጠንተው የሚቀርቡ ግኝቶች ለፖሊሲ አውጭዎች እና አስፈጻሚዎች በግብዓትነት እንዲሁም፣ ምርምር እና ጥናት ለሚያካሂዱ አካላት በማጣቀሻነት እያገለገለ የሚገኝ መሆኑን የቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ መሥራችና ፕሬዚዳንት ወንድወሰን ታምራት (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

በቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት በየዓመቱ የሚካሄደው እና ለ16ኛ ጊዜ የተዘጋጀው ኮንፍረንስ ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል፡፡

ወንድወሰን (ዶ/ር) በወቅቱ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወኑ ጥናትና ምርምሮች የሚያበረታቱ ጥረቶች አሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲውም የምርምርና ጥናት ሥራን ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት ይገኛል፡፡

የቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ ከሚያዘጋጀው አምስት ዓመታዊ የምርምር ዝግጅቶች መካከል፣ መልቲ-ዲሲፕሊን ሴሚናር (ኤምዲኤስ) ፈጠራን በማጎልበት እና በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በአካዳሚክ ምሑራን፣ በተመራማሪዎች እና በባለሙያዎች መካከል የእውቀት ሽግግር ባሕልን በማስተዋወቅ ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

ተመራማሪዎች በዘርፉ በስፋት እንዲሳተፉ፣ ግኝቶችን ለሕዝቡና ለሌሎች በስፋት እንዲታወቁ ማድረግ ዋና ድርሻችን አድርገን፣ ለፖሊሲ አውጭዎች እና አስፈጻሚዎች ሰነደን የማድረሱን ሥራ እየሠራን እንገኛለን፡፡ ጥረቱ ሰፊና ጊዜ የሚወስድ፣ ዓለም አቀፍ ሂደት ነው፡፡ እንደተቋም ጥረታችንን ሳናቋርጥ አስተዋፅዖ ማድረጋችንን እንቀጥላለን ብለዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ተቋማዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ በሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ጽሑፎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት መካከልም የከፍተኛ ትምህርት ጉዳይ፣ የግጭት አፈታት፣ የምግብ ዋስትናን የሚመለከቱ የጥናት ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

በምርምር ሥራ የተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚሳተፉበት እና በጋራ የሚያገናኝ መድረክ ነው፡፡ ጥናት አቅራቢዎቹ ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለያየ ዘርፍ ላይ ያሉ አጥኚዎች የሚሳተፉበት ነው፡፡

በመድረኩ የሚቀርቡ የጥናት ጽሑፎች ለፖሊሲ አውጭዎች ተጠርዘው የሚላኩበት፣ በቀጣይ በጉዳዩ ጥናትና ምርምር ለሚያከናውኑ አካላት በላይብረሪ ተቀምጦ እንደግብዓትና ማጣቀሻ የሚያገለግሉ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡ በየጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ወጣት ተመራማሪዎች መሳተፋቸውን አመልክተዋል፡፡

ከሀገር ውስጥ እና በውጭ ከሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑንና በተለይም በምርምር ሥራዎች የጋራ ተሳትፎ መኖሩንም ጠቁመዋል፡፡

ማኅበራዊ ተሳትፎ በማድረግ ሰፊ ሥራዎች እንደሚሠሩ በመጠቆምም፤ ተማሪዎችና መምህራን ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንደሚደረግ፣ ራሱን የቻለ ክፍል ተቋቁሞ በርካታ ሥራዎች እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያዋ የሠራችውን ጥናት ያቀረበችውና በካቶሊክ ርዳታ ድርጅት እየሠራች የምትገኘው ሀና እንዳሻው፤ የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ እንደሚገኝ ትኩረቱን በምግብ ዋስትና ላይ ባተኮረው ጥናቷ ባቀረበችው ጽሑፍ አመልክታለች፡፡

ድርቅ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እየተፈጠረ መሆኑን ተከትሎ የምግብ ዋስትና ጉዳይ በተለይም ደግሞ በገጠር አካባቢ ዋና አጀንዳ ሆኗል ብላለች፡፡

በምሥራቅ ሐረርጌ የሚገኙ ዘጠኝ ወረዳዎች ላይ በተደረገው ጥናት ከተገኙ ዘጠኝ ጉዳዮች መካከል የብድር አቅርቦትና የንግድ ሥራ ተፅዕኖ እንዳላቸው ጥናቱ ማመልከቱን ተናግረዋል፡፡

እንደጥናት አቅራቢዋ ገለጻ፤ ለወሰዱት ብድር የማዋል ችግር እንደሚስተዋል፣ የአስተሳሰብ ለውጥ አስፈላጊ መሆኑንና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ እና ቤተሰብ ምጣኔ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

በመንግሥት የሚከናወነውን የሴፍቲኔት መርሐ ግብር ማጠናከር፣ ሥራ እየሠሩ ገንዘብ የሚያገኙበት ተግባር በትኩረት መሠራት እንዳለበትም አመልክተዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ለ16ኛ ጊዜ የተከናወነው ሴሚናር ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን የማኅበረሰብ አገልግሎትንና የምርምር ሥራን ዋናው ተግባር አድርጎ እየተገበረ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየዓመቱ አራት ኮንፍረንሶችን ያካሂዳል፣ ሦስት ጆርናሎችን የሚያወጣ ሲሆን፤ አንዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ ነው፡፡

# በክልሉ የወባ በሽታ ስርጭትን ለመከላከል

## ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሙሉነሽ ደሴ (ዶ/ር)



አቶ በላይ በዛብህ

ባሕር ዳር፡- በአማራ ክልል የተከሰተውን የወባ ወረርሽኝ ለመከላከል ግብረኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በአማራ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪ እና ክልላዊ የወባ በሽታ መከላከል ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ሙሉነሽ ደሴ (ዶ/ር) በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ባለፉት አስር ዓመታት የወባ በሽታን ለመከላከል ጥረት ቢደረግም በሽታው አሁንም ድረስ የማኅበረሰብ የጤና ችግር እየሆነ መጥቷል፡፡

በተለይም ደግሞ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በሽታው በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ይገኛል ያሉት ሰብሳቢዋ፤ በአንድ ሳምንት ብቻ ባልተለመደ ሁኔታ ከ53 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች የወባ በሽታ ተጠቂ መሆናቸው የሥርጭቱን ስፋት እንደሚያሳይም ተናግረዋል። በክልሉ ምዕራባዊ ክፍል በሚገኙ 34 ወረዳዎች በሽታው በከፍተኛ ሁኔታ ተሰራጭቶ ይገኛልም ብለዋል።

ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የፀረ ወባ ኬሚካል ርጭት መቀነስ፣ የአጎበር በወቅቱ አለመቅረብ እና በአግባቡ አለመጠቀም፣ ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ ቦታዎችን ለይቶ የቁጥጥር ሥራ አለመሥራት፣ በበጋ ወቅት ለመስኖ ልማት ያገለገሉ ግድቦችን በአግባቡ አለማፋሰስ እንዲሁም የተፈጠረው ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ለሥርጭቱ መስፋፋት በምክንያትነት ተጠቅሰዋል።

አሁን ላይ በአማራ ክልል ደረጃ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሁሉን አቀፍ የወባ መከላከል እና መቆጣጠር ሥራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉም ሙሉነሽ ደሴ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

የአማራ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር በላይ በዛብህ እንዳሉት ከፍተኛ ሥርጭት ባለባቸው 21 ወረዳዎች የቤት ለቤት የኬሚካል ርጭት እየተካሄደ ይገኛል።

በግዥ ሂደት ላይ የሚገኘው የኬሚካል አቅርቦት ለክልሉ እንደደረሰ ርጭት የሚካሄድ ይሆናል ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለ10 ወረዳዎች የአልጋ አጎበር ለማሰራጨት እየተሠራ መሆኑንም አንስተዋል።

በክልሉ የቀረበውን መድኃኒት ወደ ጤና ተቋማት የማዳረስ ችግር መኖሩን ያነሱት ዳይሬክተሩ የጤና ግብዓት የጫኑ ተሽከርካሪዎች ግብዓትን ወደ ጤና ተቋማት እንዲያደርሱ ሁሉም ኃላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

ወረዳዎች በጀት በመመደብ ጭምር የተከሰተውን የወባ በሽታ መከላከል ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሠሩ ጠይቀዋል።

የጤና ባለሙያዎች ማኅበረሰቡን በማስተባበር ለወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑ ቦታዎችን እንዳይመቹ በማድረግ እና የቀረበውን መድኃኒት በፍትሐዊነት ለማኅበረሰቡ በማድረስ የወባ በሽታን የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራ እንዲሠሩ አሳስበዋል ሲል የዘገበው አሚኮ ነው።

ዜና

# ክልሉ የልማት ሥራዎችን ያስጣልቃገብነት በትብብር ማዕቀፍ እያከናወነ ነው

**ስምስም መንግሥቱ**


አዲስ አበባ፡- የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፌዴራል መንግሥት ጋር በተናበበ መልክ የልማት፣ የማኅበራዊና ሌሎችንም ተግባራት ያለጣልቃገብነት በትብብር ማዕቀፍ እንዲያከናውን የተፈጠረለት አቅም አንዱ የሀገራዊ ለውጥ ትሩፋት መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አስታወቁ፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ (ዶ/ር) ክልሉ በሕዝበ ውሳኔ እራስን በራስ የማስተዳደር መብቱን ካረጋገጠ ካለፉት ሁለት ዓመት ተኩል ወዲህ በልማትና በመልካም አስተዳደር በክልሉ የተከናወኑትን ተግባራት አስመልክተው ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ክልሉ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በተናበበ መልክ የልማት፣ የማኅበራዊና ሌሎችንም ተግባራት ያለጣልቃገብነት በትብብር ማዕቀፍ የማከናወን አቅም ተፈጥሮለታል፡፡ ይህ አቅም የተፈጠረው ከሀገራዊ ለውጥ በኋላ በመሆኑ አንዱ የሀገራዊ ለውጡ ትሩፋት ነው፡፡

ከሀገራዊ ለውጥ በኋላ በራስ አቅም ብዙ ነገር መፈፀም እየተቻለ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ «ወደ ሁለተናዊ ብልፅግና መሸጋገር አለብን፣ ለዚያም የሚሆን መሠረት ለመጣል እንደክልልም እንደሀገርም እየሠራን እንገኛለን» ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የውስጥ ችግሮችን በውይይት በመፍታት ሙሉ አቅም ለልማት ማዋል ከተቻለ ከበለፀጉ ሀገራት መካከል መሆን እንደሚቻልም እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ማብራሪያ፤ ክልሉ ራሱን ችሎ ከተደራጀ በኋላ፣ የሕዝቡ አንገብጋቢ የሆኑ ጥያቄዎችን ወደ ሕዝቡ ወርዶ የመፍታትና ምላሽ የመስጠት ጉዳይ አንዱ ነበር፤ ክልሉ ከመቋቋሙ በፊት ሸካ ዞን፣ ምዕራብ ኦሞ ዞን አካባቢ የሰዎች ሠላማዊ እንቅስቃሴ የተገደበበት፣ ጥቂት ቡድኖች ወጥተው አካባቢውን ለመቆጣጠር ሙከራ ያደረጉበት፣ በአንዳንድ ቦታዎችም የሰው ሕይወት የጠፋበት፣ ንብረትም የወደመበት፣ በአጠቃላይ የማኅበረሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ


ፎቶ - ዳኜ አበራ
ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ (ዶ/ር)

የተገታበት ጊዜ ነበር፡፡

የፀጥታ መዋቅሩን እንደገና በማደራጀት፣ በተለያየ መንገድ የማብቃት ሥራ በመሥራት ወደ ማኅበረሰቡም በመቅረብ ተከታታይ ተግባራትን በማከናወን የተረጋጋ አካባቢ መፍጠር መቻሉንና ይሄ ትልቁ ውጤትና ትሩፋት ተደርጎ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡

በአካባቢው ሀብት የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆንም ዋናው የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በግብርና፣ በኢንዱስትሪው፣ በአገልግሎት ዘርፍ፣ በቱሪዝም፣ በማዕድንና በሌሎችም የመለየት ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል፡፡ የክልሉን አጠቃላይ የልማትና የኢኮኖሚ የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱንም አመልክተዋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ክልሉ በሚታወቅበት በቡና፣ በቅመማቅመም፣ በሰሊጥ፣ ከምግብ ፍጆታ ባለፈ ለገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ላይ መሥራት እንደሚገባና ለዚህም ዘመናዊ የግብርና አስተራረስና አመራረት ዘዴ፣ ሜካናይዜሽንን ለማለማመድ፣ በተደረገው ሙከራ በግብርናው ከ182 በላይ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡


በዚህ ረገድም የቡና ምርታማነትን የመጨመር አቅም መፈጠሩን፤ ቡና ላይ ምርታማነትን የሚጨምሩ አሠራሮችን በመከተል ከአንድ ሄክታር ከስድስትና ሰባት ኩንታል ያልበለጠ ምርት ይገኝ የነበረውን ወደ አስር ኩንታልና ከዚያም በላይ ከፍ ማድረግ መቻሉንና በመስኖ የማልማቱ ልምድ መዳበሩንም አስረድተዋል፡፡

የአካባቢውን መልማትና ፀጋዎቹን መሠረት ያደረገ ልየታ በማድረግ በአራት ክላስተር በመከፋፈል ወደ ሥራ መገባቱንና በዚህ መልኩ መንቀሳቀሱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ክልሉ የኔ ነው የሚል ስሜት መፍጠሩንም ጠቁመዋል፡፡ በዚህም ብዝኃነት አስተሳሰብ ወደመሬት ወርዷል የሚል እምነት መኖሩንም ገልጸዋል፡፡

በሌማት ትሩፋት በክልሉ የተሠሩት ፕሮጀክቶች ቱሪዝሙን ከማነቃቃት ባለፈ ትርጉም ያለው ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ተረስተናል ይል የነበረ ማኅበረሰብ አለመረሳቱን ያረጋገጠበት፣ ሕዝብና መንግሥትን ያቀራረበ ፕሮጀክት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ክልሉ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ ለሆነው ለወጣቶች ሥራ ዕድል መፍጠር ተግባር አጋዥ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡ በዚህም መሠረት በተለያየ ዘርፍ ለ53ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩንና ከነዚህ ውስጥም 28ሺ የሚሆኑት በግብርና ዘርፍ በእርሻ፣ በእንስሳት እርባታ፣ በንብ ማነብና መሰል ጉዳዮች ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

በጤናው ዘርፍም የተለያዩ ሥራዎች ቢሠሩም የወባ ወረርሽኝ አሳሳቢ መሆኑን ያነሱት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ አንድ ሰው በተደጋጋሚ በወባ እንደሚያዝ፣ የታማሚውም ቁጥር መጨመሩን፣ የሞት ምጣኔውም ከፍ ማለቱን ጠቁመዋል፡፡ ከጤና ሚኒስቴርና የልማት አጋሮች ጋር በጋራ የንቅናቄ ሥራ ቢሠራም ጥረቱ መጠናከር አለበት ብለዋል፡፡


ዶክተር አባስ ሀሰን

# በሀገሪቱ የጤና ተደራሽነትን በማስፋት ጥራትን ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዳማ፡- በሀገሪቱ የጤና ተደራሽነትን በማስፋት ጥራትን ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ጠንካራና ጥራቱ የተረጋገጠ የጤና አገልግሎት ሥርዓት ለመገንባት ውጤታማ የጤና አመራር ሚና ወሳኝ መሆኑም ተገልጿል።

3ኛው የኦሮሚያ ክልል አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራት መድረክ “ሁለንተናዊ የሥርዓት እሳቤ ለተሻለ ጤና” በሚል መሪ ሀሳብ ትላንት በአዳማ ከተማ መካሄድ ጀምሯል።

በጤና ሚኒስቴር የኢኖቬሽንና የጤና ሥርዓት ዳይሬክተር ዶክተር አባስ ሀሰን እንደገለጹት፤ ጠንካራና የማይበገር የጤና ሥርዓት ለመገንባት ውጤታማ የጤና አመራር ወሳኝ ነው።

እንደ ዶክተር አባስ ገለጻ፤ በሀገሪቱ የጤና ተደራሽነትን በማስፋት ጥራትን ለማረጋገጥ እየተሠራ ሲሆን ጠንካራና የማይበገር የጤና ሥርዓት ለመገንባት ውጤታማ የጤና አመራር ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በመድረኩ በርካታ ነገሮች እንደሚዳሰሱ የገለጹት ዶክተር አባስ፤ የጤና ኢኖቬሽን፤ ውጤታማ አመራር፤ የመጀመሪያ ጤና አሐድ ሥርዓት ማነቆዎች እና የአክሪድቴሽን ፍኖተ ካርታ እንዲሁም ኢንፌክሽንን በመከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ ምክክር ይደረጋል ብለዋል።

ጠንካራ የጤና ሥርዓት በመገንባት የአገልግሎት ጥራትን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ተደራሽነትንና ጥራትን ለማረጋገጥ የዘርፉን መሠረተ ልማት ማሟላት ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ደረጄ አብደና በበኩላቸው፤ የክልሉ መንግሥት የጤና አገልግሎት ተደራሽነትንና ጥራትን ለማረጋገጥ ኢኒሼቲቭ ቀርጾ እየሠራ ነው ብለዋል።

የጤና አገልግሎት ሥርዓት በዜጎች ፍላጎት ልክ መድረስ አለበት ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የጤና አገልግሎት ሥርዓትን በዜጎች ፍላጎት ልክ ለማድረስ የዘርፉን ማነቆዎች በመቅረፍ የዜጎችን የጤና ፍላጎት ማሻሻል ይገባል ብለዋል።

የዘርፉን የአገልግሎት ጥራት ለማረጋገጥ አዳዲስ ኢኒሼቲቮችንና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ጠቅሰዋል ምክትል ቢሮ ኃላፊው፡፡

የጤናውን ዘርፍ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ዘርፉ በኢኖቬሽን፣ በቴክኖሎጂና በጠንካራ ፖሊሲ ሊደገፍ እንደሚገባውም አክለው ጠቁመዋል።

ጤናማነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የጤና አገልግሎትን ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የአገልግሎቱን ጥራት ለማሻሻል ውጤታማ የጤና አመራር ሊኖር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በትናንትናው ዕለት የተጀመረው መድረኩ በዛሬው ዕለትም ከፍተኛ የፌዴራልና የክልሉ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የሚካሄድ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

# በመዲናዋ ሀገርን የሚረከብና የሚያጸና ትውልድ ለመፍጠር የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ሀገርን የሚረከብና የሚያጸና ትውልድ ለመፍጠር የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ቢሮው በየካ ክፍለ ከተማ በሚገኘው አቢሲኒያ የደን ክልል የ2016 ዓ.ም የትምህርት ማኅበረሰቡ የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሐ-ግብር በትላንትናው እለት አካሄዷል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የቢሮው ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር)፤ ሀገርን የሚረከብና የሚያጸና ትውልድ ለመፍጠር የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

የትምህርት ማኅበረሰቡ በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ከሚያከናውናቸው ተግባራት ባሻገር በሀገር አቀፍም ደረጃ በሚካሄደው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ላይ እንደሆነም አክለዋል፡፡

እንደ ዘላለም (ዶ/ር) ገለጻ፤ በማስጀመሪያ መርሐ ግብር 30ሺህ የትምህርት ማኅበረሰቡን በማሳተፍ 100ሺህ ችግኞችን ለመትከል እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን፤ ትውልድ የሚገኘው ትምህርት ቤት በመሆኑ የትምህርት ማኅበረሰቡ የሚሠራው ሥራ ትርጉሙ ለየት ያለ ነው ብለዋል፡፡

በየወቅቱ ችግኞችን መትከል ብቻ ሳይሆን መንከባከብ አስፈላጊ በመሆኑ በየስፍራው በመገኘት በዓመት ለሁለት ጊዜ እንክብካቤ እንደሚደረግ የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ ይህም የትምህርት ማኅበረሰቡን በማስተባበር እየተከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

እንዲሁም ቀደም ሲል በሁሉም ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ችግኝ ሲተከል መቆየቱን በማስታወስ፤



የተተከሉ ችግኞችን ተማሪዎች በክበባት በመደራጀት በየእለቱ እንክብካቤ እንዲያደርጉ እየተደረገ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የተጠናከረ ተሳትፎ ለማድረግ በቂ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን ገልጸው፤ የተጀመረው የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር የትምህርት ማኅበረሰቡን በማስተባበር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

በሐምሌ 14 የ12ኛ ክፍል ማትሪክ ተፈታኝ ተማሪዎች ፈተናቸውን እንደጨረሱ ከተማሪዎቹ ጋር በጋራ በመሆን ችግኝ ለመትከል ቦታ መዘጋጀቱን የቢሮ ኃላፊው አመላክተው፤ ይህም ለሚቀጥለው ትውልድ ምቹ ሀገር ለማስተላለፍ የሚደረግ ጥረት አካል መሆኑን የቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል።

ቢሮው ከአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ጎን ለጎን በክረምት የማጠናከሪያ ትምህርትም በርካታ በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ለ2017 የትምህርት ዘመን ቅደመ ዝግጅት ሥራ ከወዲሁ እየተከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ላይ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የመምህራን ማኅበርና የተማሪ ወላጅ ኅብረት አመራሮችን ጨምሮ ወላጆችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# በ2016 በጀት ዓመት ከ2 ነጥብ 8 ቢሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኮሚሽኑ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ በ2016 በጀት ዓመት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 1 ሺህ 87 አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

በዚህም 2 ቢሊዮን 810 ሚሊዮን 235 ሺህ 799 ብር፣ 8 ሺህ490 ዶላር እንዲሁም 46 ሚሊዮን 467 ሺህ 393 ካሬ ሜትር የከተማና የገጠር ቦታን ከሙስና ምዝበራ ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡

ምዝበራው ከግዥ፣ መሬት አሰጣጥ፣ ንብረት ማስወገድ፣ ገቢ አሰባሰብ፣ ዕርዳታ አሰጣጥ፣ ንብረት ማስወገድ እና ከማዳበሪያ ስርጭት ጋር በተገናኘ ሊፈጸም የነበረ መሆኑንም ጠቁመው፤ በዚህ ሕገወጥ ሥራ የተሳተፉ አካላትም አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደባቸው፣ በዲሲፕሊን የተቀጡና ጉዳዩ ወደ ፍትሕ አካላት ተልኮ በፍርድ ሂደት ላይ የሚገኙ ጉዳዮች መኖራቸውንም ጠቅሰዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሙስናን ከመከላከል አንጻር በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን የገለጹት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ሙስናን መከላከልና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን የማመንጨት፣ በመተንተንና በማጠናቀር ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል የማድረግ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ ካለው ሀገራዊ ችግር አንጻር ግን ሙስናን መከላከል አሁንም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት የሚጠይቅ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሙስና መረጃ አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን በላይነህ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ 6 ሺህ565 ጥቆማዎችን ከሕዝብ ተቀብሏል። ከዚህ ውስጥ 2 ሺህ 123 ጥቆማዎች ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ፍትሕ አካላት ተልከዋል።

ከጥቆማዎቹ 3ሺህ208 በኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር የማይካተቱ በመሆናቸው ለጠቋሚዎቹ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ 215 ጥቆማዎች ላይ ደግሞ ተጨማሪ መረጃ እየሰበሰበ መሆኑን ገልጸዋል።

በሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ሥራ 175 ሺ 627 አመራሮች፣ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብት ማስመዝገባቸውን የጠቀሱት አቶ መስፍን፤ ምዝገባው እድሳትና አዲስ ምዝገባን የሚያካትት ነውም ብለዋል።

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታና ፀረሙስና ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሀረጎት አብርሃ፤ የፀረ ሙስና ትግል ያለኅብረተሰቡ ተሳትፎ ሊሳካ አይችልም፡፡ በዚህም ከክልል እስከ ወረዳ ለሚገኙ 470ሺህ አመራሮች፣ ሠራተኞችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ሥልጠና ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

ኅብረተሰቡ በሙስና ትግል ጉልህ ሚና እንዲኖረው ለማድረግም ለ12 ሚሊዮን 425 ሺህ 909 ዜጎች የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎችና መልእክቶች ተደራሽ መደረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት 470 ሺ ለሚሆኑ የተለያዩ የኅብረተሰብና ባለድርሻ አካላት ሙስናን መከላከል የሚያስችል ሥልጠና መሰጠቱን የገለፁት ደግሞ በኮሚሽኑ የሥነ ምግባር ግንባታና ፀረ ሙስና ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈፃሚ ሀረጎት አብርሃ ናቸው።

በእንዲህ አይነት ጥረቶችም የፀረ ሙስና ትግሉ ተቋማዊ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

# የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን መዛባት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በላይ ወደ ውጭ ስትልክ ሲሆን፤ በተቃራኒው የንግድ ጉድለት በመባል የሚታወቀው አሉታዊ ሚዛን፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ሲበልጡ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን ነባራዊ ሁኔታ አሉታዊ ሚዛን ላይ ይገኛል፡፡

እንደ ጀማል (ዶ/ር) ማብራሪያ፤ ባለፈው ዓመት የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ዋጋ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በታች ሲሆን፣ ከውጭ የሚገቡት ምርቶች ግን ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ በመሆናቸው የንግድ ጉድለቱ ወደ 7 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። ይህ እያደገ የመጣው የንግድ ሚዛን መዛባት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ሲሆን የውጭ እርዳታና ብድር ጥገኝነት እንዲጨምርም ምክንያት ሆኗል።

በታሪክ እንደ ቻይና ያሉ በኢኮኖሚ ያደጉ ሀገራት ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡት ምርት በላይ ወደ ውጭ በመላክ አወንታዊ የንግድ ሚዛን እንዳላቸው ተመራማሪው ይገልጻሉ። በአንፃሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሐራ በታች ያሉ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት አሉታዊ የንግድ ሚዛን ውስጥ መሆናቸውን ያነሳሉ። ይህ የወጭ ገቢ ንግድ አለመመጣጠን እነዚህ ሀገራት ጉድለቶቻቸውን ለመሸፈን እንዲረዳቸው ከውጭ ብድር ለመቀበል መገደዳቸውንም ይጠቅሳሉ።

ተመራማሪው፣ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀገሪቱ በሦስት ዓመታት ውስጥ 10 ቢሊዮን ዶላር ዕዳ መክፈሏን የተናገሩትን ንግግር በማስታወስ፣ ይህ ማለት ሀብት ከሀገር ውስጥ ልማት ባሻገር ለብድር አገልግሎት ምን ያህል ወጪ እየወጣ እንዳለ ማሳያ ነው ይላሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የንግድ ጉድለት የፋይናንስ ጫናን እንደሚያባብስ፣ የምንዛሪ እጥረትና የዋጋ ግሽበትን እንደሚነካ በመግለጽ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የኢትዮጵያ አሉታዊ የንግድ ሚዛን የሀገር ውስጥ ምንዛሪ ዋጋን መቀነሱን፤ የገቢ ዋጋ እንዲጨምር እና የዋጋ ንረት እንዲባባስ አንዱ ምክንያት መሆኑን አፅንዖት ሰጥተዋል።

የውጭ ገበያ ላይ ጥገኛ መሆን ኢትዮጵያን ለዓለም አቀፍ የዋጋ ውጣ ውረድ ያጋልጣል ያሉት ተመራማሪው፣ ይህም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ሁኔታውን እንደሚያባብሰውና ለተጨማሪ አሉታዊ የኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነት እንደሚዳርግ ተናግረዋል። ለአብነትም ዓለም አቀፋዊው የነዳጅ ዋጋ ለውጥ በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል በመጥቀስ ይህ የሚሆነውም ሀገሪቱ ነዳጅን ከውጭ በማስገባቷ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የሀገሪቱ የማምረት አቅም ወሳኝ ጉዳይ ነው በማለት፣ የኢትዮጵያን ምርት ከሕዝብ ዕድገትና ፍላጎት ጋር ማጣጣም አዳጋች እየሆነ መምጣቱን ይጠቅሳሉ። መንግሥታዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ቢደረጉም እነዚህ ጥረቶች የንግድ እጥረቱን በበቂ ሁኔታ ሊፈቱ አልቻሉም ነው የሚሉት። እንደ ግጭቶች እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ያሉ ጉዳዮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይ የራሳቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ማስከተላቸውን፣ ይህም የኢኮኖሚ ምሕዳሩን የበለጠ ሊያዳክመው እንደሚችል አብራርተዋል።

መንግሥት ለአገልግሎት ዘርፍ በተለይም ለቱሪዝም የሰጠውን ትኩረት የፀጥታ ስጋት ለሆኑ ጉዳዮችም ትኩረት በመስጠት ኢንቨስትመንት ተስፋፍቶ ምርት በብዛት ወደ ውጭ እንዲላክ ማድረግ እንዳለበትም ነው የገለጹት።

አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ የኢንቨስትመንት ማሻሻያ ካልተደረገ የኢትዮጵያ የንግድ ጉድለት እያደገ እንደሚሄድና ይህም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ሊያስከትል እንደሚችል ተመራማሪው ይናገራሉ።

ተመራማሪው እንደሚሉት፣ በእርዳታ እና በዕዳ ላይ ጥገኝነት መጨመር የድህነትን ደረጃ ያባብሳል። እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ እና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኛነትን ለመቀነስ የታለሙ ጠንካራ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ይጠይቃል። የንግድ ሚዛኑን ለማሻሻል እና የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማጎልበት በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና እና በማዕድን ዘርፎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ወሳኝ ነው።

በተመሳሳይ የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሑሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)፣ በሀገሪቱ ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ይልቅ የሚገባው ከፍተኛ በመሆኑ ለውጭ ምንዛሪ ክምችት መቀነስ አንዱ ምክንያት ሆኗል ሲሉ የኢትዮጵያን የንግድ ሚዛን ጉድለት ክብደት አስምረውበታል።

ጠንካራ የውጭ ምንዛሪ ክምችት በማመንጨት ረገድ በኢትዮጵያ እና እንደ ቻይና እና ቬትናም ባሉ በኤክስፖርት የሚመሩ ኢኮኖሚዎች መካከል ያለውን ልዩነት አጉልተዋል። የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ አቅም ውስንነት ንግዱን በማመጣጠን ረገድ ተግዳሮቶችን የሚፈጥር ሲሆን ይህም የወጪ ንግድ እንቅስቃሴን ለማሳደግ ከፍተኛ ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው ነው ያብራሩት።

ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፣ የንግድ ሚዛን ችግሩን ለመፍታት የኢትዮጵያን የኤክስፖርት አቅም ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል። እንደ ማኑፋክቸሪንግ እና ግብርና ያሉ የኤክስፖርት ዕድገትን ለማምጣት አቅም ባላቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት እንዲደረግም መክረዋል።

በተጨማሪም ለኢንቨስትመንትና ለኢኮኖሚ ልማት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣ ውጤታማ የፖሊሲ አተገባበር እና በሀገር ውስጥ ምርት ላይ ማተኮር የንግድ እጥረቱን ቀስ በቀስ በመቀነስ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መረጋጋትን ያመጣል ሲሉ ይናገራሉ።

ጀማል (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ጉልህ ለውጦች ካልታዩ፣ የንግድ እጥረቱ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ እንደሚቀር በመግለጽ፤ የዕዳ ጫናውም ሀገሪቱ ወሳኝ በሆኑ መሠረተ ልማቶች እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ያላትን አቅም ሊገድብ እንደሚችል ጠቅሰዋል፡፡ ይህም የኢኮኖሚ ጥገኝነት አዙሪት እንዲቀጥል ያደርጋል ነው ያሉት፡፡

ሁለቱም የኢኮኖሚ ምሑራን በኢትዮጵያ እያደገ የመጣውን የንግድ ሚዛን ጉድለት ለመፍታት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረግ እንዳለባት ይስማማሉ። መፍትሔዎቹ የሀገር ውስጥ ምርትን በማሳደግ፣ ኤክስፖርትን በማስተዋወቅ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ እና የፖለቲካ መረጋጋትን በማረጋገጥ ላይ ያተኮሩ መሆን እንደሚገባቸውም ያነሳሉ።

እንደ ዘርፉ ባለሙያዎች እይታ፣ እነዚህ እርምጃዎች ኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንድታስመዘግብ እና በውጭ ዕርዳታ እና ብድር ላይ ያላትን ጥገኛ እንድትቀንስ ይረዳታል። እነዚህ ወሳኝ ለውጦች ከሌሉ ግን የንግድ እጥረቱ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ይቆያል። ይሁን እንጂ ለታለሙ ኢንቨስትመንቶችና የፖሊሲ ማስተካከያዎች ኢትዮጵያ የንግድ ጉድለቷን ቀስ በቀስ በመቀነስ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት የማስመዝገብ አቅም እንዳላትም አመላክተዋል፡፡

# በገበያ ማዕከላቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የገበያ ማዕከላቱን እንዲያስተዳድሩ ለሁለት የግል ድርጅቶች የተሰጠ ሲሆን “ሀብ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር” የአስተዳደሩን ሥራ “ኢትዮ ጥበቃ አገልግሎት” ደግሞ የፅዳትና የጥበቃ ሥራውን ለመሥራት ጨረታ አሸንፈው የተመረጡ ድርጅቶች መሆናቸውን ቢሮው ትናንት ገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ድርጅቶቹ ከሐምሌ አንድ ቀን 2016 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ወደሥራ እንደገቡ እና ለሦስት ወር የሚቆይ መሆኑን ገልጸው የግብይት ሥርዓቱ በየሳምንቱ ንግድ ቢሮ በሚያወጣው ተመን እንደሚካሄድ ተናግረዋል። ይህም ማለት አጠቃላይ ሂደቱን ቢሮው የሚቆጣጠር መሆኑን ነው የገለጹት።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በውስጥ አቅም የሚሠሩ ሥራዎችን ለ3ተኛ ወገን በማስተላለፍ መሥራት የሚያስችል ውሳኔ በዚህ ዓመት ኅዳር ወር ላይ ማስተላለፉ ይታወሳል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ በዚህ መሠረት ቢሮው በከተማ አስተዳደሩ የተገነቡትን የኮልፌና የለሚኩራ የገበያ ማዕከላትን ለሦስተኛ ወገን አስተላልፏል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ በመዲናችን እየተስተዋለ ላለው የኑሮ ውድነት ዋነኛ ምክንያቱ የምርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው ያሉት አቶ ቢኒያም፤ ይህንን ለመቅረፍ ከተማ አስተዳደሩ ስትራቴጂካዊ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም በከፍተኛ በጀት በመዲናዋ መግቢያ በሮች ግዙፍ የገበያ ማዕከላትን በመገንባት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ ነው ያሉት።

የገበያ ማዕከላቱ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በለሚ ኩራ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች የተገነቡ ሲሆን እነዚህም እየተስተዋለ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ ባለፉት አራት ወራት በመዲናዋ መግቢያ በሮች በሚገኙ የገበያ ማዕከላት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ግብይት ፈጽመዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በእነዚህ የገበያ ማዕከላት የሚቀርቡ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ ውጪ ካለው የምርቶች መሸጫ ዋጋ ከ 10 እስከ 15 በመቶ ቅናሽ ይኖራቸዋል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ አገልግሎቶቹን ለ3ተኛ ወገን ማስተላለፍ ያስፈለገው ንግድ ቢሮ የሚያስቀምጠውን የዋጋ ተመን፣ የፅዳትና የጥበቃ ሥራዎች ላይ ጠንካራ ቁጥጥር ለማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህም ሸማቹ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ያስችላል ያሉት አቶ ቢንያም፤ ሥራው እየተጠናከረ ሲሄድ በከተማዋ የሚታየውን የዋጋ ንረት በእጅጉ ለመቀነስ ያስችላል ብለዋል።

# እስከ ሦስት ዓመታት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል ልጃቸውን ይዘው ያቀናሉ፡፡ በዚህ የሕክምና ማዕከልም ልጃቸው እየተመላለሰ ክትትል ማድረግ ቢጀምርም ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ለመታከም በርካታ ወረፋ በመኖሩ መጠበቅ ግድ ይላቸዋል፡፡

ወ/ሪት ገነት በማዕከሉ ወደ ውጭ ሄዶ ለመታከም ሕክምናውን የሚጠብቁ በርካታ ሕጻናት በመኖራቸው ሕጻን ሐዋርያ ወደ ውጭ ሄዶ ለመታከም ሦስት ዓመት ወረፋ መጠበቁን ተናግረዋል፡፡

ሐዋርያ ሕክምናውን ባላገኘባቸው ዓመታት ለመጫወት፣ እንዲሁም ምግብ ለመመገብ እጅግ ፈታኝ እንደነበር አስታውሳ፤ በሦስት ዓመታት ውስጥ ሦስት ጊዜ ጥቁር አንበሳ አልጋ ይዞ መተኛቱን ታስታውሳለች፡፡

እነዚህን ሁሉ ጊዜያት አልፈው አሁን ላይ ሕጻን ሐዋርያ በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል በኩል ወደ እሥራኤል ሄዶ ሕክምናውን ማግኘቱንና ከተመለሰ ስድስት ወር መሆኑን በመግለጽ፤ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ጤንነት ላይ እንደሚገኝ ገልጻለች፡፡

ሕጻን ሐዋርያ ሕክምናውን አግኝቶ ቢመጣም በማዕከሉ ግን በርካታ ሕክምና ፈላጊ ሕጻናት መኖራቸውንና በወረፋ ጥበቃ በርካታ ሕጻናት እየተሰቃዩ ሕይወታቸው እያለፈ መሆኑንም ወይዘሪት ገነት ትናገራለች፡፡

ለዚህም መንግሥት ሀገር ውስጥ ሕክምናው እንዲሰጥ ቢሠራ አልያም ሕክምናውን ከሚሰጡ ሀገራት ጋር በመነጋገር በወረፋ ጥበቃ የሚያልፈውን ረጅም ጊዜ ለመቀነስ ቢሠራ መልካም ነው ስትል ጠይቃለች፡፡

ሌላኛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሀሳባቸውን የሰጡት ቃልኪዳን ምሕረቱ ልጃቸው ሀሌሉያ አሥራት ከተወለደች ጀምሮ አተነፋፈሷ ልክ አለመሆኑን ማስተዋላቸውንና በተወለደች ዘጠኝ ቀን ወደ ኢትዮጵያ ልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል መሄዳቸውን ይናገራሉ፡፡ በዚያም ልጃቸው የልብ ክፍተትና ጥበት እንዳለባት ይሰማሉ፡፡

የልጃቸው ሕመም ሕክምና በሀገር ውስጥ እንደማይሰጥ የሰሙት እናትም ልጃቸውን ወደ ውጭ ልኮ ወደሚያሳክምላቸው ማዕከል ከአራስነት ጊዜያቸው ጀምሮ መመላለስ መጀመራቸውን ይገልጻሉ፡፡

በዘጠኝ ቀኗ ወደ ማዕከሉ ያቀናችው ሕጻንም ወረፋ በመጠበቅ ዓመታት ተቆጥረው የናፈቀችው ወረፋ በሦስት ዓመቷ ደርሷት ወደ እሥራኤል ሄዳ ታክማ መጥታለች፡፡

ሕጻኗ ሕክምናውን ካገኘች ወዲህ በጥሩ ጤንነት ላይ እንደምትገኝ የገለጹት እናት፤ ልጃቸው ሕክምናውን ባታገኝ እንዴት ልትሆን እንደምትችል ማሰብ እንኳን እንደሚከብዳቸው ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን አሁንም በርካታ ሕጻናት ሕክምና አጥተው ስቃይ ላይ መሆናቸውን የገለጹት እናት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚችለውን ድጋፍ ቢያደርግ መልካም ነው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር ሚልኮል መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ደርጅት እንደገለጹት፤ ማዕከሉ የተለያዩ የልብ ሕክምና የሚፈልጉ ሕጻናት በሀገር ውስጥ እንዲሁም ወደ ውጪ በመላክ በነፃ ሕክምና የሚሰጥ ግብረ ሠናይ ድርጅት ነው፡፡

በማዕከሉ የደም ስር ውስጥ ሕክምናና የልብ ቀዶ ሕክምና የሚሰጥ ሲሆን እነዚህ አገልግሎቶች በመንግሥት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና በሦስት የግል ሆስፒታሎች ብቻ ይሰጣል፡፡ ይህም ሆኖ ሕክምናው እስከ ግማሽ ሚሊዮን ብር የሚጠይቅ በመሆኑ አብዛኛው ሰው ይህንን ማዕከል እንደሚመርጥ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በማዕከሉ ስምንት ሺህ የሚሆኑ ሕጻናት ሕክምናውን ለማግኘት ወረፋ እየጠበቁ መሆኑን የገለጹ ሲሆን አንድ ሕጻን ወረፋ ደርሶት ሕክምናውን እስኪያገኝ በአማካይ ከአራት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ እንደሚጠብቅ ገልጸዋል፡፡

ይህ የሚሆነውም በዋነኝነት በሀገሪቱ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ፣ ለልብ ሕክምና የሚውሉ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ አለመመረቱና ውድ መሆን፣ ለዚህ ሕክምና የሚውሉ ግብዓቶች ሀገሪቱ ከምታስገባቸው የመድኃኒት ዝርዝር ውስጥ አለመካተት፣ የአማራጭ የሆስፒታሎች እጥረት እንዲሁም የአቅም ማነስ ዋነኛዎቹ ችግሮች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ለዚህም ኅብረተሰቡ ባለው አቅም ማዕከሉን በመደገፍ እንዲሁም በጤና ሴክተሩ ያሉ የመንግሥት ተቋማት በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ትኩረት በመስጠት መፍትሔ እንዲሹ ጠይቀዋል፡፡

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# “የባሕር በር ጉዳይ የመተንፈስ አለመተንፈስ ጉዳይ ነው”

ረዳት ፕሮፌሰር ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር)
በአዳማ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር


ፎቶ ፡- ገበበ ገብሬ

**አስቴር ኤልያስ**

የዛሬው የዘመን እንግዳችን ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር) ይባላሉ። የአዳማ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ መምህር ሲሆኑ፣ ያጠኑት የቅየሳ እና ካርታ ሥራ ምሕንድስናን ነው። እስከ ሦስተኛ ዲግሪያቸው የሠሩትም በዚህ ዘርፍ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳሉ የጂኦግራፊ እና ታሪክ መምህር ነበሩ። በአሁኑ ወቅት የሚያስተምሩት በአዳማ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ሲቪል ኢንጂነሪግ አርክቴክቸር ጂኦማቲክስ ኢንጂነሪንግ ዲፓርትመንት ውስጥ ሲሆን፣ ረዳት ፕሮፌሰር ሆነው ያገለግላሉ። በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሪሰርች ኤንድ ፐብሊኬሽን ኦፊስ ዳይሬክተርም ሆነው አገልግለዋል።

ኖውሌጅ ኤንድ ቴክኖሎጂ ኢንተርቼንጅ ፋውንደር ዳይሬክተር ሆነውም ሠርተዋል። ስኩል ኦፍ ሲቪል ኢንጂነር ኤንድ አርክቴክቸር ዲፓርትመንት ዲን እንዲሁም የሰርቬይን ትምህርት ክፍል ዲፓርትመንት ሄድ በመሆን ሠርተዋል። በኢትዮጵያ ቻሪቲስ ኤንድ ሶሳይቲስ የፕሮፌሽናል አሶሴሽን ውስጥ አሶሴሽኖችን በመወከል በቻሪቲስ ኤንድ ሶሳይቲስ ፎረም የቦርድ አባል ሆነው ወደ ዘጠኝ ዓመት አገልግለዋል።

የኢትዮጵያ ሰርቬይን ፕሮፌሽናል አሶሴሽን ፋውንደር ፕሬዚዳንት ሆነው እየሠሩም ይገኛሉ። በሌሎች የሕዝብ ልማት ድርጅቶች ውስጥ ይሳተፋሉ። እኚህ ምሑር፣ “የግብፅና አጋሮቿ ጠላትነት እስከ መቼ” በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትመው ለአንባቢያን አቅርበዋል። |አዲስ ዘመንም ከባሕር በር እና ከቀይ ባሕር ጋር አያይዞ በዘርፉ ሰፋ ያለ ጥናት ያካሄዱትን ጥላሁን ኤርዱኖን (ዶ/ር) የዛሬ እንግዳ አድርጎ አቅርቧል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከባሕር በር አንጻር ያላትን ታሪክ በአጭሩ ይግለጹልን?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ ትንሽ አገር አይደለችም። እንደሌሎቹ አገራት ከቅኝ ግዛት በኋላ የተፈጠረችም አይደለችም። በጣም በጣት ከሚቆጠሩ ጥንታዊ ሀገራት መካከል አንዷ ነች። ይህን እውነታ የምናውቀው እኛ ብቻ ሳንሆን ሌሎችም የጻፉለትና የተናገሩለት ሐቅ ነው። እንዲያውም ትክክለኛውን መናገር ካስፈለገ ኢትዮጵያ የምትወሰነው በባሕር ብቻ አይደለም፤ በውቅያኖስም ጭምር እንጂ። ምክንያቱም ውቅያኖሶችም የእኛ እንደነበሩ በግልጽ የሚያሳዩ ታሪካዊ ካርታዎች አሉና ነው።

ለምሳሌ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን የሚያውቁት በምሥራቁ በኩል በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ ያለ ታሪክ መኖሩን ነው። ከአፍሪካ በስተምዕራብ ያለው አትላንቲክ ውቅያኖስ ራሱ የኢትዮጵያ የሆነ እና ደቡብ ውቅያኖስ የሚባል እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን፣ በቅርቡ “የግብፅና አጋሮቹ ጠላትነት እስከ መቼ?” በሚል ርዕስ ለሕትመት ባበቃሁት መጽሐፌም በመረጃ ተደግፎ የሰፈረ ሐቅ ነው።

አትላንቲክ ውቅያኖስ ማለት በአሜሪካ እና በአፍሪካ መካከል የሚገኝ ውቅያኖስ ነው። ይህ እውነታ እኛ ኢትዮጵያውያን የጻፍነው ወይም ደግሞ የኢትዮጵያ ወዳጆች የጻፉት ታሪክ ብቻ አይደለም። የዓለም አሳሾች የሠሩት ካርታም ጭምር አለ፤ በተጨማሪም ታሪክም አለ። የታሪክ ድርሳናትም ጉዳዩን ይናገራሉ። ይህ ጉዳይ በቻይናውያን ተጽፏል። በባቢሎናውያን ተጽፏል። እንዲሁም በሮማውን ተጽፏል። ረፈድ ብሎ ደግሞ በእነጣሊያን፣ ጀርመን፣ እንግሊዝ እና በመሰሎቻቸው ተጽፏል። ስለሆነም እኛ የሚመለከተን ስለባሕር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ስለውቅያኖስም ጭምር ሲሆን፣ ውቅያኖስ ራሱ የኛ ነበር ማለት ነው። አትላንቲክም ሆነ ሕንድ ውቅያኖስ ከእኛ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ስለዚህም ምንም የሚያጠራጥርም ሆነ ግርታ የሚፈጥር ነገር የለውም።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቅርብ ርቀት የሚገኘውን የባሕር በር ተፈጥሯዊ ሀብቷን የተነጠቀችበት ሂደት ምን ይመስላል?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** በተቃራኒው ምስጋና ይገባቸዋል መባል ከተቻለ ምስጋና የሚሆነው ለቅኝ ገዥዎች ነው። ከራሳቸው ሀገር ወጥተው ሌላን በመመኘት ለመዝረፍና ለመንጠቅ እንዲሁም ባሪያ ለማድረግ የዘመቱ የአውሮፓ ኃይሎች ናቸው። እኛ የባሕር በር ቀርቶ የውቅያኖስ በር ያለን ነበርን። ተስፋፊዎች ኢትዮጵያን በቁጥጥር ስር ማዋል ሲያቅታቸው በተለያየ መንገድ እየገዘገዙና በአሳሾች እየሰለሉ፣ የሀገር ጎብኚዎች በመምሰል የሀገር ምስጢር እያወጡ ሲገዳደሩን ኖረዋል። ለምሳሌ በመጀመሪያ በአሰብ አካባቢ ጣሊያኖች የተቆጣጠሩት እና የሰፈሩት በቀላል መንገድ ነበር። በእዛ አካባቢ ሡልጣን ነበሩ፤ ታሪኩ የሚጀምረው እርሳቸው ለዓሣ አስጋሪ ጣሊያናዊ ከአሰብ አካባቢ የተወሰነችን ቦታ ሸጠው ነው።

ከዚያ በኋላ እንደ ፍልፍል እየፈለፈሉ አሁን ኤርትራ የምትባለውን አካባቢ ጣሊያኖቹ በቁጥጥር ስር አደረጉ። ይህም ማለትም ከኤርትራ ሰሜናዊ ጫፍ እስከ ጂቡቲ መጨረሻ ድረስ ያለውን ስፍራ ነው። ይህም ከአንድ ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የሚሆን የባሕር በር ነው። አራት እና አምስት ሚሊዮን የማይሞላ ሕዝብ ያላት ኤርትራ፣ አንድ ሺ ኪሎ ሜትር የባሕር በር ይዛ 120 ሚሊዮን ሕዝብ የምታስተናግድ አገር ኢትዮጵያ ደግሞ በ60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የባሕር በር አጥታ ትኖራለች ማለት ነው።

ስለዚህ ይህ ሀብቷ የተነጠቀው በራሳችን ጥፋት ነው። በእርግጥ ጣሊያኖች የሚኮነኑት ኤርትራን በቁጥጥር ስር አውለው በማስተዳደራቸው ብቻ አይደለም፤ ከዚያ አካባቢ ላለመውጣት እንደእነእንግሊዝ፣ እንደእነጣሊያን ሌሎችም ቅኝ የገዙ ሀገሮች በሙሉ ቀብረውት የሚሄዱት መጥፎ መጥፎ ነገር ነበረም፤ አለም። ኤርትራ የጣሊያን ቅኝ ግዥ በነበረችበት ወቅት ለኤርትራውያን ይፈቀድ የነበረው ሲኒማ ቢዶቲ የሚባል ሲኒማ ቤት ብቻ ነው። እሱም በግልጽ ስድብ ባዘለ ስያሜ የሚጠራ ሲኒማ ቤት ነበር።

በወቅቱ ኤርትራውያን ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማሩ ሲደረጉ ነበር። ይህ ሁሉ ግፍ ተፈጽሞባቸው እንኳን የወቅቱ ተቃዋሚዎች “በጣሊያን ቅኝ ተገዝተን ስለነበር ከኢትዮጵያ እንነጠል፤ ከዚያም የቅኝ ግዛቱ ውል እና የድንበር ውል ይከበርልን” የሚል ሐሳብ ይዘው ተነሱ። በዚህም ሀሳብ ታገሉ። ይህን ሁሉ ትግል ሲያደርጉ የነበረው አንድ ሺ ኪሎ ሜትር የባሕር በር ለመያዝ ነው።

በእርግጥ የባሕር በር ሀብታችንን መልሰን ይዘነው ነበር። ዳግም ልንነጠቅ የቻልነው ጣሊያኖች ይዘውት ስለነበር ነው፤ እንግሊዞች ደግሞ ከጣሊያኖች ወስደው በሞግዚትነት አስር ዓመት አስተዳደሩ። ከዚያ በኋላ እንደገና በአፄ ኃይለሥላሴ ሰፊ ትግልና ተጋድሎ አምጥተነው ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያን ኃያልነትን የማይደግፉ ኃይሎች መልሰው ደግሞ ውስጥ ለውስጥ ሴራ መሸረብ ያዙ። በተለይ ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የእነሱዳን እና ግብፅ መሰሪነት እየበረታ መጣ። ከእነርሱ ጀርባ ያሉ 22 የዓረብ ሀገራት በሙሉ ከእነርሱ ጋር በመተባበራቸውም መልሶ ከእጃችን ወጣ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያን ከባሕር በር ቀጣና የማሸሹ ፍራቻ እና ተገፍታ የመውጣቷ ምስጢር ከምን የተነሳ ነው ይላሉ?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ምስጢሩ በዋነኝነት ከኢትዮጵያ የተለየ ባሕሪ ነው የሚል እምነት አለኝ። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የውሃ ማማ ናት። በዙሪያዋ ባሉ በሁሉም አገሮች ዘንድ ማለት ይቻላል የውሃ ችግር አለ። ሌላው ቀርቶ ከኬንያ ጋር በራሱ ከውሃ ጋር የተያያዘ ችግር አለ። ኬንያ ቱርካና ሐይቅ የሚገባው የኦሞ ወንዝ እንዳይነካ ትፈልጋለች። የኦሞ ወንዝ ተብሎ የሚጠራው ከኢትዮጵያ ከተለያየ ቦታ የሚነሱት ግቤ ወንዝ እና ዋቤ ወንዝ ተቀላቅለውት ነው። እንደሚታወቀው ደግሞ የኢትዮጵያ ወንዝ ወደሁሉም አቅጣጫ የሚፈስ ነው።

ምንም እንኳ ዓረቦች የቱንም ያህል ስጋት ቢኖራቸውም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ የሰውን የማይነካ የራሱን የማይሰጥ ነው። ሌሎቹ ሀገራት በቅኝ ግዛት ሲገዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተገዛ ሕዝብ ነው። በቅኝ ገዥዎች ያለመገዛቱ ምስጢር የራሱን መስጠት ስለማይፈልግና የሌላውንም መውሰድ ስለማይፈልግ ነው። የብዙዎቹ ሀገራት ትልቁ ፍራቻቸው ኢትዮጵያ ወንዞችን ገድባ ውሃ ታሳጣናለች ከሚል የመነጨ ነው። ይህን የምታባብሰው እና ድራማውን የምትጫወተው ደግሞ ግብፅ ናት።

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር በርን በተመለከተ የኢትዮጵያ መሪዎች የዘመናት አቋምን እንዴት ይመለከቱታል?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ከጥንቶቹ እንጀምር፤ እኛ ኢትዮጵያውያን በአብርሃ እና አፅብሃ ዘመን ቀይ ባሕርን ተሻግረን የመንን፣ ከፊል ሳዑዲ ዓረቢያንም አስተዳድረናል። ቀይ ባሕር ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አልነበረም፤ አይደለምም፤ ከዚያ ቀጥሎ አፄ ቴዎድሮስን ብንመለከት እንዲያውም እርሳቸው ሁሌ የሚታወሱበት አንድ አባባል እንዳለ እናውቃለን። አፄ ቴዎድሮስ፣ የኢትዮጵያ ግዛት እስከኢየሩሳሌም መሆኑን ሲናገሩ የሚደመጡ ነበሩ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ግዛት እንኳን ቀይ ባሕር ቀርቶ እስከ ሜዲትራንያንም የሚዘልቅ መሆኑ የሚታመን ነው።

ወደ ዓፄ ዮሐንስ ስንመጣ፤ በግልጽ ቋንቋ የተቀመጠ ነገር አለ። እንዲያውም በቅርብ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ባሕር በር ነች፤ ድንበርም ነች። ወደ ዓፄ ምኒሊክ ዘንድ ሲመጣ ደግሞ ከጣሊያን ጋር ስንዋጋ በረሃብ የተነሳ ድርቅና እልቂት ነበር። ጣሊያንን ከኤርትራ ገፍተው ወደእኛ ሲገባ ወደምፅዋ መግፋት ግን አልቻሉም። ጣሊያን በአየር ከላይ ሲያዘንብብን የነበረው መርዝ ነው። እንዲያም ሆኖ ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆኖ የወጣችበት ጦርነት እንደነበር የአደባባይ ምስጢር ነው። ዓፄ ምኒልክ ኤርትራን ከጣሊያን እጅ ነፃ ለማውጣት የሚታሙ አይደሉም። ከኤርትራም ለማስወጣት ፍላጎት ነበራቸው፤ ይሁንና ፍላጎት ብቻ ምንም ዋጋ የለውም። ዓድዋን አስለቅቀው አሁን ያለውን በትግራይ በኩል ሰሜናዊ ድንበርን ይዘው እንዲቀመጡ ያስገደዳቸው የጣሊያን መርዝ የሚረጭ ሁኔታ እና ተፈጥሮ ነው።

ወደ ዓፄ ኃይለሥለሴ መለስ ስንል ደግሞ ኤርትራን መልሰው ከኢትዮጵያ ጋር ቀላቅለው ነበር። በዚህም የአንድ ሺ ኪሎ ሜትር የቀይ ባሕር ባለቤት፣ የእነዳህላክ ወደቦች ባለቤት አድርገውንም ነበር። መንግሥቱም መጨረሻ ላይ በማይጠበቅ መንገድ ከሀገር ቢሸሽም ለዚያ ሲሟሟት እና በእጅጉ ሲጋደል የቆየ ነው። እድሜውንም ሙሉ ሲታገል ኖሯል።

ቀደም ሲል ነበረው አገዛዝ ግን ሁልጊዜም በታሪክ ተወቃሽ ነው። የቅኝ ግዛት ድንበር እንዳለ ተግባራዊ እንዲደረግ በመወትወት ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንድትሆን ፈረዱባት። 120 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደብ ገዝቶ ይኑር የሚል ፍርድ በኢትዮጵያ ላይ የተፈረደው በቀድሞ መንግሥት ነው።

የቅድመ አያቶቻችንና የአያቶቻችን ታሪክ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር ግን ለሀገራቸው ጥቅም መከበር የሚሞቱ መሆናቸውን ነው። እነርሱ ለሀገራቸው ጥቅም ለመቆም ቅንጣት ታህል አያመነቱም። የኢትዮጵያ የሆነውን ቅንጣት ታህል መሬትም አይሰጡም። የሌላውን ስንዝር ታህልም መሬትም አይፈልጉም።

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር በር ማጣት የሚያስከትሉ ጉዳቶችን በተመለከተ ዘርዘር አድርገው ቢያብራሩልን?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** የባሕር በር ማለት የመተንፈስ አለመተንፈስ ጉዳይ ነው፤ የገቢና ወጪ ምርት ጉዳይ ነው። ያመረትነውን ወደውጭ የምናስወጣበት፤ ከውጭ የሚመጣውን ደግሞ የምናስገባበት ጉዳይ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ የባሕር በር የተዘጋባቸው ሀገሮች የባሕር

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## “የባሕር በር ጉዳይ የመተንፈስ...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

በር እጦት አደጋ የሚሆንባቸው በጦርነት ጊዜ ነው። ለምሳሌ ከአንዱ የአፍሪካ ወይም የዓረብ ሀገር ጋር ጦርነት ብንገጥም የጦር መሣሪያ የምናስገባው በየትኛው ወደብ ነው? እንደሚታወቀው ደግሞ ሁሉን የጦር መሣሪያ እኛ አናመርትም። የማናመርት ከሆነ ደግሞ የተመረተውን መግዛት የግድ ነው፡።

ለምሳሌ የምንዋጋው ከሱዳን ጋር ነው ብንል፤ ጅቡቲ ፈልጋም እንኳ ባይሆን የዓረብ ሊግ አባል ሀገራት ጋር የአባልነት ስምምነት መሠረት የአንዱን አባል ሀገር ጥቅም የሚጎዳ ነገር በወደብ ማሳለፍ አትችልም። አደጋው እዚህ ላይ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ወደብ ቅንጦት አይደለም። ወደብ እንደእኛ አይነት ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለው ሀገር ከ60 ኪሎ ሜትር ባነሰ ከቀይ ባሕር በቅርብ ርቀት ላይ ሆኖ አለማግኘት ማለት ከባድ ነው።

ይሁንና ተፈጥሯዊ መብት ያለን ከመሆናችንም በላይ ቀይ ባሕር የሚለውን ስያሜ ያወጣነው እኛ ነን። ዛሬ የዓለም ሕዝብ በእንግሊዝኛ (Red sea) እያለ ሊጠራው ይችላል። ምክንያቱም እነርሱ የእኛን ተረጎሙት እንጂ እኛ የእንግሊዝኛውን ስያሜ ወደ አማርኛ አልተረጎምንም። በመሆኑም በታሪክ እኛ ጥንታዊ ነን። ለዚህ ደግሞ ማረጋገጫ ሊሆን የሚችለው ትልቁና ዋነኛ ተጠቃሽ የሚሆነው እንደእነሉሲ አይነት ታሪክም ጭምር ነው። ይህ የሰው ዘር መገኛነታችንን የሚያመላክት ነው። ከዚህ የተነሳ ወደብ አጥቶ መኖር ፈታኝ ነው። እንዲያም ሆኖ አደጋው ገና አልተሰማንም።

በየጊዜው ጅቡቲን እያሳደግን እኛ የምንቆረቁዝበት ምክንያት መኖር የለበትም። ይህን ማስተዋል የምንችለው ግን ኢንዱስትሪዎቻችን በሚፈለገው ልክ እያመረቱ ባለመሆናቸው ነው። በአሁኑ ወቅት ጉዳቱ ያን ያህል ያልቆረቆረን የምናስገባው ብቻ በብዙ ስለሚበልጥ ነው። በጥቅሉ የባሕር በር የማጣት ጉዳቱ በአንድ ነገር ብቻ የሚለካ ሳይሆን በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውም ሆነ በማኅበራዊው ጉዳይ ሁሉ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል የባሕር በር የማጣት ጉዳይ በባሕር ውስጥ የሚገኘውንም ሀብት ጭምር የሚያሳጣን ነው። የወደብ ጥገኝነት ከኢኮኖሚ ጥገኝነት የባሰ ነው። የወደብ ጉዳይ ከብዙ ነገር ጋር የሚያያዝ ነው። ከውጭ የሚመጣን ጠላት ለመከላከል ጠላትን መያዝ የሚገባው ባሕሩን ከመሻገሩ በፊት ነው። ባሕሩ የእኛ ካልሆነ ግን የሚመጣው በምድር ስለሆነ ቀጥታ ወደእኛ መዝለቅ ይችላል። ከዚህም የተነሳ የባሕር በር የማጣት ጉዳቱ መጠነ ሰፊ ነው በሚል መግለጹ የተሻለ ነው።

በመሆኑም ወደብ ለኢትዮጵያ የግድ ነው። እንዲህ ሲባል ግን የማንንም መብት ለመቀማት አይደለም። ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ወደቦች የነበሩና ዝም ብለው አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ አሉ፤ እነዚያም አገልግሎት መስጠት ቢችሉ መልካም ነው።

ኤርትራ አሰብን እና ምፅዋን ካልተጠቀመችበት ምን ያደርግላታል? ሱዳን፣ ግብፅ፣ ኬንያ፣ ሱማሊያ ሆነች ጅቡቲ ወደብ አላቸው። የኤርትራን ወደቦች ኢትዮጵያ ካልተጠቀመችባቸው ማን ይጠቀምባቸዋል? የኤርትራ ሕዝብስ ቢሆን የኢትዮጵያን የባሕር በር በመዝጋት የሚጠቀመው ነገር ምን አለ? ችግሩ ኤርትራ ውስጥም ስለኤርትራ የሚያስብ አለመኖሩ ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥም በዘር፣ በጎሳ እና በሥልጣን የተተበተበ እንጂ ለኢትዮጵያ የሚያስብ ባለመኖሩ ነው። ቢኖር ሁለቱ ሀገሮች የሚቸገሩበት ምክንያት አይኖርም ነበር ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር በር አጠቃቀምን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ሕጎች ምን ይላሉ? ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ጥያቄዋ ምን ያህል ተገቢ ነው ይላሉ?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ከዚህ ጥያቄህ በፊት አስቀድሜ ላነሳ የምፈልገው ነገር የትኛው ዓለም አቀፍ ሕግ ነው? ማነውስ ነው ሕጉን የሚያከብረው? ሕጉንስ ቢሆን ማን ነው ያወጣው? በመሠረቱ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚባለው በአብዛኛው ከቅኝ ግዛት በኋላ ቅኝ ገዥዎች መጥተው በሀገራት መካከል የሠሩት ድንበር ነው። አንደኛውን ሕዝብ ከሌላኛው ሕዝብ ጋር እያጋጩ ለመኖር ትክክል ያልሆነ ድንበር ፈጠሩ። ልክ ያልሆነውን ሕግ ነው ዓለምአቀፍ ሕግ በማለት መርሕ ሆኖ የሚመጣው እንጂ ሀገሮች አሊያም ሕዝቦች ተስማምተው ያወጡት ሕግ የለም። ያለው የቅኝ ገዥዎች ኃያላን የሚባሉ ሀገሮች ለራሳቸው በሚመች መንገድ ያወጡት ሕግ ነው።



እንደዚያ ከሆነማ አሜሪካ ከጎረቤቷ ጀምሮ ስንት እና ስንት የሌላ የሆነውን ግድብ አፈረሰች? ለምሳሌ የሜክሲኮን አፍርሳ ስትሠራ ማን “ተይ!” አላት? አንዳንዶቹ ኃያላን ሀገራት ሥራቸውን የሚሠሩት ዝግት አድርገው ነው። ምንም አይነት ነገር ሳይሉ ነው። የቅኝ ግዛት ውልን እና ድንበርን ይከበር የሚሉት ለዚህ ነው። ለምሳሌ ኤርትራ በጣሊያን ቅኝ ተገዝታ ስለነበር ጣሊያን ባሰረችው መስመር ብቻ ተወሰናችሁ ኑሩ እያሉን ነው።

ስለዚህ ስለምንድን ነው ስለዓለም አቀፍ ሕጉ እንድናስብ የምንደረገው? ማሰብም የለብንም፤ መስመር አስምረው የሚሰጡን እነርሱ ናቸው እንዴ? ያልተጋበዙ እንግዶች መጥተው አልጋችንን ሊወርሱ አይገባም፤ ከሆነም ሊተኙ የሚገባው ያነጠፍንላቸው ቦታ ነው። ስለዚህ የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት በሚፈታተንበት መንገድ የሠሩት ድንበር መፍረስ አለበት። በእነርሱ ብቻ የወጣው ዓለም አቀፍ ሕግም መፍረስ አለበት ባይ ነኝ። በተለይ ቅኝ ግዛት የሚባል ውል መፍረስ አለበት።

የግብፅን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል። ግብፅ ሁለት አስገዳጅ ስምምነቶችን ማለትም የ1929 እና የ1959ኙን እንድናፀድቅ ትሻለች። የ1929ኙ እንግሊዝና ግብፅ የተፈራረሙት ነው። ይህ ማለት ቅኝ ገዥው እና ቅኝ ተገዥው ነው። ሁለቱ ብቻቸውን የተፈራረሙት ደግሞ ውሃ አመንጪዋ ሀገር ኢትዮጵያ በሌለችበት ነው። የ1959ኙ ደግሞ ግብፅ እና ሱዳን የውሃ ክፍፍልን አስመልክተው ተፈራረሙ። አንድ መለኪያ ውሃ የማያመነጩ ሀገራት ውሃ ሲከፋፈሉ ዝም ብለን ያየነው ጉዳዩን ማስረዳት አቅቶን ነው የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ከዚህ የተነሳ የግብፅ እና የሱዳን መንግሥታት የሚያራምዱት ሞራል የሌለው ፖለቲካ ነው። እንዲያው ተሳክቶላቸው ግብፅ እና ሱዳን ውሃውን ይከፋፈሉ እንበል፤ ታዲያ ስለምን ኢትዮጵያን አላካተቱም? ሲሆን ሲሆን ማካፈል የነበረባት ውሃ አመንጪዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት። ስለዚህ ዓለም አቀፍ የሚባል ሕግ የለም። ዓለምን እየመራ ያለው ጉልበተኛ የሆነ አካል ነው። በመሆኑም አንድነታችንን አጠናክረን ከጎረቤቶቻችን ጋር ሆነን በጋራ ሊገዛን የሚችል ሕግ ማውጣት ነው ያለብን እንጂ የዓለም አቀፉ ሕግ አዋጭ መሆን አልቻለም።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ በፊት በሀገር መሪ ደረጃ ሳይቀር ወደብ ሸቀጥ እንደሆነ ሲነገር ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የመኖር አለመኖር ጉዳይ እንደሆነ ታምኖበታል፤ ከዚህ አኳያ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ከዚህ በፊት ወደብ ሸቀጥ ነው ሲባል ሰምተናል። በወቅቱ ሸቀጥ የተባለው የኢትዮጵያን ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ለመድፈን ሲሆን፣ ጉዳዩንም አቅልሎ እንዲያይና ጥያቄም እንዳያነሳ በማሰብ ነው። ይሁንና በወቅቱ ኢትዮጵያ ባሏት ምሑራን ወደብ ሸቀጥ እንዳልሆነ ሞግታ ነበር። በወቅቱ ወደብ ሸቀጥ ነው ላሉ አመራር ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ደግሞ ግልጽ ነው። በዚያን ወቅት ወደብ ሸቀጥ ነው በሚል ለሌላ ተላልፎ መተው የኢትዮጵያን አንገት እንደመቁረጥ የሚቆጠር ጉዳይ ነው። ዓላማው የሕልም እንጀራ ሆኖ የቀረ ቢሆንም “ታላቋን ትግራይ” ለመፍጠር ነበር።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን አንድ ማንሳት የምፈልገው ነገር አለ። ግብፆች የአስዋንን ግድብ ከገነቡ በኋላ ግድቡን ለምረቃ አበቁ፤ በወቅቱ ግድቡ ሲመረቅ በርካታ የአፍሪካ መሪዎች ሲጠሩ የውሃ አመንጪዋ አገር ንጉሥ የሆኑት ዓፄ ኃይለሥላሴ ግን አልተጠሩም ነበር። በወቅቱ የነበረው የግብፁ መሪ አብዱል ናስር ሲጠየቁ ያሉት፤ “የዓባይ ጉዳይ ኢትዮጵያን አይመለከትም” ነው። ስለዚህ ግብፆች ጥፋተኛ ማድረግ ካለባቸው መሪያቸውን ነው እንጂ ኢትዮጵያውያንን አይደለም።

በአንድ ወቅት ዓፄ ኃይለሥላሴ የእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤጥን የዓባይ በረሃ ወስደው ባስጎበኙበት ጊዜ ጢስ ዓባይን እያስጎበኟቸው እያለ ዓፄ ኃይለሥላሴ “ይህቺን ግድብ መገደብ እፈልጋለሁና ብር ያስፈልገኛል ያበድሩኝ” ሲሉ ይጠይቋቸዋል። ይሁንና ምላሻቸው የነበረው “አይ! ወዳጃችን ግብፅ ትቆጣለች” ነው። ንግሥቷ፣ እንዲያ ቢሉም አፄ ኃይለሥላሴ ያሉት ነገር ነበር። ይኸውም “ብድር ስጡን ብንል ግብፅ ትቀየመናለች ብለው አይሰጡንም። ” በአሜሪካውያን የተጠና ጥናት ነበርና “ጥናቱ በክብር ይቀመጥ፤ የእኛ ልጆች ይሠሩታል። ” ነበር ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ ወዲህ ኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር በርና የወደብ ጥያቄ ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ነው። በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** ከላይ እንደገለጽኩት የባሕር በር ጉዳይ እስትንፋስ ጉዳይ ነው። ስለዚህም መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ ተገቢ ነው። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በዚህ እንስማማለን። የራሳችን የሆነና እኛ የምናዝዝበት ወደብ ማግኘት አጠያያቂ አይደለም። እንዲህ ሲባል ግን የሆነ ሀገር ወረን የምናገኘው ጉዳይ አይደለም። የውስጥ ሠላማችንን ማስከበር እስከቻልን ድረስ በየትኛውም ጊዜ ወደብ የማግኘት መብታችንን ማስጠበቅ እንችላለን የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም የመጀመሪያው ጉዳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደጋራ ማንነቱ ማምጣት ይቀድማል እላለሁ።

ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ነግሶ የሚታየው የብሔር እና የዘር ፖለቲካ ነው። ባለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት ጥቂቶች ብዙኃኑን የኢትዮጵያ ሕዝብን ለማስተዳደር ሲሉ ሕዝቡን በዘርና በጎሳ መከፋፈልን እንደ መፍትሔ አድርገው ወስደው ነበር።

አሁን ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞ የነበረውን በጋራ አብሮ የመኖር ባሕሉን መመለስ ይኖርበታል። የመተሳሰብና የመከባበር እሴቱን ከወደቀበት ማንሳት ይጠበቅበታል። ለዚህ ደግሞ በመጀመሪያ ሠላም ሊሰፍን የግድ ነው። ሠላም ካለ የሕግ የበላይነት ይሰፍናል፤ መልካም አስተዳደር ይመጣል። መልካም አስተዳደር የሚጀምረው ደግሞ ከታች ከቀበሌ ነው።

መልካም አስተዳደር ካለ የሕግ የበላይነት አለ ማለት ነው። የሕግ የበላይነትም ሠላምም ካለ የልማት ፍላጎት አለ ማለት ነው። ልማት ካለ ደግሞ ብልፅግና አለ። ብልፅግና ሲኖር ምንም ሳንጠይቅ ወደባችንን ተጠቀሙ የሚል አካል በራሱ ጊዜ ይመጣል። ነገር ግን ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ ሠላም መኖር አለበት።

ሠላምን ለማስከበር መንግሥት ረጅም ርቀት መሄድ ይጠበቅበታል። መጀመሪያ የውስጥ ሠላማችን ላይ መሥራት አለብን። ሠላም ሳይመጣ የምንጀምረው የወደብ ጥያቄ መጥፊያችን ይሆናል። እጅግ አደገኛ ነው። በመጀመሪያ ሠላም የሚነሱንን ችግሮች ማምከን አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቀጣናው እና በቀይ ባሕር ላይ ያላትን ተፅዕኖ መልሶ ለማምጣት ምን መደረግ አለበት?**

**ጥላሁን (ዶ/ር)፡-** በቀይ ባሕር ላይ በአሁኑ ሰዓት ምንም አይነት ሚና የለንም። የነበረንን ሚና ካጣን ቆየን። አንደኛ በአሰብ አካባቢ በርካታ ሀብት ነበረን። አሰብ ላይ ያለን ወደብ ብቻ አልነበረም፤ የነዳጅ ማጣሪያም ጭምር እንጂ። ከዚህ ሌላ በጣም ጠንካራ የነበረ የባሕር ኃይልም ነበረን።

ቀደም ሲል እርግጥ በቀይ ባሕር አከባቢ ኢትዮጵያ የነበራት ተፅዕኖ ከፍተኛ ነበር። ያንን ተፅዕኖ ይዛ ቆይታ ቢሆን ዛሬ ላይ የት በደረሰች ነበር? የገነባነው ጠንካራ የባሕር ኃይል ነበርና በሱማሊያ አካባቢ የሚታየው የባሕር ላይ ውንብድና ባልኖረም ነበር። ይሁንና አሁንም ቢሆን ተስፋ የሚቆረጥበት አይደለም። በቀጣይ ተፅዕኖ ይኖረናል የሚል እምነት አለኝ፡። እኔ ተስፋ አልቆርጥም። ይህ ግን የሚወሰነው የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡን የሚይዝበት አያያዝ ሲስተካከል ነው፡።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው በሠላም መኖር ነው። ለፖለቲከኞች ብሎ መሞት አይፈልግም። በተጣመመ ፖለቲካ ምክንያት ደግሞ ሀገራችን እንድትበተን ሕዝቡ አይፈልግም። እና ኢትዮጵያውያን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ ጊዜ እንፈርስ የነበርን ሀገር ነን። ነገር ግን ሕዝቡ እጅግ በጣም ታጋሽ፣ ስብዕናው ላቅ ያለ እና ሀይማኖት ያለው ሕዝብ ነው። ዛሬ ሆዱን እየራበው ነገ ሌላ ቀን ይመጣል ብሎ ተስፋ የሚያደርግ ሕዝብ ነው። ይህንን ሕዝብ ማስተዳደር አለመቻል ደግሞ ከባድ ነገር ነው። ይህ ሕዝብ ለማስተዳደር በጣም የሚመች ነው።

በዙሪያችን ያለው ወደብ በሙሉ ማለት ይቻላል በዓረብ ሊግ አባል ሀገራት የተያዘ ነው። ኤርትራም ተለዋጭ የዓረብ ሊግ አባል ሀገር ነች። ስለዚህ የራሳችን ወደብ የሚያስፈልገን መሆኑ የግድ ነው ማለት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህ ጉዳይ ያሳሰባቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም የምንጠቀምበት የጅቡቲ ወደብ እንደመሆኑ በጊዜ ሒደት ጅቡቲ ተፅዕኖ ውስጥ ልትገባ ትችላለች። ሱማሊያም ብትሆን የተዳከመች ሀገር ከመሆኗ በተጨማሪ አልሸባብም እያስቸገረ ነው። ሌላውም ወደብ የራሱ ተፅዕኖ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የቀድሞ ቅኝ ገዥዎች የእጅ አዙር ተፅዕኖ ያለበት ነው።

ስለዚህ እኛ ወደብ እንድናገኝ ማድረግ ያለብንን ሁሉ በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል። ውስጣዊ ሠላማችንን ስናረጋግጥና ልማታችን ስናፋጥን የጀመርነው የባሕር በርም ሆነ የወደብ ጥያቄ መልስ ያገኛል። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያ ተፅዕኖ ፈጣሪነት ያድጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ጥላሁን፡-** እኔም ዕድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ።

# ግንዛቤና የባህሪ ለውጥ ለወባ መከላከል ስራ

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ የወባ በሽታ አዲስ ክስተት አይደለም። ወባን የማያውቅ የማኅበረሰብ ክፍል የለም። ይህም ሊሆን የቻለው የወባ በሽታ በአብዛኛው ቆላማ አካባቢዎች ላይ የሚከሰት በመሆኑ ነው። አሁን ባለበት ሁኔታና የዓለም ጤና ድርጅት በሚሰጠው ሪፖርት መሰረት በሽታው ከብዙ ሀገራት ቢጠፋም አሁንም ቆላማ በሆኑ የአፍሪካና እስያ አካባቢዎች እንዲሁም የላቲን አሜሪካን ሀገሮች ስርጭቱ እንዳለ ይታወቃል።

ባለፈው ዓመት ከዓለም ጤና ድርጅት በወጣ ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት 245 ሚሊዮን የሚሆን የዓለም ሕዝብ በወባ በሽታ ተይዟል። ከ600 ሺ በላይ የሚሆኑት ደግሞ በዚህ በሽታ ምክንያት ሕይወታቸውን አጥተዋል። ኢትዮጵያም ከፍተኛ የወባ ስርጭት ከሚታይባቸው ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ይሁንና የወባ በሽታ ባለፉት አስር ዓመታት ስርጭቱ በተከታታይ እየቀነሰ መጥቷል። ስርጭቱን በመቀነስ ረገድ ጠንካራ ስራዎች በመሰራታቸው ተከታታይነት ያለው ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ሕይወት ሰለሞን እንደሚናገሩት፣ የወባ ስርጭትን በመቀነስ ረገድ ሁለት አይነት መስፈርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥቅም ላይ ይውላሉ። አንዱ የታማሚ ቁጥር መቀነስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሞት ምጣኔን ማውረድ ነው። ከዚህ አኳያ ለተከታታይ ዓመታት ስኬቶች ተመዝግበዋል። በኢትዮጵያ በተለይ በ2009 ዓ.ም ከ1 ሚሊዮን በታች የወባ ኬዝ የተመዘገበበትና ትልቅ ስኬት የታየበት ሲሆን ከዚህ ዓመት በፊት ከነበሩ ሪፖርቶች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ለውጥ የመጣበት ነው።

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ነበር። በወባ በሽታ የሚሞቱ ሰዎችን ቁጥር ለመቀነስ በተሰራ ስራ ግን ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። ይሁንና ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የወባ ወረርሽኝ እያንሰራራ መጥቷል። በዘንድሮው በጀት ዓመት 4 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በወባ በሽታ ስለመያዛቸውም ሪፖርት ተደርጓል። ይህም ለመንግስትም ሆነ ለማኅበረሰቡ አሳሳቢና የማንቂያ ደውል ሆኗል።

የወባ በሽታን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ስትራቴጂክ ሰነድ በጤና ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ስራዎች እየተሰሩ ነው። ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን መሰረት ያደረጉ ሲከናወኑ ቆይተዋል። አሁንም ቢሆን ስራዎቹ በተጠናከረ መልኩ እየተከናወኑ ይገኛሉ። ወባን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር ስልጠና መስጠትና መመርመሪያ መሳሪያዎችን ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም። መረጃዎችን በደምብ ማጠናቀር በጣም አስፈላጊ ነው። ለዚህም ይህን የሚያግዙ ነገሮች ከግዜ ወደግዜ በአቅምም፣ በሀብትም እየተሟሉ የተሻለ ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

መሪ ስራ አስፈፃሚዋ እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ በየግዜው ወባን ለመከላከል የፕሮግራም ስልቶች ይወጣሉ። ከነዚህ የፕሮግራም ስልቶች ውስጥ አንዱና ጥቅም ላይ የሚውለው የትንኝ ቁጥጥር ስራ ነው። የወባ ትንኝ ቁጥጥር ስራ ሲሰራ በርካታ አማራጮች አሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለወባ ትንኝ ቁጥጥር ስራ ሚመከረው አንዱና ዋነኛው የአልጋ አጎበር መጠቀም ነው። እንዲሁም ለርጭት ምቹ የሆነ ግድግዳ ካለ ኬሚካል መጠቀም ነው። ትንኟ እጭ ሆና ወደጉልምስና የምትቀየር እንደመሆኗ እዚህ ላይም የሚሰሩ ስራዎች አሉ።

ለዚህም ወባን ለመከላከል የሚያግዙ ግብዓቶች ፍትሁነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሁሉም ኬሚካል ሁልግዜ መፍትሄ ያመጣል ማለት አይደለም። ስለዚህ በየዓመቱ የግባቶችን ውጤታማነት መፈተሽ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ጤና ሚኒስቴር ለወባ መከላከል የሚያግዙ ግብአቶችን እንደሚያቀርብ ሁሉ ጥናቶችን ለማድረግ በቂ የሆነ ሀብት ይመድባል። የተለያዩ የምርምር ተቋማትም በተለይ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ የአርማወር ሀንሰንና ሌሎችም ዩኒቨርሲቲዎች ጥናቶች ይሰራሉ። እነዚህን ወደ አንድ በማምጣት በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው መረጃ ይታያል። በሌላው ሀገር ላይ ያለው ችግር ነገ ወደ ኢትዮጵያ ምንም ምክንያት የለምና እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ድምበር ተሻጋሪ ጥናቶችም ይታያሉ። ለምሳሌ በዚህ ሳምንት ከኢጋድ አባል ሀገራት ጋር የጋራ እቅድ ታቅዶ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።



ዶክተር ሕይወት ሰለሞን፣



ዶክተር ጌታቸው ቶሌራ፤

**የአየር ንብረት ለውጥ፣ ግጭቶችና የተፈጥሮ አደጋዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወባ መከላከል ስራ በጤና ሚኒስቴርና በሕክምና ተቋማት ብቻ የሚሰራ ስራ አይደለም**

እንደወባ ያሉ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ቅንጅት እንጂ የተናጠል ስራ ውጤት ሊያመጣ አይችልም። በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚሰሩና የሚሰበሰቡ ጥናቶችም ወደ ዋናው ሀገር አቀፍ የመከላከል፣የመቆጣጠርና ማጥፋት ላይ ያላቸው አንድምታ ላይ ትንታኔዎች ይሰራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ወባን ለማከምና ለመመርመር ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብአቶች አሉ። ለምርመራ ፈጣን የመመርመሪያ መሳሪያ/RDT/ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህን እ.ኤ.አ ከ2004 ጀምሮ ስራ ላይ መዋል ጀምሯል። ይህ መሳሪያ በማኅበረሰብ ደረጃ በተለይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንዲመረምሩና ወዲያው ደግሞ አስፈላጊውን መድሃኒት ይዘው እንዲያክሙ ያገዘ ነው። በዚህ ስራም ብዙ ለውጥ መጥቷል።

ሕብረተሰቡ የወባ ምልክቶች ከታዩት በኋላ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ርቆ መሄድ የለበትም። በማኅበረሰብ ደረጃ የወባ ሕክምና አገልግሎቱን በማግኘቱ በርካታ ሰዎች የወባ በሽታ የከፋ የጤና ጉዳት ሳያስከትልባቸው ታክመው እንዲድኑ አስችሏቸዋል። ይህ ስራ አሁንም ቀጥሏል። ወባን ለመመርመር የሚያስችለው መሳሪያም በየግዜው ይፈተሻል። በዚሁ መሰረት አንዳንድ ማስተካከያ በሚያስፈልጉ ቦታዎች ላይ የተሰሩ ስራዎች አሉ። ከዚህ ባለፈ ሌላኛው ወባን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውለው መድሃኒት ሲሆን በመድሃኒት ፍቱህነት ላይ በየሁለት ዓመቱ ፍተሻና ጥናት ይደረጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ «ሴንትናል ሳይቶች» አሉ። ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ጣቢያዎችን በመምረጥ ጥናት ይደረጋል። ይህም ሳይቆራረጥ እየተሰራ ያለና ጥሩ ግብአት እየሰጠ የሚገኝም ነው። ጥቅም ላይ የሚውለውን መድሃኒት ብቻ ሳይሆን ነገ ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መጠባበቂያ መድሃኒቶችንም ማስቀመጥ ያስፈልጋል። እደነዚህ አይነት ስራዎችም በጥናት ተደግፈው እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ትልቁና ቁልፉ ነገር በባለፈው ዓመት የወባ የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ተፈትሾ የመጠቀሚያ ግዜው ገና ሳይጠናቀቅ የመከለስ ስራ ተሰርቷል። የኢትዮጵያ የወባ ቁጥጥር ስራ ምን እንደሚመስልና መታየት ያለበት ቦታ ካለ እንዲታይና እንዲሻሻል ተደርጓል። በዚህ መሰረት አዲሱ በጀት ዓመት ሲጀመር ግብአቶች፣ ግዢዎች ይህን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲሆኑ ተደርጓል። የአየር ንብረት ለውጥ፣ ግጭቶችና የተፈጥሮ አደጋዎች አገልግሎትን ሊያቋርጡ ይችላሉ። ይህ ችግር ደግሞ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ዓለምን የሚያሳስብ ነው።

ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው የወባ ሕክምናና ሌሎችንም የጤና አገልግሎቶችን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በቅርበት መስራት እንደሚገባ በተለያዩ ጉባኤዎች ላይ በመሳተፍ ግንዛቤ ለመውሰድ ተችሏል። የአየር ንብረት ለውጥ፣ ግጭቶችና የተፈጥሮ አደጋዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወባ መከላከል ስራ በጤና ሚኒስቴርና በሕክምና ተቋማት ብቻ የሚሰራ ስራ አይደለም። የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና ርብርብ ይጠይቃል። ከግለሰብ ጀምሮ በቤት ውስጥ የምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች ለወባ መከላከል ስራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። የታቆረ ውሃን ማፍሰስ ብቻ ሳይሆን በባልዲ ውስጥ ሁለትና ሶስት ቀን የተተወ ውሃ ለወባ መፈልፈል ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል ከቤት ውስጥ ጀምሮ የጥንቃቄ ስራዎችን ማከናወን ይገባል።

ስለዚህ በማኅበረሰብና በግለሰብ ደረጃ የሚሰሩ ስራዎች ለወባ መከላከል ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳላቸው በመረዳት እዚህ ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ የወባ ስርጭት ከፍ ባለባቸው አካባቢዎች የአልጋ አጎበሮች ለሌላ ስራ ሲውሉ ይታያል። ከዚህ አንፃር በኅብረተሰቡ ዘንድ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ ተከታታይነት ያለው ስራ መስራት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የሚዲያ አካላት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። ለወባ መከላከል ስራ የሚውሉ የአልጋ አጎበሮች፣ ኬሚካሎችና መድሃኒቶች በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እንደመሆናቸው ኅብረተሰቡ በአግባቡ እንዲጠቀምባቸው ሰፊና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ስራዎችን መስራት የግድ ይላል።

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ጌታቸው ቶሌራ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ ኢንስቲትዩቱ የጤና ሚኒስቴር ቴክኒካል አማካሪ ነው። በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ካሉ ተቋማት ውስጥም አንዱ ነው። በመደበኛነት የወባ በሽታን ክትትልና ሕክምና የሚያደርገው ጤና ሚኒስቴር ቢሆንም ቁጥሩ ከፍ ሲል ወይም ወደ ወረርሽኝ ደረጃ ከፍ ሲል በቀጥታ ስራውን ወስዶ የሚሰራው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ነው። ስለዚህ በተለየ መልኩ ለዚሁ ስራ የተቋቋመ ተቋም ነው።

ኢንስቲትዩቱ ከወባ አንፃር በኅብረተሰብ ጤና አደጋ ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል። የምርምር፣ የላብራቶሪና የብሄራዊ ዳታ አስተዳደር ስራዎችን ያከናውናል። በኅብረተሰብ ጤና አደጋ በተለይ በሽታዎች ከሚፈለገው ቁጥር ወይም ደግሞ ከመደበኛ ሕመሞች በላይ ሲሆን ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን የሚሰራ ስራ ነው። የወባ ስርጭትም በአሁኑ ግዜ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ በመደበኛ ስራ የሚመለስ አይደለም። በተለይ ደግሞ የክልል ጤና ቢሮዎችን፣ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶችን ሁሉንም እስከ ቀበሌ ድረስ በተዋረድ አብሮ መስራትን ይጠይቃል። የአደጋ ምላሽ ማእከሉም የሚሳተፍበት ነው። ከአደጋ ምላሽ ማእከሉ ከሚሰራቸው ዋነኛ ስራዎች ውስጥ ደግሞ አንዱ የተግባቦት ስራ ነው።

ምክንያቱም ወባን ልዩ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ ብዙ አካላትን የሚነካና የሚያሳትፍ መሆኑ ነው። ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያዎቹና አስፈላጊዎቹ ሰዎች ወይም ማኅበረሰቡ ናቸው። ለምሳሌ ጤና ሚኒስቴር የወባ መከላከያ ኬሚካሎችን ታች ወርዶ ሊረጭ ይችላል። ነገር ግን ግድግዳዎች መልሰው ቀለም ወይም ጭቃ አልያም እበት የሚለቀለቁ ከሆነ በታሰበው ልክ የወባ በሽታን መከላከል አይቻልም።

ስለዚህ ማኅበረሰቡ የወባ በሽታ መከላከያዎችን አውቆ ራሱን ከበሽታው እንዲከላከል በየግዜው የግንዛቤ ማስጨበጫና የተግባቦት ስራ መስራት ያስፈልጋል። በተመሳሳይ በአካባቢው የታቆሩ ውሃዎችን ማፍሰስ ልምድ ኖሮት ይህንን ተግባር በየግዜው ያለመሰልቸት እንዲተገብርና ለወባ ሕክምና የሚውሉ መድሃኒቶችን በአግባቡ እንዲጠቀም ያለመታከት የግንዛቤ ስራዎችን መስራት ተገቢ ይሆናል። ማኅበረሰቡ በወባ መከላከል ዙሪያ እውቀት እንዲኖረውን ያን እውቀት ሁልግዜ ተግባባዊ እንዲያደርግ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

በዋናነት ደግሞ ማኅበረሰቡ በወባ መከላከል ዙሪያ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ተመሳሳይ ስራዎችን መስራት ይገባል። በማኅበረሰቡ ላይ የሚሰራው የግንዛቤና የባህሪ ለውጥ ስራ ደግሞ ቀጣይነትና ድግግሞሽ ያለው መሆን አለበት። የባህሪ ለውጥ ስራው የድግግሞሽ ስራ ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነትም ይጠይቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ አንዱ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ ሲባል ታዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የአየር ንብረት ለውጥም ነው የሚታየው። ስለዚህ ዓለም አቀፋዊ የአየር ንብረት ለውጥን ቀድሞ በመማንበብ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ከዚህ ባሻገር አመራሩ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ በተግባቦት መስራት አለበት። በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ችግሩ የሰፋ ሊሆን ይችላል። አመራሩም በሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን ሊያደርግ ይችላል። ማኅበረሰቡ እንደተዘናጋ ሁሉ አመራሩም ሊዘናጋ ይችላል። ስለዚህ ወባ ክረምት ብቻ ተጠብቆ የሚሰራ ስራ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ በተከታታይ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በዚህ ስራ ውስጥ ጥናቶች፣ የአመራር ስራዎች፣ ሕክምና፣ ላብራቶሪ፣ የመድሃኒት አቅርቦት ይካተታሉ። ስለዚህ ወባን የመከላከል ስራ የአንድ አካል ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ነው።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ሕሙማንን የመፈወስ የዕለት ተዕለት ሩጫ

ፍሬሕይወት አወቀ

ኢትዮጵያውያን ሳይማሩ ልጆቻቸውን በማስተማር ይታወቃሉ። ብዙ ውጣውረዶችን አልፈው፤ ብዙም ዋጋ ከፍለው ልጅ ከእኔ የተሻለ መሆን አለበት ብለው ልጃቸውን ያስተማራሉ፤ እያስተማሩም ይገኛሉ። ልጆቻቸውም በየመስኩ ተሰማርተው ከራሳቸውና ከቤተሰባቸውም አልፈው ለአገርና ለወገን አለኝታ ሆነዋል። የዕለቱ እንግዳችንም ከዚሁ ማኅበረሰብ እንደመገኘታቸው በተማሩበት ሙያ ሳይማር ያስተማራቸውን ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብና አገርን በሕክምናው ዘርፍ እያገለገሉ ይገኛሉ።

እንግዳችን ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ከተማ መሀል መርካቶ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ዑመር ሰመተር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ አዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል፤ የከፍተኛ ትምህርታቸውንም በሕክምና ዘርፍ በቀድሞ አጠራሩ በጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስቲትዩት ተምረዋል። ሕክምናን ተምረው ሕክምና ውስጥ የኖሩት የዕለቱ እንግዳችን ዶክተር መሀመድ ኑሪ ዑስማን የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካን ጨምሮ የሜዲቴክ ኢትዮጵያ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ሰብሳቢ እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው።

ሙሉ ሕይወታቸውን በትምህርትና በሥራ ያሳለፉት ዶክተር መሀመድ፤ በተለየ ሁኔታ ለሕክምና ሥራቸው ልዩ ፍቅር አላቸው። ይህ ለምን ሆነ ካላችሁ፤ ሕክምና መማራቸው አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ገና ከጅምሩ የአንደኛ ዓመት ተማሪ እያሉ ወላጅ እናታቸውን በመድሃኒት እጦት ማጣታቸው ነው። በወቅቱ ወላጅ እናታቸው የሚያስፈልጋቸው መድሃኒት በአገር ውስጥ አልነበረም። አቅም ኖሮ ከውጭ መግዛት አልተቻለምና እናት ወደማይቀረው ዓለም ተሰናብተዋል። ይህ ቁጭት የገባቸው ዶክተር መሀመድ፤ ንግድ ውስጥ በመግባት በተለይም ለማኅበረሰቡ አስፈላጊ የሆኑ የመድሃኒት አይነቶችን በማቅረብ ዜጎችን ለመታደግ ሲነሱ በልበ ሙሉነት ነበር።

ማኅበረሰቡን ይጠቅማል ለአገር ይበጃል ያሉትን በሙሉ ያለ ስስት የሚያካፍሉት ዶክተር መሀመድ፤ ተማሪ እያሉ ጀምሮ ጎበዝና ታታሪ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ይህም በጥረታቸው ዛሬ ካሰቡት እንዲደርሱ አስችሏቸዋል። የሕክምና ትምህርት ለመማር ጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስቲትዩትን የተቀላቀሉት ገና በ16 ዓመት ዕድሜያቸው ነበር። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያትም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጎበዝ ተማሪ በመሆናቸው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ ከክፍል ወደ ክፍል የመዘዋወር ዕድል አግኝተዋል።

በወቅቱ ከፍተኛ ውጤት በማምጣትም የሕክምና ትምህርት በመማር አራት ነጥብ አምጥተው አጠናቅቀዋል። ይህ ውጤትም ጎበዝና ታታሪ በመሆናቸው የተቀዳጁት ድል እንጂ በዘፈቀደ የተገኘ ዕድል አይደለም። የሕክምና ትምህርታቸውን ለሰባት ተከታታይ ዓመታት ተከታትለው በከፍተኛ ማዕረግ ሜዲካል ዶክተር የሆኑት ዶክተር መሀመድ፤ ባስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት መሰረት በኢንስቲትዩቱ የማስተማር ወርቃማ ዕድል አግኝተዋል።

ይሁን እንጂ የቅጥር ደብዳቤያቸውን በተቀበሉ ማግስት ወደ አዲስ አበባ ያቀኑት ዶክተር መሀመድ፣ ተወልደው ያደጉባት፣ የተማሩባትና ክፉ ደጉን የለዩባት አዲስ አበባ በዋዛ ልትለቃቸው አልፈቀደችም። እናም ወደ ኢንስቲትዩቱ ሳይመለሱ ንግድ ውስጥ ገቡ። ጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስቲትዩት መምህርነትን ባይቀበሉም ዛሬ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ዳይሬክተር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

"ንግድ ውስጥ እንድገባ ምክንያት የሆኑኝ አብሮ አደግ ጓደኞቼ ናቸው" የሚሉት ዶክተር መሀመድ፤ ከትምህርት ሲመለሱ ዩኒቨርሲቲ መግባት ያልቻሉ ጓደኞቻቸው ሀብታም ነጋዴ ሆነው ነው አገኟቸው። ይህን ጊዜ ሕይወታቸውን መለወጥና ሳይማር ያስተማራቸውን ቤተሰብ ማገዝ የሚችሉት በመምህርነት ደመወዝ ሳይሆን ነጋዴ መሆን ሲችሉ እንደሆነ በማመን ጓደኞቻቸውን በዕውቀት ማገዝ ጀመሩ። በአንድ አጋጣሚ ዱባይ በማቅናት በሙያቸው መሥራት የሚያስችሏቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ሮያል ፋርማሲን ከፈቱ።

"ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል" እንዲሉ የንግድ ሥራቸውን በዕውቀት በመምራት ንግዳቸውን ማቀላጠፍ ያዙ። "ሮያል ፋርማሲን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ መክፈቴ ውጤታማ አድርጎኛል" ያሉት ዶክተር መሀመድ፤ ሥራውን በዕውቀት መምራት በመቻላቸው ታዋቂነትን በማትረፍ ከአስር ዓመት በላይ ገበያ ውስጥ ቆይተዋል። በወቅቱ የመድሃኒት እጥረት በከተማ ውስጥ በመኖሩ አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን ከአስመጪዎች በመረከብ ፋርማሲው 24 ሰዓት ይሰራ ስለነበረ ምሽት ላይ ራሳቸው ይሸጡ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ሮያል ፋርማሲ አሁን ለደረሱበት ደረጃ ትልቅ መሰረት



ዶክተር መሀመድ ኑሪ ዑስማን

የጣለ ስለመሆኑ አጫውተውናል። "በትምህርት ካገኘሁት ዕውቀት በተጨማሪ ሮያል ፋርማሲ ውስጥ በመሥራቴ እና ከማሕበረሰቡ ጋር በቀጥታ በመገናኘቴ ያካበትኩት ልምድ ዛሬ ለደረስኩበት ደረጃ ጠንካራ መሰረት ጥሎልኝ አልፏል" በማለት ተናግረዋል። የሰሩትን ገንዘብ እንዲሁም ያገኙትን ዕውቅና ደምረው በሕክምናው ዘርፍ ሰፋፊ ሥራዎችን በመሥራት መድሃኒት አስመጪ የሆኑት ዶክተር መሀመድ፤ በወቅቱ ትልቅ የቢዝነስ ጉብኝት አግኝተዋል።

ጉብኝቱ አጠቃላይ የቢዝነስ ጉብኝት ሲሆን፤ በሕክምናው ዘርፍ ብቸኛ ተሳታፊ በመሆን ከአገር አገር በመጓዝ ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበዋል። ያኔ እንደዛሬው ዘመኑ በቴክኖሎጂ አልደረጀምና ሙሉ አቅማቸውን በመጠቀም ከየአገሩ የሰበሰቧቸውን ከ100 ኪሎ ግራም በላይ ካታሎጎችን በፖስታ ወደ አገር ቤት ልከዋል። በዚህም መድሃኒት አስመጪ የመሆን ዋንኛ ዓላማቸውን አሳክተዋል።

"ዕውቀትን መሰረት በማድረግና ቁጭት በወለደው ከፍተኛ መነሳሳት የተጀመረው መድሃኒት የማስመጣት ሥራ ፍሬው ያማረ ነው" ያሉት ዶክተር መሀመድ፤ ከፋርማሲው ጎን ለጎን ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ሜዲቴክ ኢትዮጵያ መድሃኒት አስመጪና አከፋፋይ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን ማቋቋም ችለዋል። ሜዲቴክ ኢትዮጵያ የተለያዩ መድሃኒቶችን ጨምሮ አጠቃላይ ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ይታወቃል። ሜዲቴክ ወደ ሥራ ሲገባ ነብስ አድን መድሃኒት ወይም በተለምዶ ግሉኮስ በአገሪቱ እጥረት የነበረ በመሆኑ በስፋት በማስገባት ለግልና ለመንግሥት ተቋማት በማቅረብ ፍላጎቱን መሙላት ችሏል።

በዕውቀትና ከልብ በመነጨ ፍላጎት የሚመራ ቢዝነስ አዋጭና ተመራጭ ነው የሚሉት ዶክተር መሀመድ፤ የሰው ኃይል ወሳኝ እንደሆነ በማመን አሉ የተባሉ ባለሙያዎችን በማፈላለግ እየቀጠሩ ሜዲቴክ ኢትዮጵያን በአጭር ጊዜ ከፍ ማድረግ ችለዋል። ሜዲቴክ ኢትዮጵያ ከጉልኮስ በተጨማሪ ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በመከላከል ሥራ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ነበረው። በሽታው በተስፋፋበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የጸረ-ኤች. አይ. ቪ መድሃኒትን ሜዲቴክ ኢትዮጵያ ከመንግሥት ጋር በመሆን ለአራት ተከታታይ ዓመታት በብቸኝነት ሲያስመጣ ቆይቷል። በወቅቱ መድሃኒቱን ሳያገኙ ብዙዎች ቢያልፉም በርካቶችን በመታደግ ኢትዮጵያ ኤች.አይ.ቪ አስከፊ ከሆነባቸው አገራት ዝርዝር እንድትወጣ የበኩላቸውን ጉልህ አበርክቶ እንዳደረጉ ይጠቅሳሉ።

ሕክምና ተምረው ሕይወታቸውን ሙሉ ለሕክምና የሰጡት ዶክተር መሀመድ፤ የተለያዩ መድሃቶችን ወደ አገር ቤት በማስገባት በዘርፉ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ መድሃኒት አስመጪዎች ብዙ መድሃኒቶችን በማስመዝገብና በማስመጣት ቀዳሚ በመሆን በአሁኑ ወቅት 550 አይነት መድሃኒቶችን ማስመጣት ችለዋል። ይህም በኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን የተረጋገጠ መሆኑን ይናገራሉ።

ሙያዊ ዕውቀትን መሰረት አድርገው መድሃኒት በማስመጣት ቀዳሚ የሆኑት ዶክተር መሀመድ፤ በግል ካቋቋሙት ሜዲቴክ ኢትዮጵያ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ በመድሃኒት አቅርቦት ትልቅ ስም ያለውና ስድስት አስርት ዓመታትን ያስቆጠረውን አንጋፋውን የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካን ጭምር ከመንግሥት ገዝተው የኢንቨስትመንታቸው አካል አድርገውታል።

ስለመድሃኒት ጠንቅቀው የሚያውቁት ዶክተር መሀመድ፤ የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካንም በልኩ ያውቁት ነበርና ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ጨረታውን አሸንፈው ፋብሪካውን የግላቸው ማድረግ ችለዋል። በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ መድሃኒቶችን ወደ አገር ውስጥ ከማስመጣት ባለፈ በአገር ውስጥ በማምረት ጭምር ማኅበረሰቡ ጋር በስፋት መድረስ ችለዋል።

የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካን ሲረከቡ ፋብሪካው ያመርታቸው የነበሩ መድሃኒቶችን በማስቀጠል እንዲሁም ተጨማሪና አገሪቷ ውስጥ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን በመለየት በአዲስ መልክ ወደ ሥራ ገብተዋል። የመድሃኒት አይነቶችን ከማስፋት ባለፈም ዘመናዊ ማሽኖችን በማስመጣት ስራውን ማስፋት የቻሉት ዶክተር መሀመድ፤ "ከፍትፍቱ ፊቱ" እንዲሉ የመድሃኒት ማሸጊያዎቹን ጭምር ባማረና ሳቢ በሆነ አቀራረብ መቀየር ችለዋል። መድሃኒት እንደማንኛውም ሸቀጥ እንዳልሆነና ትልቅ ጥንቃቄ እንደሚፈልግም አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለመድሃኒት ፋብሪካው ማስፋፊያ በማድረግ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሰሩ ሲሆን፤ ከአገር ውስጥ ባለፈም 25 በመቶ በአገር ውስጥ የሚመረቱ መድሃኒቶችን ወደ ውጭ በመላክ የአገሪቷን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ ትልቅ ራዕይ ሰንቀዋል። ለዚህም በቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርክ የማስፋፊያ ቦታ አግኝተዋል። በኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካ ብቻ 125 የሚደርሱ የመድሃኒት አይነቶች የሚመረቱ ሲሆን፤ በቀጣይም በማስፋፊያው 200 የሚደርሱ ይሆናል። ፋብሪካዎቹ የተለያዩ መድሃኒቶችን እያመረቱ ይገኛሉ። ለአብነትም ሽሮፕ፣ ክኒን፣ ካፕሱሎች፣ ቅባት ነክ የቆዳ መድሃኒቶች፣ መርፌዎች፣ ሕይወት አድን ንጥረ መድሃኒቶችና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።

የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ በማስመጣት በአገር ውስጥ ቀምመው የሚያመርቷቸውን መድሃኒቶች በአገር ውስጥ ለሚገኙ መድሃኒት አስመጪና አከፋፋዮች እንዲሁም ለመንግሥት በማቅረብ ማኅበረሰቡ ጋር ይደርሳሉ። ሜዲቴክ ኢትዮጵያ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን የተለያዩ መድሃኒቶች ለባለሙያዎች በማስተዋወቅ ማኅበረሰቡ ጋር መድረስ እንዲችል ያደርጋሉ። ይሁንና የ60 ዓመት ታሪክ ያለው የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካ የሚያመርታቸው መድሃኒቶች ባላቸው ጥራት በስፋት የሚታወቁና ከውጭው ይልቅ እጅግ ተፈላጊ እንደሆኑ የተናገሩት ዶክተር መሀመድ፤ በዚህም ከፍተኛ ኩራት ይሰማቸዋል።

መድሃኒት ሲመረት በከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሆነና ከፍተኛ ወጪ እንደሚጠይቅ የሚናገሩት ዶክተር መሀመድ፤ መድሃኒት ከሌሎች ምርቶች ጋር ሲነጻጸር በብዙ እጥፍ የሚከብድ ነው ይላሉ። ምክንያቱም 99 በመቶ ያህሉ ጥሬ ዕቃ ከውጭ አገር የሚመጣ በመሆኑ ዘርፉን ከባድ ያደርገዋል። ከአገር ውስጥ የሚጠቀሙት ውሃ ብቻ ሲሆን፤ ውሃውም ቢሆን ታክሞና የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ መድሃኒት መስሪያ የሚሆን ነው።

በአገሪቱ ከነዳጅ ቀጥሎ መድሃኒት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቅ እንደመሆኑ እሳቸውም ይህን ችግር ለማቃለል ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። በአሁኑ ወቅትም መድሃኒት ለማምረት የሚያስችሉና መሰረታዊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ለማምረት እየሠሩ ሲሆን፤ እስከዚያው ግን ጥሬ ዕቃውን ከውጭ ማስመጣት የግድ ነው ብለዋል።

መንግሥት አሁን ላይ ለአምራች ኢንዱስትሪው የሰጠው ትኩረት የሚበረታታ እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር መሀመድ፤ ይሁንና በፋርማሲቲዩካል ዘርፍ እየተሰጠ ያለው ማበረታቻ ግን መሻሻል እንዳለበት ገልጸዋል። በተለይም የውጭ ምንዛሪ እጥረት ከፍተኛ ችግር በመሆኑ መንግሥት ለዘርፉ እየሰጠ ያለውን ትኩረት ይበልጥ ማሻሻልና ቅድሚያ በመስጠት ተደራሽነትን ማስፋት ይጠበቅበታል ይላሉ። መንግሥት ቦታ ከመስጠት ጀምሮ አስፈላጊ የሆኑ ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት እንዲቻል በርካታ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል ሲሉ ጠቅሰው፤ ይሁንና ሕጎችን ተፈጻሚ ከማድረግ አንጻር አፈጻጸም ላይ ክፍተት ይታያልና ይህ ሊታረም ይገባል ባይ ናቸው።

በሚሠሩት ሥራ ውጤት ማስመዝገብ ተቀዳሚ ዓላማቸው የሆነው ዶክተር መሀመድ፤ «ውጤት ማስመዝገብ የሚቻለው ተነሳሽነት ያለውና የተነቃቃ ሠራተኛ ሲኖር ነው» ይላሉ። ለዚህም የሰው ኃይልን በማብቃት ረገድ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ። የኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካን በግላቸው ለማስተዳደር በተረከቡበት ወቅትም ሰራተኛ ሳይቀንሱ የሁሉንም የሠራተኞች ደመወዝ ከመቶ እጅ በላይ አሻሽለዋል። ይህም ሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት ኖራቸው እንዲሰሩ ከማድረግ ባለፈ ውጤት ማስመዝገብ አስችሏቸዋል።

የሰው ልጆች ከሕመማቸው የሚፈውሳቸውን መድሃኒት ሲያስመጡ፣ ሲያከፋፍሉና ሲያመርቱ የኖሩት ዶክተር መሀመድ፤ ሕክምና ተምረው ሕይወታቸውን ሙሉ ከሕክምናው ዘርፍ የተለዩ አይደሉም። ከሕክምናው በተጨማሪም የተለያዩ ኩባንያዎችን ያስተዳድራሉ። ከእነዚህም መካከል ከኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካ፣ ሜዲቴክ ኢትዮጵያ እና በጂቪ ጁልፋ ኢትዮጵያ (መድሃኒት አምራች) በተጨማሪ ቆንጆ ውሃ፣ እናት ኢንጂነሪንግ፣ ኤክሰለንስ ኮንስትራክሽን እና ሪልስቴት ይጠቀሳሉ።

እነዚህ እህት ኩባንያዎች አጠቃላይ ከሁለት ሺ ለሚልቁ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአገር አለኝታነታቸውን አስመስክረዋል። በቀጣይም በርካታ የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ ያላቸው ዶክተር ሙሀመድ፤ የነብስ ጥሪያቸው ከሆነው የሕክምና ዘርፍ ውጭ የመስራት ብዙ ፍላጎት የላቸውም። ነገር ግን የሚሠሯቸው ተጓዳኝ ሥራዎች በሙሉ የሕክምናው ዘርፍ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጪ እንዲሚደግፉላቸው አጫውተውናል።

ለሰው መኖር የሕይወት ፍልስፍናቸው የሆነው ዶክተር ሙሀመድ፤ "የኢትዮጵያዊነት ዋና መገለጫ መረዳዳት ነው" ይላሉ። ያለ ስስት የተሰጣቸው ጸጋ መልካምነት በመሆኑ ለተቸገሩ በመድረስ ለብዙዎች የጓዳቸው ሙላት ሆነዋል። በግልም ሆነ በድርጅት ስም በሚሰሩት በጎ ሥራ እንዲሁም ባስመዘገቡት ውጤት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከ100 በላይ የዕውቅና ሰርተፍኬቶችን አግኝተዋል።

ዶክተር መሀመድ፤ ግብራቸውን በወቅቱና በታማኝነት ከመክፈል ባለፈ መንግሥታዊ ለሆኑ ማንኛውም ጥሪዎች በቀዳሚነት ምላሽ እንደሚሰጡ ይናገራሉ። ከመደበኛ ሥራቸው ባልተናነሰ ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ጉልህ አበርክቶ እንዳላቸው ቢገልጹም፣ "ቀኝ እጅህ ሲሰጥ ግራህ አይመልከት" በሚለው አስተምህሮ በዝርዝር መናገር አልፈቀዱም። ይሁንና ከብዙ በጥቂቱ በደቡብ ዞን ወራቤ አካባቢ በ13 ዞኖች ንጹህ የመጠጥ ውሃ አውጥተዋል፤ ትምህርት ቤቶች ገንብተዋል፤ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት 500 ተማሪዎችን በቋሚነት ይመግባሉ። በተጨማሪም ከኩባንያዎቻቸው ዓመታዊ ትርፍ ሶስት በመቶውን በየዓመቱ ለበጎ አድራጊ ድርጅቶች ተደራሽ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

# ተናጋሪው ዶሴ

# አባት ወይስ ጠላት?

አስመረት ብስራት



‹‹አባት›› የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የአንድ ነገር ምንጭ ወይም ጀማሪ የሚል ትርጓሜን ይይዛል:: አባት ምንጭ ቢሆንም አባትነት እምነት እናትነት እውነት ይባላል:: ልጅ ሲወለድለት አባት መሆኑን አምኖ ተቀብሎ ለልጆቹ ጥላ ሆኖ ከመከራ ከልሎ ያሳርፋል:: ልጆቹ ማደጋቸውን በጉጉት እየተመለከተ ነጋቸውን በአይነ ሕሊናው ይቃኛል:: በእርጅናው ደግሞ በፀሎት የልጆቹን ቀና መንገድ ሲመኝ የሚኖር ታላቅ ሃብት ነው አባትነት።

ታዲያ ይህ አባትነት የግድ በስጋ ከመዋለድ ጋር ብቻ የተሳሰረ አይደለም:: ብዙዎች በስጋ ያልወለዷቸውን ልጆች እንደአብራካቸው ክፋይ አባት ሆነው አሳድገው ለቁም ነገር አድርሰዋል:: ጠባቂ መደገፊያ ማምለጫ በመሆን የአባትነት ግዴታን ተወጥተዋል:: በተቃራኒው ደግሞ እንደአባት ታምኖ በስጋ ወልዶም ሆነ ሳይወልድ አባትም ሆነ የእንጀራ አባት ሆኖ እንደአባት ግዴታውን የማይወጣም ሞልቷል:: የአባትነት ግዴታውን መወጣት ሲገባው በተቃራኒው ጠባቂ ሳይሆን እራሱ አራጅ ሆኖ ሲገኝ ምን ይባላል? ይህን የአባትነት ምስጥር ያፈረሰ ትስስሩን ባልተገባ መንገድ የበጠሰ አባት ሲገኝ አባት ወይስ ጠላት ያሰኛል:: ለዛሬ ተናጋሪ ዶሴ አምዳችን የ8 ዓመት የእንጀራ ልጁን አስገድዶ የደፈረው ግለሰብ ታሪክ ልናካፍላችሁ ወደድን።

ይህን የወንጀል ታሪክ ህብረተሰቡን በሚያስተምር መልኩ ይቅረብ ዘንድ የፈቀዱልንን የአዲስ አበባ ፖሊስ መዝገብ ቤት ሰራተኞችን እያመሰገንን ታሪኩን በዚህ መልኩ አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

### እናትና ልጅ

ከተወለደችባት ቀዬ የወጣችው ገና በአፍላ የወጣትነት ዘመኗ ነበር። ያኔ ወደ አዲስ አበባ የመጣችው ሥርታ ከድህነት ለማመለጥ አቅዳ ነበር። ከድህነት አመልጥበታለሁ ያለችበት ሥራ የልጅነት ልጇን እስኪ ያሳቅፋት ድረስ ያገኘቻትን ገንዘብ እየቆጠበች ሕይወቷ ለማሻሻል ቀን እየጠበቀች በአገኘችው አጋጣሚ ትታር ነበር።

በአንዲት ክፉ ቀን በሰራተኝነት የተቀጠረችበት ቤት የሚኖር የዘመድ ልጅ በክፉ አይኑ ተመለከታት። በወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበረው ወጣት የአስራ አምስት ዓመቷ የገጠር ጉብል ላይ አይኑን ከማሳረፍ አልፎ፤ አብሯት ሊተኛ ተመኛት:: ምኞቱ አብሮ ለመኖር እና የትዳር ጓደኛው ለማድረግ ሳይሆን ጊዜያዊ ስሜቱን ከማርካት ያለፈ አልነበረም:: ከእለታት በአንዱ ቀን ለዓመታዊ ክብረ በአል የቤቱ ሰው በሙሉ ተለቃቅሞ ለንግስ ጉዞ ሄደ። ያኔ እሷና የዘመድ ልጅ ተብዬው ብቻቸውን ቤት ቀሩ። ይህች የዋህ የገጠር ልጅ እንደለመደችው ስራዋን ሰርታ ለልጁ እራት አቅርባ ወደ መኝታዋ ሄደች። ከዛም መአድ ቤት ውስጥ ፍራሽ አንጥፋ ጋደም ከማለቷ እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ አለ።

ድብን ያለ እንቅልፍ ውስጥ መግባቷን የተመለከተው ወጣትም ቀድሞ አይኑ ያረፈባትን ልጅ ተመኘ። ወጣቱ እንዳትነቃነቅ አድርጎ ካሰራት በኋላ ልጅቱ ከእንቅልፏ ነቃች:: እኩይ ተግባሩን ለመፈፀም አቅዶ የነበረው ወጣት ቀድሞ በተዘጋጀው መንገድ እጇን አስሮ አፏን በጨርቅ ጠቅጥቆ ግንኙነት ፈፀመባት።

ያላሰበችው ነገር የደረሰባት ወጣት ቤታቸውን አደራ ሰጥተዋት የሄዱት ሰዎች ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ ጨርቋን ማቄን ሳትል ማልዳ ተነስታ እንደ ወፍ በራ ጠፋች። ጠፍታ ሕክምና ወስዳ እራሷን አጠንክራ ወደ ሥራዋ ለመመለስ ስታስብ ነፍሰ ጡር መሆኗን ሰማች። ይህንን ስታውቅ ሰማይ ተደፋባት:: ሥራ ሠርታ ራሷን የመቀየር ዕቅዷ ተበላሸ:: ነፍሰ ጡር ሆና የሚቀጥራት ባለመኖሩ ዘመድ ጋር ተጠግታ ለመኖር ተገደደች:: ዘመድ ቤት እየሰራች እና እየበላች ልጅ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ:: በሰላም ሴት ልጅ ተገላገለች::

ልጅ ከወለደች በኋላ ሕይወት ቀላል አልሆነችም:: በብዙ መከራ ውስጥ አለፈች:: በመከራ ውስጥ ስታልፍ ለጇን ለማንም ሳትሰጥ ጉያዋ ውስጥ ሸሽጋ እና አዝላ በየሰው ቤቱ እየሰራች እስከ አምስት ዓመት እድሜዋ ድረስ ብቻዋን አሳደገቻት። ከዛ በኋላ ግን ኑሮ እየከበዳ መጣ:: የልጇም ፍላጎት እየጨመረ ሄደ:: በዚህ መሃል ልጅ ቢኖርሽም አገባሻለሁ፤ የሕይወትን ፈተና አብረን እንጋፈጥ ብሎ ደጋግሞ ለሚጠይቃት ሠው ምላሽ ሰጠች:: ጥያቄውን ተቀብላ አብራ ለመኖር መፍቀዷን አሳወቀች።

ትዳር ፈላጊው ሙዓዝ ከፈለኝ ባሳየችው ፈቃደኝነት ተደሰተ:: የሞቀ የደመቀ ትዳር መስርተው ኑሮን ማጣጣም ጀመሩ:: የትዳር አጋሯ ልጇን እንደ ልጁ እየተንከባከበ ማሳደጉ እጅግ አስደሰታት። አዲሱ ባልና ሕፃኗን አብረው ለተመለከታቸው በስጋ አባትና ልጅ እንጂ፤ የእንጀራ አባትና ልጅ አይመስሉም ነበር። ያበላታል፣ ያጠጣታል፣ ያለብሳታል፣ ወደ ትምህርት ቤት ያደርሳታል:: ብቻ ማንኛውም ወላጅ ለልጁ ሊያደርግ የሚገባውን እንክብካቤ በሙሉ ያደርግላታል::

### ያልታሰበው ጥቃት

ባሏ ለልጇ መልካም አባት መሆኑ ያስደሰታት ሴት ሙሉ ትኩረቷን ወደ ስራ አድርጋ ለእድገታቸው ደፋ ቀና ማለቷን ቀጠለች። ባልም በትርፍ ጊዜው በሙሉ ልጅቷን መንከባከብ ስራው ነበር። እንደ አባት አስፈላጊውን ነገር በሙሉ እያሟላለት ያስተምራት ጀመር። ልጅቷ የቅድመ መደበኛ ትምህርቷን አጠናቃ አንደኛ ክፍል ገባች። በእንክብካቤ በመያዟ ቁመቷ አድጎ ቆንጆ ልጅ ሆነች።

አባዬ የምትለው አባትም የልጅቷ ቁመት ሲያድግ እድሜዋን ረስቶ ክፉ ሃሳብ በአይነ ሕሊናው ይመላለስ ጀመር። የሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ልጅም በትምህርቷ ጎበዝ ቀልጣፋና ታዛዥ ነበረች። እናት የራስዋን ቁስል ዋጥ አድርጋ ልጇን ለማሳደግ አቅም የሰጣትን ባለቤቷን እጅግ ከማመኗ የተነሳ ልጇ ላይ እንኳን ጥቃት ቁንጥጫ ያሳርፍባታል ብላ አታስብም ነበር።

ነገር ግን ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው እናቷ የቀመሰችውን ፅዋ ልጅቷም ባመነችው ሰው እንድትቀምስ ተፈረደባት። አባትየው ሙዓዝ ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 6፡00 ስዓት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው ካራ ጋቢሳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤት ውስጥ አባትና ልጅ እንደ ሁልጊዜው ተቀምጠው እየተጫወቱ ነበር።

ይህች የ8 ዓመት ዕድሜ ያላትንና በራሱ ቁጥጥር ስር የሚያሳድጋትን የእንጀራ ልጁን ከትምህርት ቤት ስትመጣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ተቀምጦ ያገኛትውን አባቷን ስማ አጠገቡ ተዝናንታ ተቀምጣ ነበር። የእናቷን አለመኖር የተመለከተው ሙአዝ ከፈለኝ የልጅቷን አፍ አፍኖ አስገድዶ ደፈራት። አባት ለድጋፍ ለእቅፍ እንጂ ለጉዳት ሳይታሰብ የልጅቷን ሕልም አጨለመው።

ድርጊቱ እንዳይታወቅበት ልጅቷን ቢላዋ ይዞ “ብትናገሪ እንችንም እናትሽንም እገላችኋለሁ“ በማለት ዝም እንድትል አስጠነቀቃት። ልጅቷ ከዛን ቀን አንስቶ ደስታዋ መጥፋቱን እናት ብታስተውልም የልጅ ነገር ነው በማለት ቸል ትላታለች። ሰውየው ግን የሰራው ጥፋት ሳይነቃበት በመቆየቱ ሕፃኗን እየደጋገመ ይደፍራት ጀመር።

ከእለታት አንዱ ቀን እናት ሥራ ውላ መጥታ እንደተለመደው ልጇን ውሃ ስጪኝ ስትላት፤ ልጅቷ አስገድዶ ደፋሪ የተጫወተባት በመሆኑ መንቀሳቀስና ከመቀመጫዋ መነሳት አለመቻሏን ትመለከታለች። እናቷም ስትጠይቃት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አባቴ የምትለው ሰው ያደረገባትን ነገር በዝርዝር ትነግራታለች።

ሙዓዝ የተባለው የሴትየዋ ባለቤት በተደጋጋሚ እንደሚደፍራት እና ቢላዋ ይዞ “ብትናገሪ አንችንም እናትሽንም እገላችኋለሁ::" እያለ ያስፈራራት እንደነበር ለእናቷ ትናገራለች። ከሥራ ደክሟት የመጣችው እናት በራሷ የደረሰው ቁስል በልጇ መድረሱን ስትሰማ እንደ እብድ እያደረጋት ወደ ፖሊስ ጣቢያ በረረች።

ለፖሊሶቹ በልጇ ላይ የደረሰባትን ነገር በሙሉ በእንባ በማጀብ ታስረዳለች:: ፖሊሶቹን ወደ ቤት ይዛቸው ስትመጣ አድብቶ አራጁ አባት የሠራውን ሠርቶ አገር ሠላም ብሎ ቤት ቁጭ እንዳለ ተገኘ:: ፖሊስ ያለብዙ ውጣ ውረድ ግለሰቡን በቁጥጥር ሰር አዋለው። እናት ወንጀለኛው መያዙን አረጋግጣ፤ በማታ ልጇን ይዛ ወደ ሕክምና ቦታ ሄደች። በሆስፒታሉ በድንገተኛ ክፍል ተቀብለው ያስተናገዷት ሀኪሞችም ጉዳቱ የከፋ ባይሆንም የስነ ልቦና ጉዳቷ ከፍ ያለ መሆኑን ነግረው፤ ክትትል እንደታደርግ መክረው ወደ ቤት ላኩዋት። ባመነችው የተከዳችው እናት እንባዋን እያፈሰሰች ልጇን አቅፋ ፍትህ እስክታገኝ መጠባበቅ ቀጠለች።

### የፖሊስ ምርመራ

የፖሊስ ምርመራ ቡድኑ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ወዲያው ምርመራውን ቀጠለ። የልጅቷን ቃል፤ የሕክምና ምርመራ ወረቀትን ይዞ የተጠርጣሪውን የእምነት ክህደት ቃሉን ለመቀበል ቁጭ አለ። ድርጊቱን የፈፀመው ሰው መጀመሪያ ጉዳዩን ማመን ባይፈልግም ምርመራው እየጠነከረ ማስረጃዎች እየወጡ ሲሄዱ፤ ጥፋቱን አምኖ መቀበል ግድ ሆነበት። አዎ በተደጋጋሚ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ሲል አመነ::

ተጠርጣሪው ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ቁጥር 627/1/ እና 627/4/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ለአካለ መጠን ያልደረሰችን ልጅ በተለያዩ ቀናት እና ጊዜ በተደጋጋሚ አስገድዶ በመድፈር ወንጀል ተከሶ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የመርማሪ ፖሊስ ቡድኑ ለዐቃቤ ሕግ አቀረበ::

### የአቃቤ ህግ ክስ ዝርዝር

የዐቃቤ ሕግም ከፖሊስ የምርመራ ቡድን የቀረበለትን ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ አስፈላጊውን ስርዓት ይዞ አጥፊው ለፍርድ የሚቀርብብት አካሄድ ላይ መሥራት ጀመረ። አቃቤ ሕግ ያገኘውን ማስረጃ በመጠቀም በእዚህ መልኩ የክስ ዝርዝሩን አቅርቧል።

ሙዓዝ ክፍሌ የተባለው ተከሳሽ ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 5፡00 ስዓት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው ካራ ጋቢሳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የ8 ዓመት ዕድሜ ያላትንና በራሱ ቁጥጥር ስር የሚያሳድጋትን የእንጀራ ልጁን ከትምህርት ቤት ስትመጣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ አፏን አፍኖ አስገድዶ ደፍሯታል:: ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላም እናቷ ከስራ መጥታ ውሃ ስጪኝ ስትላት መንቀሳቀስና ከመቀመጫዋ መነሳት ባለመቻሏ እናቷም ስትጠይቃት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተደጋጋሚ እንደሚደፍራት እና ቢላዋ ይዞ “ብትናገሪ እንችንም እናትሽንም እገላችኋለሁ“ እያለ ያስፈራራት የነበረ መሆኑን ተናግራ እናት ለፖሊስ ጥቆማ ሰጥታለች:: ጥቆማውን ተከትሎ በተካሔደው ምርመራ ተከሳሽ ሙዓዝ ድርጊቱን ይፈፅም እንደነበር እና የሕፃኗን ቃል፣ የተከሳሹን የእምነት ክህደት ቃል እና የሕክምና ማስረጃውን በማጠናቀር ዐቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝሩን አቅርቧል::

በክስ ዝርዝሩ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ቁጥር 627/1/እና 627/4/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ለአካለ መጠን ያልደረሰችን ልጅ በተለያዩ ቀናት እና ጊዜ በተደጋጋሚ አስገድዶ በመድፈሩ ተከሶ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተመላክቷል::

### ውሳኔ

**በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ቢሰጠውም ተከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበበትን ክስና ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ሙዓዝ በተከሰሰበት ወንጀል የጥፋተኝነት ብይን አስተላልፎበታል:: በመሆኑም የፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ 7 ኛ ወንጀል ችሎት ተካሣሹን ያስተምራል፣ ያርማል ሌላውንም የማኅበረሰብ ክፍል ያስጠነቅቃል በማለት በ15 (አስራ አምስት) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል::**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# እንግሊዘኛ እውቀት ወይስ ክህሎት?

**ዋስልኝ አየለ**

እንደ ጃፓን እና ቻይና ያሉ የበለፀጉ ሀገራት እንግሊዘኛ ቋንቋ መናገር ግዴታቸው አይደለም። እንግሊዘኛ ቋንቋ ላይ መራቀቅ የሥልጣኔ መገለጫቸው አይደለም። እንዲያውም ጃፓን ውስጥ ከቅርብ ዘመን ወዲህ ተጀመረ እንጂ እንግሊዘኛ አይነገርም ነበር። አሁንም ቢሆን መረጃዎች እንደሚያሳዩት ጃፓን ውስጥ እንግሊዘኛ የሚሞካከሩ 13 በመቶ ብቻ ናቸው። እዚህ ላይ አንድ የፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴን ገጠመኝ ልጥቀስ።

ለታሪክ ጥናት ጃፓን በቆዩበት ጊዜ በጣም የተቸገሩት በቋንቋ ነበር። በሀገሪቱ ውስጥ አሉ የሚባሉ የታሪክ ተመራማሪዎችና የዩኒቨርሲቲ ምሑራን እንግሊዘኛ አይችሉም። ይሄኔ ፕሮፌሰር ባሕሩ አንድ ጥያቄ ጠየቁ። ‹‹ለመሆኑ የዓለምን ታሪክ የምታስተምሩት በምንድነው?›› የሚል ነበር። የተሰጣቸው መልስ ‹‹ወደ ጃፓንኛ ያልተተረጎመ ታሪክ ለምን እናስተምራለን?›› የሚል ነበር። የዓለምን ታሪክ ለተማሪዎቻቸው የሚያስተምሩት ወደ ጃፓንኛ አስተርጉመው ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ጥቂት ምሑራንን ያሠለጥናሉ ማለት ነው።

ይህ ለምን ሆነ? ብለን ከጠየቅን የራሳቸውን ማንነትና ምንነት ስለገነቡ ነው። በአሜሪካና አውሮፓ ሀገራት ላይ ጥገኛ ለመሆን ስለማይገደዱ ነው። ከአውሮፓ ሀገራት የኮረጁት አነጋገርና አለባበስን ሳይሆን ራሱን ጥበብን ስለሆነ። የወሰዱት የተሠራውን ቁስ አካል ሳይሆን አሠራሩን ስለሆነ። ስለዚህ እንግሊዘኛ ለመናገር አይገደዱም።

ነገሩን ወደ አፍሪካ እናምጣው። ከኢትዮጵያና ላይቤሪያ በስተቀር የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ የተገዙ ናቸው። ሥር የሰደደ እና የዳበረ የራሳቸው ማንነትና ምንነት የላቸውም። ብዙዎች የሥራ ቋንቋቸው ሳይቀር ቅኝ በተገዙበት ሀገር ነው። እንግሊዘኛና ፈረንሳይኛ ዋናዎቹ ናቸው። ስለዚህ ሀገራቱ የእነዚህ ቅኝ ገዥዎቻቸው ጥገኛ ናቸው። የአስተዳዳሪዎቻቸው ቋንቋ ነው። የዘመን አቆጣጠራቸውም ሆነ ሁሉ ነገራቸው በቅኝ ገዥዎቻቸው የተቃኘ ስለሆነ እንግሊዘኛ ማወቅ ግዴታ ሆኖባቸዋል ማለት ነው። በብዙ የአፍሪካ አገራት ከአገር መሪ እስከ አርሶ አደር እንግሊዘኛ ይናገራሉ።

አሁን ደግሞ እንግሊዘኛን ከአፍሪካ ወደ ኢትዮጵያ እናምጣው። ኢትዮጵያ ልክ እንደ ኃያላኑ የአውሮፓ ሀገራት የራሷ ቋንቋና ፊደል፣ የዘመን አቆጣጠር ያላት ናት። እንግሊዘኛ ቋንቋ መስፋፋት የጀመረው በ17ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ያሳያሉ። የአማርኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥታት ቋንቋ ሆኖ ያገለግል የነበረው ግን ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የጻፏቸው ሰነዶች ያሳያሉ። በ12ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያኑም ቢሆን ከአማርኛ የተለየ የዳበረ ቋንቋ አልነበራቸውም።

አማርኛ የመንግሥታት ቋንቋ በመሆኑ በመላው ኢትዮጵያ የመስፋፋት ዕድል አገኘ። በዚያ ላይ ኢትዮጵያ የብዝኃ ማንነት ሀገር ስለሆነች ብዙ ብሔሮች የየራሳቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ አላቸው። በአጠቃላይ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ያለ ማኅበረሰብ ከእናቱ የሚሰማው ቋንቋ እንግሊዘኛ ሳይሆን የአካባቢውን አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። ወደ ከተሞች አካባቢ ደግሞ አማርኛ ነው። ለዘመናት የኢትዮጵያ የሥራ ቋንቋ የሆነውንና የብዙ አካባቢዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ምሳሌ አድርገን እንቀጥል።

አንድ በአማርኛ አፉን የፈታ ኢትዮጵያዊ በአካባቢው ሲያድግ በአማርኛ የትኛውንም አገልግሎት እያገኘ ነው። በአማርኛ ሙዚቃ እየሰማ፣ የአማርኛ ፊልሞችንና ድራማዎችን እያየ፣ የዳበሩ የአማርኛ ተረቶችን እየሰማ፣ አካባቢውን በአማርኛ እየተረዳ፣ የሀገሩንና የዓለምን ታሪክ በአማርኛ እየሰማ ያድጋል። ይህ ሰው እንግሊዘኛን የሚያገኘው በትምህርት ሂደት ነው። በትምህርት ሂደት የሚያገኘው እንግሊዘኛ ደግሞ አካዳሚያዊ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ ነው። ስለዚህ ይህ ሰው በእንግሊዘኛ ቅኔ የሚቀኝና በእንግሊዘኛ የሚራቀቅ አይሆንም ማለት ነው። ምክንያቱም ቅኔ የሚቀኝበትና የሚራቀቅበት የራሱ ቋንቋ አለው።

አንድ በኦሮምኛ ወይም በትግርኛ ወይም በአፋርኛ ወይም በሶማሊኛ አፉን የፈታ ሰው በራሱ ቋንቋ እምቅ ቅኔና ሥነ ቃል አለው። አካባቢውን የሚያውቀው በራሱ ባሕልና ቋንቋ ነው። ስለዚህ ይህ ሰው በምን አግባብ እንግሊዘኛ ላይ የሚራቀቅ ሊሆን ይችላል? ግዴታስ አለበት ወይ? በራስ ቋንቋ የሚታወቅ እውቀት እንደ ዕውቀት አይቆጠርም ወይ? የዓለምን ጓዳ ጎድጓዳ ታሪክና የተፈጥሮን ምሥጢር በአማርኛ ብናገረው እንደ እውቀት አይቆጠርልንም ወይ?

አንድ የማያከራክር እውነታ አለ። እንግሊዘኛ ማወቅ ብዙ ጥቅም አለው። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ግዴታ የሚሆንበት አጋጣሚም አለ። ምክንያቱም ቋንቋው ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነው። በቴክኖሎጂ የዳበረ ቋንቋ ነው። ብዙ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና መተግበሪያዎች የአሠራር መመሪያ (Instruction) በእንግሊዘኛ ነው። ከዚህ የተነሳ ልማድ አድርገነዋል። ለምሳሌ የብር ማውጫ ማሽን (ኤ ቲ ኤም) ቋንቋ ሲያስመርጠኝ የምመርጠው እንግሊዘኛን ነው። የተለየ የእንግሊዘኛ ፍቅር ወይም ችሎታ ኖሮኝ ሳይሆን የእንግሊዘኛ ትዕዛዞችን ስለተላመድኳቸው ነው። የኢሜይል ግድግዳዬ ትዕዛዞች በአማርኛ ሲሆኑ ግራ ይገባኛል። ይህ ቴክኖሎጂው ያመጣው ተፅዕኖ ነው። ስለዚህ እንግሊዘኛን መላቀቅ አይቻልም ማለት ነው።

ዳሩ ግን ቋንቋውን ከቋንቋነት ባለፈ የእውቀት መለኪያ ማድረግ አላዋቂነት ነው። ቋንቋ በባሕሪው እውቀት ሳይሆን ክህሎት ነው። አፈጣጠሩም ሆነ ዕድገቱ ዘፈቀዳዊ ነው። የሚያገለግለውም ለመግባቢያ ነው፤ መልዕክት ለማስተላለፍ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ግን እንግሊዘኛን የእውቀት መለኪያ አድርጎ ማየት ነው። ወቀሳው ደግሞ በተቃራኒው መሆኑ ነው። ለምሳሌ፤ ጋዜጠኛ እና ፖለቲከኛ የሚናገራቸው ቃላት በብዙኃኑ የሚታወቁ የተለመዱ ቃላት ሊሆኑ ይገባል። አሻሚ፣ ውስብስብ፣ ዘይቤ እና ፈሊጣዊ ቃላት የበዙበት ቃላትን መጠቀም ለጋዜጠኛና ፖለቲከኛ አይመከርም። በዚህም ምክንያት ፖለቲከኞች በእንግሊዘኛ ሲናገሩ ግልጽ እና የተለመዱ ቃላትን መሆን አለበት።

ብዙ ጊዜ ግን እንደ ብቁ የእንግሊዘኛ ተናጋሪ የሚታየው በቃላት ላይ ቃላት እየደራረቡ በፍጥነት መንጣጣት እና በእንግሊዘኛው ‹‹Idiomatic›› የሚባለውን ከመዝገበ ቃላት ተፈልገው የሚገኙ ፈሊጣዊ ቃላትን መጠቀም ነው። ሲጀመር እንዲህ አይነት ቃላትን መጠቀም ለጋዜጠኛና ፖለቲከኛ አይመከርም። ‹‹ምን ማለት ይሆን?›› የማይባሉ ቃላትን ነው መጠቀም ያለባቸው። በቋንቋ ባለሙያዎች ‹‹ከባዱ ነገር ቀላል ማድረግ ነው›› ይባላል። ቀላል ማድረግ ማለት ለሁሉም የሚገባ ማድረግ ማለት ነው። በቃላት መራቀቅና መፈላሰፍ ለጋዜጠኛና ፖለቲከኛ ሳይሆን ለልቦለድ ደራሲና ለኪነ ጥበብ ሥራዎች ነው። ምክንያቱም የኪነ ጥበብ አንዱ ውበት የቃላት ጨዋታው ሊሆን ይችላል። ገለጻዊ ለሆኑ ነገሮች ግን የሚመከረው በተቻለ መጠን አሻሚ ቃላትን ማስወገድ ነው።

ሌላው ችግር ደግሞ የቃላት አጠራር (Pronunciation) ነው። የቃላት አጠራር (አነባበብ) ከአገር አገር ብቻ ሳይሆን ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል። ብዙ ጊዜ እንደ እንግሊዘኛ ችሎታ የሚታየው ምላስን ቆልፎ አፍ መፍቻቸው የሆኑትን እንግሊዝና አሜሪካን ለመምሰል መታገል ነው። በነባራዊ ሁኔታዎች ምክንያት እንግሊዘኛ መናገር ግዴታ ሊሆን ቢችልም የእንግሊዝ ተወላጅ ዜጎችን ለመምሰል መታገል ግን ግዴታ አይሆንም። ምክንያቱም ዓረቦችም፣ ሕንዶችም፣ ቻይናዎችም የሚታወቁበት የየራሳቸው የእንግሊዘኛ ዘዬ (አክሰንት) አላቸው።

በሌላ በኩል አፋቸውን በእንግሊዘኛ የፈቱ ሀገራት (እንግሊዝና አሜሪካ) ራሱ የአጠራር (አነባበብ) ልዩነት አላቸው። ስለዚህ ‹‹እገሌ ትክክለኛ እንግሊዘኛ ተናጋሪ ነው›› ሊባል ይችላል ወይ? እንዴት ሲሆን ነው ትክክለኛ እንግሊዘኛ ተናጋሪ የሚባለው? ማንን ሲመስል ነው?

በአጠቃላይ እንግሊዘኛ ክህሎት እንጂ እውቀት አይደለም። አንድ ጃፓናዊ ወይም ቻይናዊ እንግሊዘኛ የማይችል (ምናልባትም የማይፈልግ) ሆኖ በአስተርጓሚ ሲናገር እንደ ኩሩ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ እንግሊዘኛ ካልተናገረ ግን እንደ መሐይም የሚታየው በምን አግባብ ነው? ኢትዮጵያዊው በራሱ መኩራት አይችልም እንዴ?

ልብ ማለት ያለብን ነገር፤ ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ያደገ ኢትዮጵያዊ በራሱ ቋንቋና ማንነት ያደገ መሆኑን ነው!

# ዓለም አቀፍ

## ኔቶ ከእሥራኤል ጋር ለመተባበር የሚያደርገውን ጥረት እንደምትቃወም ቱርክ አሳወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቱርክ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ከእሥራኤል ጋር ትብብሩን መቀጠል አይችልም ስትል ተቃወመች።

በዋሽንግተን ዲሲ በተካሄደው የኔቶ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ የተሳተፉት ፕሬዚዳንት ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶሃን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ነው ተቃውሟቸውን ያሰሙት።

“በፍልስጤም ሁሉን አካታች እና ዘላቂ ሠላም እስካልተረጋገጠ ድረስ ኔቶ ከእሥራኤል ጋር የሚያደርገው ትብብር በቱርክ ተቀባይነት አይኖረውም” ብለዋል ፕሬዚዳንቱ።

የእሥራኤልና ሃማስ ጦርነት ከተጀመረ አንስቶ በእሥራኤል ላይ የሰላ ትችት የሚሰነዝሩት ኤርዶሃን 32 አባላት ያሉት ወታደራዊ ስብስብ ለቴል አቪቭ ድጋፍ ከማድረግ እንዲቆጠብ ነው የጠየቁት።

አንካራ ለስዊድን የኔቶ አባልነት ጥያቄ ድጋፍ መስጠቷን ተከትሎ 23 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ኤፍ-16 ጄቶችና መለዋወጫዎች ግዥ እንድትፈጽም አሜሪካ መፍቀዷ የሚታወስ ነው።

የስዊድንን የኔቶ አባልነት ጥያቄ ለመቀበል ያስቀመጠችው ቅድመ ሁኔታም ከአሜሪካ ጋር ዳግም ግንኙነቷን እንድታድስ ማድረጉ ይታወሳል።

ፕሬዚዳንት ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶሃን በኔቶ ዓመታዊ ጉባኤ የወታደራዊ ጥምረቱ አባላት አንካራ በሽብርተኞች ላይ የጀመረችውን ዘመቻ እንዲያግዟት ጠይቀዋል።



ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶሃን

ኤርዶሃን በስም ባይጠቅሷቸውም የተወሰኑ የስብሰቡ አባል ሀገራት ከዋይፒጂ ታጣቂዎች ጋር ግንኙነት እንዳላቸውን ነው ያነሱት።

ከኩርዲስታን ሠራተኞች ፓርቲ (ፒኬኬ) ጋር ግንኙነት ያለው ዋይፒጂን በሽብርተኝነት የፈረጀችው ቱርክ፥ ምዕራባውያን አጋሮቿ እንደ ፒኬኬ ሁሉ ዋይፒጂን በሽብርተኝነት እንዲመዘግቡት ተደጋጋሚ ጥሪ ማቅረቧን ሬውተርስ አስታውሷል።

## የሩዋንዳ ወታደሮች ከኮንጎን እንዲወጡ ተጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎን መንግሥት ለመጣል ከሚንቀሳቀሰው ኤም 23 አማጺ ቡድን ጋር የተሰለፉ እስከ 4ሺ የሚጠጉ የሩዋንዳ ወታደሮች ሀገሪቷን ለቀው እንዲወጡ የተባበሩት መንግሥታቱ ድርጅት ጠየቀ።

የሩዋንዳ መንግሥት በአሜሪካና በዓለም አቀፍ ተቋማት በጦርነቱ ዙሪያ ባለው ተሳትፎ የሚቀርብበትን ክስ ሲያስተባብል ቆይቷል።

ከሰሞኑ ተመድ ባወጣው ሪፖርት የሩዋንዳ ሠራዊት በጦርነቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳለው አረጋግጫለሁ ብሏል።

ሩዋንዳ የኮንጎን ሉዓላዊነት ተላልፋለች ያለው ድርጅቱ ግጭቱ ከዚህ የበለጠ ከመስፋፋቱ በፊት ሀገሪቱ ጦሯን እንድታስወጣ ጠይቋል።

የኮንጎ ምሥራቅ ክፍል ላለፉት ሁለት ዓመታት ነፍጥ ባነገቡ ታጣቂዎች እየታመሰ ሲሆን በአካባቢው 120 የሚጠጉ ታጣቂዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከፍሊክስ ቴሽኬዲ መንግሥት ጋር እየተዋጉ ይገኛሉ።

ምሥራቅ ኮንጎ ታጣቂዎች የማዕድን ስፍራዎችን ለመቆጣጠር፣ አካባቢያቸውን ከመንግሥት እና ከታጣቂ ኃይሎች ጥቃት ለመከላከል እንዲሁም ፖለቲካዊ ዓላማ አንግበው የሚዋጉ ታጣቂዎች የሚገኙበት ስፍራ ነው።

በመንግሥታቱ ድርጅት ማዕቀብ የተጣለበት ኤም 23 ከሩዋንዳ መንግሥት በሚያገኛቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች በጦርነቱ በርካታ ስፍራዎችን እየተቆጣጠረ መቀጠሉ በሪፖርቱ ላይ የተገለጸ ሲሆን ፤ የመካከለኛ ርቀት የአየር መቃወሚያ ፣ ሞርታር እና ሌሎች ከባድ መሣሪያዎችን በጦርነቱ ጥቅም ላይ እያዋለ ይገኛል ብሏል።

ከሩዋንዳ ቱትሲ ብሔረሰብ ጋር የደም ግንኙነት እንዳላቸው የሚነገርላቸው የኤም 23 አማጺ ቡድኖች የምሥራቅ ኮንጎ ትልቋ ከተማ የሆነችውን ጎማ ከተማን



መቆጣጠር ችለው ነበር።

ከሁለት ዓመታት በላይ በውጊያ ላይ የሚገኘው የሀገሪቱ ጦር በሎጂስቲክ አቅርቦት እጥረት፣ በውስጥ ክፍፍል እና በውጊያ አቅም መዳከም እየተናጠ ይገኛል።

በአማጺያን እና በሀገሪቱ ጦር መካከል በተለያዩ ስፍራዎች በሚደረገው ጦርነት ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ተሻግሯል።

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ፕሬዚዳንት ፍሊክስ ቴሽኬዲ የሩዋንዳ መንግሥት ለአማጺያኑ የሚያደርገውን ድጋፍ የማያቆም ከሆነ በሩዋንዳ ላይ ጦርነት እናውጃለን ብለዋል።

ተመድ በሪፖርቱ በሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት የሚገኘው ሁኔታ እጅግ አስከፊ ነው ያለ ሲሆን በተለይ ውጊያ በተፋፋመባቸው አካባቢዎች ያሉት የሰብዓዊ ሁኔታዎች አስቸኳይ ምላሽ የሚሹ ናቸው ብሏል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ጭፍን ፍረጃ፣ ጥላቻንና አግላይነትን ማስወገድ!

**አስናቀ ፀጋዬ**

የማኅበራዊ ስነ-ልቦና ሳይንስ አንድ ሰው በሌሎች ኑሮ ምክንያት የሚደርስበትን ተፅእኖ ወይም የእርሱ ኑሮ በሌሎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ያጠናል:: ይህም በማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ በሚፈጠር ግንኙነት የተነሳ አንዱ ሌላው ላይ ወይም ሌላው አንዱ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ያጠቃልላል:: በዚህ ተፅእኖ ምክንያትም ሌሎች ሰዎችን የምናይበት መንገድ የተለያየ ይሆናል:: ማኅበራዊ እይታ ደግሞ በሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ያለን አመለካከት ሲሆን ከዚህ በመነሳት ሌሎች ሰዎች እንዲህ ናቸው፤ እንዲያ ናቸው እያልን እንመድባቸዋለን ወይም እንፈርጃቸዋለን::

አንዳንድ ግዜ ምደባችን ወይም ፍረጃችን በተጨባጭ መረጃ ላይ ያልተመሰረተና በምክንያት ያልተደገፈ፣ በደፈናው ፊት ለፊት ካገኘነው ነገር በመነሳት የሚሰጥ ሊሆን ይችላል:: ጭፍን ፍረጃ ወይም /stereotype/ ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በተወሰነ አካላዊ አቀማመጥ ወይም ሌላ እውነታ ላይ የተመሰረተ አመለካከት ነው የሚባለውም ለዚህ ነው:: ለምሳሌ የቆዳ ቀለምን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን ወይም የሚያሳየውን ባህሪይ በማየት ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚኖር አመለካከት ጭፍን ፍረጃ ነው::

ጭፍን ፍረጃን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ግለሰብ ተኮር ፍረጃ ሲሆን ይህ የፍረጃ አይነት በግለሰብ ላይ ያነጣጠረ ነው:: ለምሳሌ የሰዎች መጠሪያ ስም ላይ ተንተርሶ የሚኖር አመለካከት ግለሰብ ተኮር ፍረጃ ሊባል ይችላል:: በ1973 እ.ኤ.አ በሀራንና ማክዴቪድ የፅሁፍና የማርክ አሰጣጥ ላይ በተሰራ ጥናት በጣም ሳቢ ስም ያላቸው ተማሪዎች ሳቢ ስም ከሌላቸው ተማሪዎች የተሻለ ማርክ ተሰጥቷቸዋል:: በሌላ በኩል ግለሰባዊ ፍረጃ አካላዊ አቋምን በማየት የሚደረግ ነው:: በዚህም እ.ኤ.አ በ1967 በተሰራ አንድ ጥናት ቆንጆ መልክና ቁመና ያላቸው ሰዎች ከሌላቸው ሰዎች ይልቅ ደስተኞች፣ ጥሩዎችና ጎበዝ ተወዳዳሪዎች ናቸው የሚል የተሳሳተ ፍረጃ ተሰጥቷቸው ነበር::

ሁለተኛው ፍረጃ የቡድን ተኮር ፍረጃ ሲሆን እንዲህ አይነቱ ፍረጃ የሚመነጨው አንድ ግለሰብ የሆነ ቡድን አባል በመሆኑ ምክንያት የተነሳ የሚኖር የተዛባ አመለካከት ነው:: ይህም በአብዛኛው ከጭፍን ጥላቻ ጋር የመመሳሰል ሁኔታ አለው:: ካዝና ብራል የተባሉ ተመራማሪዎች እ.ኤ.አ በ1933 በብሄርተኝነት ላይ ጥናት ለማድረግ መላ ዘይደው ነበር:: በዚህም ለጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ የብሔር ቡድኖችን ለአብነትም አሜሪካውያንና አይሁዶችን እንዲሁም 84 የስብእና መገለጫ ቃላቶችን አቅርበውላቸው ነበር:: ከዚህ በኋላ የጥናቱ ተሳታፊዎች አምስት ወይም ስድስት የስብእና መገለጫ ቃላቶችን ለየብሄሮቹ እንዲሰጡና እንዲገልፁ ተነገራቸው::

ይህ ጥናት በወቅቱ ያሳየው እነዚህ ተሳታፊዎች በተወሰኑ ብሄሮች ላይ ጭፍን የሆነ ፍረጃ ወይም ጥላቻ እንዳለባቸው ነበር:: ይኸው ጥናት እ.ኤ.አ በ1951 እና በ1967 ሲደገም ፍረጃውና ጥላቻው በፊት ከነበረው ቀንሶ ታይቷል::

ጭፍን ጥላቻ ወይም /prejudice/ የጭፍን ፍረጃ ወይም /stereotype/ ፅንፍ ወይም ጥግ ነው:: ከላይ በተቀመጡት የአመለካከት ክፍሎች መሰረት ጭፍን ፍረጃ አስተሳሰባዊ፣ ጭፍን ጥላቻ ስሜታዊ፣ እንዲሁም አግላይነት ባህሪያዊ ይሆናል:: የጭፍን ጥላቻ ስሜት የሚያድግና የሚጎለብት ነው:: እንደ እውቁ የማኅበረሰብ ስነ-ልቦና ባለሞያ ጎርደን ኦልፖርት ይህ የጭፍን ጥላቻ እድገት በአምስት ደረጃዎች ይከፈላል::

አንደኛው አጉል ቀልድ ወይም የጥላቻ ንግግር ነው:: አጉል ቀልድ ወይም የጥላቻ ንግግር ስለ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በፌዝ፣ በቀልድ፣ በስላቅ፣ በሃሜት ወይም በማሾፍ የሚደረግ አሉታዊ ንግግር ነው:: ለምሳሌ አጥንት የሚሰብር ንግግር ተናገረኝ እንደሚባለው አይነት ንግግርና በብሄር ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሰረተ ቀልድን ጨምሮ ማለት ነው:: ይህ ሁኔታ እንደቀልድ ስለሚቆጠር በግለሰቡ ወይም በቡድኑ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያመጣ ይቆጠራል:: ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ንግግር የሰዎችን ስብእና ከመንካትም አልፎ በራስ መተማመንን የሚያወርድና ስለራስ የሚኖር ምስልን ዝቅ የሚያደርግ ነው::

ሁለተኛው መነጠል ወይም መለየት ነው:: ይህ የጭፍን ጥላቻ እድገት በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በሌላ ቡድን ከሚገኙ ጋር ይለያሉ ወይም ይነጠላሉ እንደማለት ነው:: በዚህ ግዜ አደጋው የበዛ ይሆናል:: ሌሎች ከቡድናቸው ውጪ ያሉ ቡድኖችን ወይም ሰዎችን የመፍራት ዝንባሌ ያሳያሉ:: ለምሳሌ መጤ ጠል ወይም /xenophobia/ ይከሰታል:: ይህም መገለልን ያስከትላል::

> **‹‹በማኅበረሰብ የመጣን ጭፍን ጥላቻ በቀላሉ ለማስወገድ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ነው፡፡ የሚያስቸግርበት አንዱ ምክንያት ጭፍን ጥላቻ አስተሳሰባዊና ስሜታዊ ክስተት በመሆኑ ነው፡፡ እናም ጭፍን ጥላቻ ከዚህ የሚፈልቅ አመለካከት ነው፡፡››**

ሶስተኛው አግላይነት ነው:: አግላይነት አንድ ቡድን ሌላውን ቡድን እኩልነት በማሳጣት፣ ፍትህ በመንፈግና በመሳሰሉት መንገዶች ይገለፃል:: ይኸውም የተለያዩ አገልግሎቶችን በመንፈግ፣ በመከልከል እንዲሁም እኩል አገልግሎት እንዳያገኙ ማድረግን ይጨምራል:: በዚህም የተገለለ ቡድን ስራ፣ ትምህርት፣ ሕክምናና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ክልከላ ይደረግባቸዋል:: በዚህ የአግላይነት ዘውግ ስር የስልጣን ተዋረድን በመጠቀም የሚደረግ አግላይነት ሲሆን ይህም እውቀትን፣ እድሜን ወይም ፆታንና ባህሪን መሰረት በማድረግ የተወሰኑ ቡድኖች እንዲገለሉ የሚደረግበት ነው::

አራተኛው አካላዊ ጥቃት ሲሆን በአብዛኛው የጥላቻ ጥቃት በመባል ይታወቃል:: በዚህም የተወሰኑ የቡድን አባላትን ለይቶ ማጥቃት፣ ንብረታቸውን ማቃጠል ወይም ግለሰቦቹን በመንጋ ማጥቃትና ጅምላ ጭፍጨፋ ማድረግን ያጠቃልላል::

አምስተኛውና የመጨረሻው የጭፍን ጥላቻ እድገት አይነት ጭፍጨፋ ማካሄድ ሲሆን የዘር ማጥፋት፣ የብሄር ማፅዳትንና የመሳሰሉትን ያካትታል:: ጎርደን ኦልፖርት እንደሚገልፀው ጭፍን ጥላቻ በተሳሳተ መንገድ በተወሰኑ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የሆነ ቡድን አባል በመሆናቸው ብቻ እነርሱ ላይ ያነጣጠረ ተለዋዋጭና ተጣጣፊ የሆነ ጥቅል መገለጫ ነው:: እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ግን ጭፍን ጥላቻ እንዴት ሊኖር ቻለ? የሚለው ነው::

ስለ ጭፍን ጥላቻ መኖርና አለመኖር ጥናት የማያስፈልገው ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተሰርተዋል:: ለምሳሌ አሮንሰንና ኦሽሮው ጃን ኦልዊት የምትባል አስተማሪን አሳትፈው ተማሪዎቿን ቡናማ የአይን ቀለም ያላቸው ሰማያዊ የአይን ቀለም ካላቸው ልጆች የተሻለ ጎበዝ ናቸው ብላ እንድትነገርላቸው ካደረጉ በኋላ በውጤቱ ሰማያዊ የአይን ቀለም ያላቸው ልጆች ቡናማ የአይን ቀለም ካላቸው ልጆች ያነሰ ውጤት ማስመዝገብ ጀምረው ነበር:: ምክንያቱም ቡናማ የአይን ቀለም ያላቸው ልጆች ይህ ንግግር ከተነገራቸው በኋላ አግልለዋቸው ስለነበር ነው::

በአብዛኛው ጭፍን ጥላቻ እንዴት ለብዙ ግዜ በውስጣችን ይቆያል የሚል ጥያቄ ይነሳል:: በመሰረቱ ጭፍን ጥላቻ ሳይናወጥ ለብዙ ግዜ መቆየት የሚችል ነው:: ይህም ማለት አንድ ግዜ በውስጣችን ካለ እንደነበር ለብዙ ግዜ ይቆያል ማለት ነው:: ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች ስለ ጭፍን ፍረጃ የነበሩ እውነታዎችን ከሌሎቹ ይልቅ በተሻለ ያስታውሳሉ:: ጭፍን ፍረጃ ያልተለመዱ ወይም ወጣ ያሉ ሁኔታዎችን ስለሚያደርግ አንድ ግዜ በጣም ከፍ ካለ ለማውረድ ከባድ ይሆናል::

ሌላው ነገሮችን አውነት አድርጎ መቀበል ነው:: ሰዎች ብዙውን ግዜ ለተደረገባቸው ፍረጃና ጥላቻ በምላሹ እነርሱም ያደርጉታል:: ይህ ጥላቻን በጥላቻ የመመለስ ሂደት ጥላቻን ይበልጥ ያባብሰዋል እንጂ አይቀንሰውም:: የሆነው ሆኖ ጭፍን ጥላቻን በተመለከተ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰነዝራሉ:: ከነዚህም ውስጥ ሁለቱ ይጠቀሳሉ::

አንደኛው የምሁራን ወገን ጭፍን ጥላቻ በተፈጥሮ አብሮን የሚወለድ ነው ሲል ሌላኛው ወገን ደግሞ ጭፍን ጥላቻ ከማኅብረሰብ ግንባታ ጋር የሚመጣ እንጂ በተፈጥሮ የሚገኝ አይደለም ሲል ይሞግታል:: ይህ ክርክር ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ እንችላለን ወይስ አንችልም የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መነሻ የሚሆን ነው:: በዚህም ላይ እንደተጠቀሰው ጭፍን ጥላቻ በተፈጥሮ የሚመጣ ነገር ከሆነ ማስወገድ ከባድ ነው የሚለውን ምላሽ ሲሰጥ በማኅበረሰብ ግንባታ ወቅት የሚመጣ ከሆነ ደግሞ የማኅበረሰቡን አተያይ በተለያየ መንገድ በመቀየር ማስወገድ ይቻላል ወደሚለው መደምደሚያ ይወስደናል::

ከላይ የተቀመጡትን ክርክሮች በመውሰድ ስነ ልቦናዊ አስተያየቶች እንዲህ ይላሉ፡- ቀደም ብሎ እንደተቀመጠው በተፈጥሮም ይሁን በማኅበረሰብ የመጣን ጭፍን ጥላቻ በቀላሉ ለማስወገድ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ነው:: የሚያስቸግርበት አንዱ ምክንያት ጭፍን ጥላቻ አስተሳሰባዊና ስሜታዊ ክስተት በመሆኑ ነው:: እናም ጭፍን ጥላቻ ከዚህ የሚፈልቅ አመለካከት ነው:: አመለካከት ደግሞ በውስጡ በርካታ ነገሮችን ያቅፋል:: አመለካከት ካለን እውቀትና ልምድ የተነሳ ይመጣል:: ይህም የምናየውን ብቻ እንድንረዳ ያደርገናል:: ሌላው አመለካከት ሌሎች ከሚሰጡን ጥሩ ወይም መጥፎ አስተያየት ጋር ይገናኛል:: ይህም ማለት ሌሎች ሰዎች ያላቸው አመለካከት እኛ ካለን አመላካከት ጋር ከተመሳሰለና ያንን የምንጋራ ከሆነ ለነዛ ሰዎች ወይም ቡድኖች ያለን አመለካከት የተለየ እንዲሆን ያነሳሳናል::

በሌላ በኩል ደግሞ አመለካከት ስለራሳችን ያለንን ዋጋ ከፍ እንዲል የማድረግ ስራ ይሰራል:: ይህም የሆነ አይነት አመለካከትን ማዳበር ለራሳችን የሚኖረንን ዋጋ ከፍ እንዳርጋለን፤ በመጨረሻም አመለካከት ራሳችንን ካላስፈላጊ ትችት የመከላከል ሥራ ይሰራል:: በዚህም ጭፍን ጥላቻ ያለምንም በቂ ምክንያት በሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ላይ የበላይነትን የማሳየት ዝንባሌ እንዲይዝ ያደርጋል::

እውቁ የስነ- ልቦና ምሁር ሲግመንድ ፍሮይድ እንደሚለው ሰዎች ጠበኝነታቸውንና ፍርሃታቸውን በትክክለኛው ምክንያት ላይ ንዴታቸውን ከመግለፅ ይልቅ በሌላ ነገር ላይ ያስወጡታል:: በሌላ በኩል በዚህ የፍርሃት ጠበኝነት አዙሪት ውስጥ መግባታቸው ሰዎች ፍርሃታቸውንና ጠበኝነታቸውን እንደምክንያትና ውጤት ይጠቀሙበታል:: ይህም ማለት ፍርሃት ለጠበኝነት መንስኤ፤ እንዲሁም ጠበኝነት እንደገና ፍርሃትን ይወልዳል::

ሌላው ጭፍን ጥላቻን ከውስጣችን እንዳይወገድ ከባድ ከሚያደርጉ ስነ -ልቦናዊ መላምቶች የታችፌልና ተርነር ማኅበረሰብ ማንነት መላ ምት ነው:: ይህ ማለት ሰዎች በተፈጥሮ ለራሳቸው መልካም ገፅታ ለመገንባት ይታገላሉ:: በዚህ ሂደት ውስጥ ማኅበራዊ ማንነት ሰዎችን ቡድን ውስጥና ከቡድን ውጪ በሚል በመከፋፈል ይገለፃል:: ይህ ማኅበራዊ ማንነትን የመገንባት ሂደት ጭፍን ጥላቻ እንዲፈጠር ያደርጋል::

ሰዎች ለራሳቸው መልካም ግምትን በመገንባት ሂደት ውስጥ ሁለት አይነት ገፅታዎች ይኖራሉ:: አንደኛው የግላዊ ማንነትን መገንባት ሲሆን ሌላኛው ማኅበራዊ ማንትን መገንባት ነው:: በሌላ በኩል አዶርኖ የተባለ ተመራማሪ በበኩሉ ጭፍን ጥላቻን ሊፈጥር የሚችል ማግነናዊ ስብእና አለ ብሎ ይከራከራል:: ይህ የስብእና አይነት ዝቅተኛ የማኅበረሰብ ክፍሎች ወይም ቡድኖችን የመናቅና ዝቅ አድርጎ የመመልከት እንዲሁም ከፍ ያሉ ማኅበረሰቦችን የማጉላትና ለእነሱ የማጎብደድ የስብእና አይነት ሲሆን ይህ አይነት ስብእና ያላቸው ሰዎች እጅግ ግትርና የማይተጣጠፉ ናቸው ይላል::

አዶርኖ እንደሚለው ይህ የስብእና አይነት ከአስተዳደግ ችግርና ከማኅበረሰብ ጫና የሚመጣ ነው:: ይህም ማለት በአስተዳደግ ወቅት ቤተሰቦቻቸው በጣም ወግ አጥባቂ፣ ሃይለኛና ከፍተኛ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ልጆች በወላጆቻቸው ላይ እልህና ቁጭት ውስጥ ይገባሉ:: ነገር ግን በወቅቱ ስለማያወጡት ተደብቆ ይቆይና ኋላ ላይ በነዚህ ዝቅተኛ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ያወጡታል:: ዋናው ጥያቄ ጭፍን ጥላቻን ለመቀነስ ምን ይደረግ? የሚለው ነው::

ከዚህ በፊት ጭፍን ጥላቻን ፈፅሞ ለማስወገድ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ አይተናል:: ነገር ግን ማስወገድ እንችላለን ብለን ካሰብን የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል:: በዘርፉ ምርምር ያደረጉ ሰዎችም የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ እንችላልን ይላሉ::

1ኛ. በቡድን በተደራጁና ባልተደራጁ ወይም በሌላ ቡድን ውስጥ ባሉ መካከል ምንም አይነት የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዳይኖር በማድረግና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ::

2ኛ. በሁለቱም የቡድን አባላት የሚሰራና መሳካት የሚችል የጋራ ዓላማ ማቀድና ለዛም በእኩልነት እንዲሰሩ ማድረግ::

ከላይ የተጠቀሱት መንገዶች ጭፍን ጥላቻን ማስወገድ የሚችሉ ቢሆንም በተለያዩ ሀገራት እስካሁን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባይቻልም በመቀነሱ ረገድ ግን መልካም ውጤት ተመዝግቧል:: በተለይ የጋራ ዓላማ ላይ መስራት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምሮበታል:: በዚህም ከተለያዩ የቡድን አባላት የመጡ ሰዎችን በመቀየጥና በጋራ ለሚመዘን ውጤት እንዲሰሩ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአምባሳደርነት ልዕልና፣

### የሀገርና ሕዝብ ጥቅምን አስቀድሞ በመሥራት ውስጥ ይገለፃል!

ከትብብር ይልቅ ውድድርና ፉክክር ላይ በተመሰረተችው ዓለም፤ ሀገራት ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ሲፈጽሙ ይስተዋላል። በተለይ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሚዛንን በራስ ፍላጎት ቃኝቶ ለማስጓዝ ባላቸው ከፍ ያለ መሻት፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በኪነ ጥበብና ፈጠራ፣ በታሪክና ባህል፤... የመሳሰሉ ጉዳዮችን ማዕከል አድርገው አንዱ በአንዱ ላይ የራሱን ማንነት ለማኖር ሲታትር ይታያል።

ከዚህ ሁሉ የበዛ ውድድር ባሻገር ግን፤ ሀገራት በባለ ብዙም ሆነ በሁለትዮሽ ግንኙነት ውስጥ የራስን ጥቅም ማዕከል ያደረገ የጋራ ተጠቃሚነትን መርኅ ሲያራምዱ ይታያል። የዚህ መርህ ማስኬጃ መሣሪያው ደግሞ ዲፕሎማሲ ነው። ዲፕሎማሲው ደግሞ በዲፕሎማቶች አማካኝነት ሲከወን፤ የዲፕሎማቶቹ ቀዳሚ ባለድርሻዎች ደግሞ አምባሳደሮች ናቸው።

ለዚህም ነው ሀገራት በዓለም መርኅ መሰረት በመካከላቸው ለሚኖር ማናቸውም ግንኙነት ዲፕሎማቶችን መድበውና አምባሳደሮችን ሾመው ሥራን የሚከውኑት። ይሄ የዲፕሎማሲ ሥራ ደግሞ እንደየሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ በኤምባሲ አልያም በቆንጽላ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት የሚከወን ሲሆን፤ በየኤምባሲዎቹ የሚመደቡ አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶችም የየተመደቡበትን ሀገርና ሕዝብ ጥቅም ማዕከል አድርገው እንዲሰሩ ይጠበቃል።

ኢትዮጵያም ባልተቆራረጠውና እድሜ ጠገብ በሆነው የሥርዓተ መንግስት ጉዞዋ፤ ከአንድ ከግማሽ ክፍለ ዘመን የተሻገረ የዲፕሎማሲ ግንኙነትን ስታከናውን ቆይታለች። በዚህም በርከት ያሉ የሁለትዮሽ ግንኙነቶቿን የሚወስኑ፤ የባለ ብዙ መድረክ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ሚናዋን የሚያጎለብቱ ተግባራትት በእነዚሁ ዲፕሎማቶቿ አማካኝነት አስጠብቃ ዘልቃለች።

ይሄ የኢትዮጵያ የሁለትዮሽም ሆነ የባለ ብዙ መድረክ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ታዲያ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀያየረ የተጓዘ ቢሆንም፤ ባለፉት አምስት ዓመታት የነበረው አካሄድ ግን ወርቃማ የዲፕሎማሲ ዘመን ተብለው ከሚመደቡት ተርታ የሚቀመጥ ነው። ምክንያቱም በእነዚህ ዓመታት ኢትዮጵያ የበዙ ፈተናዎችን የተጋፈጠችባቸው፤ እጅጉን የሚያኮሩ ስኬቶችና ውጤቶችንም ያስመዘገበችባቸው ናቸው።

ታዲያ እነዚህ የሀገር ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያ በተፈተነችና ዓለምአቀፍ ጫናዎች በበረቱባት ወቅት ከችግሮቿ መሻገሪያ መፍትሄን በማፈላለግም ሆነ ዓለምአቀፍ ጫናዎች እንዲረግቡ በማድረግ በኩል እነዚህ ዲፕሎማቶቿ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ከውነዋል። ሥራዎቻቸውም ፍሬ አፍርተው ኢትዮጵያ ከፈተናዎቿ ልቃ እንድትወጣ፤ ነጻነትና ሉዓላዊነቷም ተከብሮ እንዲዘልቅ አቅም ሆነዋል።

ከዚህም ባሻገር በሚገለጸው የስኬትና የውጤት መንገዷም ውስጥ ቢሆን፤ እነዚህ ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያ የችግርና ግጭት ሀገር ሳትሆን፤ እየተፈተነችና ጫና እየተደረገባትም ቢሆን ዘርፈ ብዙ ስኬቶችን እያስመዘገበች ያለች ሀገር መሆኗን በዓለም አደባባይ በመግለጥ ገጿን አድምቀዋል። በዚህም ከየአቅጣጫው እንዲጫንባት የሚፈለገውን ዘርፈ ብዙ ተጽዕኖ በማለዘብ ሂደት ውስጥ ከፍ ያለ ሚናቸውን ተወጥተዋል።

ይሁን እንጂ አምባሳደርነት ወይም ዲፕሎማትነት የአንድ ወቅት ስራ አይደለም። በተወሰኑ ግለሰቦች ላይም ተንጠልጥሎ የሚዘልቅ ሁነት አይደለም። ይልቁንም በየጊዜው አቅም መፍጠርን፤ አዳዲስ አቅሞችን ማካተትን፤ የዜጎችን ተሳትፎና ድጋፍ ማሳደግን፤... በጥቅሉ ከፍ ያለ አቅም፣ ክህሎትና የዲፕሎማትነት ልዕልናን የተጎናጸፈ አውድና አካሄድን መላበስን ይጠይቃል።

ከዚህ አኳያ ከሰሞኑ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን በዓለም መድረክ ከፍ አድርገው የሚገልጡ፤ የሀገርና ሕዝቦቻቸውን ጥቅም አስቀድመው የሚሰሩ አዳዲስ አምባሳደሮችን ከቀድሞዎቹ ጋር የሚያቀናጅ ተግባር ተከናውኗል። በዚህም አዳዲስ አምባሳደሮች ተሹመው፣ በተለያየ ጉዳዮች ላይ አቅም መፍጠር የሚያስችላቸው ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

ይሄ ስልጠና ደግሞ አዳዲስ ተሿሚ አምባሳደሮች፣ በሚሰማሩባቸው ቦታዎችና መስኮች ሁሉ ምን እንዴትና መቼ መሥራት እንዳለባቸው በልኩ ግንዛቤ እንዲይዙ የሚያስችል ነው። በተለይ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ በብዙ ፈተና ውስጥ እንዳለች እና በፈተና ውስጥም ከፍ ያለ ድልና ስኬት እያስመዘገበች እንዳለች ሀገር፤ ይሄንን በልኩ ተገንዝቦ የሚያስገነዝብ ዲፕሎማት ትሻለች።

በመሆኑም እነዚህ ዲፕሎማቶች ከምንም በላይ የሀገራቸውን እውነት አውቀው በማሳወቅ፤ ለሀገራቸው ልዕልና፣ ለሕዝባቸው ክብር፣ በጥቅሉም ሀገር እና ሕዝብ ለሚፈልገው ሁለንተናዊ ብልጽግና እና ልዕልና መሳካት የማይተካ ሚናቸውን መወጣት ይገባቸዋል። አምባሳደሮችም ኢትዮጵያን ወክለው በተለያዩ ሀገራት ሲሾሙ የመጀመሪያ ተግባራቸው ይሄው መሆኑን ተገንዝበው ሊሰሩ፤ አምባሳደርነታቸው የሚገለጸውም ስለ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ጥቅም በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ውስጥ መሆኑን አውቀው ሊሰሩ ይገባል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ፣ "አምባሳደሮች ከፍ ያለ የሀገር ፍቅር ብሎም፣ ሀገርንና ሕዝብን የማገልገል ስሜት ሊኖራቸው ይገባል፤ የሀገርንና የሕዝብን ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበር መትጋት ይጠበቅባቸዋል፤ ምክንያቱም አምባሳደር ሆኖ መመረጥ ሀገራዊ ኃላፊነትንና የሕዝብ አደራን በትጋት ለመወጣት የሚሰጥ ትልቅ ኃላፊነት ነው። በዲፕሎማት ሥራ ዋናው ቁም ነገርም የሕዝብና የሀገር አገልጋይነትን ከፍ ማድረግ ነው። " ሲሉ፣ በሥልጠና መርሃ ግብሩ መክፈቻ ላይ የተናገሩትም ለዚሁ ነው!

አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
• ኃይሉ ሣህለድንግል
• እስማኤል አረቦ
• ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ባለዘርፈ ብዙ ፋይዳው መርሀ ግብር

ክብረ መንግስት

እንደ አብዛኛው ሕዝቧ አርሶ አደር የሆነው ኢትዮጵያ ሐምሌ ወር የተስፋ፣ የእምነትና የበረከት ወሯ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። አርሶ አደሩ ፈጣሪውን አምኖ ጥሪቱን አሟጦ ባለሰለሰው ማሳ ላይ የሚዘራበትና እንደ አረምና ኩትኳቶ ባሉት የእንክብካቤ ስራዎች የሚጠምድበት ወር ነው።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር የተጀመረበት ሐምሌ 2011 ዓ.ም ደግሞ ልዩ ወሩ መሆኑን አጠናክሮታል። ከዚህ ዓመት አንስቶ መላ ኢትዮጵያን አረንጓዴ የሚያለብሰውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከግብርና ስራው ጎን ለጎን ከመላ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን በዚህ ወር በስፋት ያከናውናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሀገሪቱን አረንጓዴ ለማልበስ ያስጀመሩት ይህ መርሀ ግብር ይሄው ላለፉት ዓመታት በተጠናከረ መልኩ ተካሂዷል፤ ዘንድሮም ይበልጥ ተጠናክሮ ከሰባት ነጥብ አምስት ቢሊየን በላይ ችግኞች ይተከሉበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በ2011 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) 75ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር "የእኛ ዋነኛ ግብ የተራቆተውን መሬት በደን መሸፈንና የተሻለ ነገን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ስራችንን ከአረንጓዴና ከአየር ጠባይ ለውጥ ጋር በተስማማ መልኩ ማከናወን ነው፤ ይህን እውን ለማድረግም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለብን፤ ስለጉዳዩ የሚያሳስበን ሌላ አካል አያስፈልገንም። ምክንያቱም የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አውዳሚ ጥፋት በመላው ዓለም በተለያዩ ቦታዎች ላይ በተጨባጭ አይተነዋል" በማለት ለመርሃ ግብሩ ስኬታማነት ያላቸውን ቁርጠኝነታቸውን ባሳወቁት መሰረት ሀገሪቱን አረንጓዴ የማልበሱ ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩም ቃላቸውን በተግባር አረጋግጠዋል።

እስከ አሁን 32 ነጥብ አምስት ቢሊየን ችግኞች ተተክለዋል። በአንድ ጀምበር በመቶ ሚሊየን ችግኞችን መትከል የተቻለበትም ነው። በ2011 ዓ.ም በአንድ ጀምበር ብቻ 200 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ግብ ተቀምጦ፣ ከዚያ የላቀ መትከል ተችሏል። በ2015 ዓ.ም እንዲሁ በአንድ ጀምበር 500 ሚሊየን ለመትከል ታቅዶ ከ567 ሚሊየን በላይ መትከል ተችሏል። ዘንድሮም በብዙ መቶ ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን በአንድ ጀምበር በመትከል ስኬቱን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ታስቧል።

መርሃግብሩ ሀገራዊ እሳቤን ያነገበ በመሆኑም እንደ ሀገር ብዙ ለውጦችን እያመጣ ስለመሆኑ መርሃግብሩን በዋናነት የሚመራው አካል ሪፖርትም ያመላክታል። ኢትዮጵያ በመርሀ ግብሩ ያከናወነችውና እያከናወነች ያለችው የችግኝ ተከላ ዓለም አቀፍ አጀንዳ እስከመሆን ደርሷል። ሌሎች ሀገራትም ተሞክሮውን እንዲወስዱና እንዲተገብሩት አስከማስቻልም ተደርሷል።

የኢትዮጵያ የደን ሃብት ከግብርና፣ ከማገዶ፣ ከከሰል ማውጣት፣ ከልቅ ግጦሽ፣ ከግንባታና ከእንጨት ስራ ጋር በተያያዘ በማይታመን ፍጥነት መጠኑ መቀነሱ ይታወቃል። ይህን ሁኔታ መለወጥ ስለመጀመሩም እየተጠቆመ ነው።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ የሚተከሉ ችግኞች ጽድቀት እየጨመረ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፤ ፊት 75 በመቶ የነበረው የጽድቀት መጠን 80 በመቶ የደረሰበት ሁኔታ ታይቷል። በመርሀ ግብሩ ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቮካዶ፣ ቡና የመሳሰሉት ምርት እስከ መስጠት የደረሱበት ሁኔታም መርሀ ግብሩ ምድሪቱን አረንጓዴ ከማልበስ ባሻገር ለምግብ ዋስትናም አስተዋጽኦ ማድረግ ስለመጀመሩ ሌላው ማሳያ ነው።

በችግኝ ተከላው የፍራፍሬ ችግኞችን በስፋት የመትከሉ ስራ ዘንድሮም ተጠናክሮ ቀጥሏል። የችግኝ ተከላውን ከግብርና ስራ ጋር በማቀናጀት ማካሄድ እና አቮካዶን እንዲሁም ፓፓያን የመሳሳሉ ፍራፍሬዎችን ጨምሮ የተለያዩ ችግኞች እየተተከሉ ናቸው።

ችግኞቹን በጥናት ላይ ተመስርቶ በመለየት፤ ተገቢውን ችግኝና ዝርያ ለተገቢው አካባቢና ለትክክለኛው ዓላማ የመትከል ስራ እየተከናወነ ይገኛል። እንደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ያሉት የማንጎ ችግኝ በስፋት ወደ መትከል የገቡበት ሁኔታም ይህንን ያመለክታል። ይህም ሀገሪቱ በመርሀ ግብሩ የተመናመነባትን የደን ሀብት በድጋሚ ከማልማት ጎን ለጎን ለምግብ ዋስትና ስራም እያዋለችው መሆኑን ያመለክታል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሩ ባለቤቱና ተጠቃሚው ሕዝቡና ሕዝቡ ብቻ እንዲሆን ያስቻለ መሆኑ መርሃ ግብሩ በመታገዝ በርካታ የስራ ዕድል እድሎች እንዲፈጠሩም እያደረገ ነው። በተለይ የገጠሩን ማህበረሰብ ሕይወት በማሻሻል በኩል ብዙ ለውጦች ማሳየት እየተቻለ ነው።

በችግኝ ማፍላትና ማዘጋጀት ስራ በርካቶች የተሰማሩበት ሁኔታ ለሥራ እድል ፈጠራ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ያመለክታል። በተለይ ወጣቶችና ሴቶች ችግኝ በማፍላትና በመንከባከብ በስፋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ራሳቸውን በገቢም በምግብም እንዲደጉሙ እያስቻለ ነው።

የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም መልካምድርን መልሶ ከመፍጠር አንጻርም ለውጦች እየታዩ መሆናቸው እየተጠቀሰ ነው። አንዳንድ ጥብቅ ደኖች በዓለም አቀፉ የካርቦን ንግድ በኩል ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለም እየተገለጸ ይገኛል።

እንደሚታወቀው የደን ልማት እና የግብርና ሥራ በሚከናወንባቸው ስፍራዎች የሚኖረው አርሶ አደርና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ደረቃማው ወቅት ሲያበቃ ነው የአካባቢያቸው አፈር ርጥበታማ የሚሆነው። በዚህ ምክንያት ሁሌም ዝናብ ጠባቂ ናቸው። ይህም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ አምራች እንዲሆኑ ሲያስገድዳቸው ኖሯል።

በአረንጓዴ ዓሻራ መርሃ ግብሩ የተፋሰስ ልማት በተሰራላቸው የተጎዱ አካባቢዎች ላይ ችግኞችን በመትከል በአረንጓዴ ልማት ላይ መስራት ውስጥ በስፋት መገባቱ ይህን ሁሉ ሁኔታ ይቀይራል ተብሎ ይጠበቃል። የከርሰ ምድር ውሃ አቅም እየጨመረ ሊመጣ ይችላል፤ ምንጮች ውሃ መስጠት የማይቸገሩበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በአንዳንድ አካባቢዎችም ይሄው እየሆነ መሆኑ ይነገራል፤ ደርቀው የነበሩ ምንጮች ውሃ መስጠት ያቆሙበት፣ ደን በመመንጠሩ የተነሳ ተሰደው የነበሩ አንዳንድ የዱር እንስሳትና አእዋፋት ወደ ቀድሞ ቀዬቻው እየተመለሱ ስለመሆኑም ይገለጻል። መርሃ ግብሩ የውሃ አቅርቦትና ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ አርሶ አደሮችም በዓመት አንዴ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሶስቴ ማምረት ወደሚችሉበት ሁኔታም የሚገቡበት ሁኔታ እየተፈጠረ እንዲመጣም ያደርጋል።

ከዚህ ባለፈ መርሃ ግብሩ የተሻሻለ የግብርና አሰራርን በማስፈን፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ የአፈር፣ የውሃ ሃብትና የብዝሃ ህይወት ጥበቃን በማረጋገጥ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ማስገኘት እየተቻለ ስለመሆኑም የተለያዩ ወገኖች ይናገራሉ።

ይህ መርሃግብር ከተሞችንና አካባቢያቸውን ከማስዋብ ባለፈ ነፋሻና ንጹህ አየር የሚገኝባቸው እንዲሆኑ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የተበከሉ ወንዞችን ደህንነት በማስጠበቅ፣ የአረንጓዴ ስፍራዎች በስፋት በማልማት፣ ደኖች ተጠብቀውና ለምተው ለቱሪዝም አገልግሎት እንዲውሉ ምቹ ሁኔታንም ይፈጥራል።

ሀገሪቱ ይህን ተሞክሮ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ለማስፋትም እየሰራች ትገኛለች። ለጎረቤት ሀገሮች ችግኝ በማቅረብ ጭምር እያከናወነች ያለችው ተግባርም ይህንኑ ያመለክታል። የደን ልማት በአንድ ሀገር ውስጥ ብቻ ታጥሮ መቀመጥ ያለበት እንዳለመሆኑ መንግስት ይህን ማድረግ ውስጥ መግባቱ በተለይ ለአካባቢውና ለአፍሪካ ሀገሮች በአጠቃላይ ለዓለም ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

ስለዚህ ይህ ተግባር እንደ ሀገር ያለው ጥቅም እጅግ በርካታ ነው። ይህ መርሀ ግብር የያዘው ዓላማ እንዲሳካ እስከ አሁን በተከናወኑ ተግባሮች የተገኙ ልምዶችን ቀምሮ ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በተለይ የፍራፍሬ ልማትን ከመርሀ ግብሩ ጋር የማስተሳሰሩ ተግባር ያለው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ለሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች ልማትም ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል። ትኩረቱ ግን በልዩ ትኩረት ሊያዝ ይገባል። እነዚህ የዛፍ ዝርያዎች ለመሬት ለምነት፣ ለተያዘው የውሃ ሀብት ልማት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ይህ ብቻውን ለዝርያዎቹ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ያስገነዝባል። ዝርያዎቹ እንዲጠበቁ ከማድረግም በላይ እንዲለሙ ማድረግም ይገባል።

በአረንጓዴ ዐሻራም ይሁን በተለይ በከተሞች የአረንጓዴ ስፍራዎች ልማት ውስጥ በተለይ እንደ ወይራ ዛፍ ላሉት ልማት ትኩረት መሰጠቱ ያስመሰግናል። እነዚህ ወይራና የመሳሰሉት የዛፍ ዝርያዎች ደርሰው ለተፈለገው ዓላማ ለመዋል ረጅም እድሜ የሚጠይቁና ልዩ እንክብካቤ የሚፈልጉ ቢሆኑም ያለምንም መታከት በልዩ ትኩረት ልማታቸው ላይ መስራት ይኖርበታል። የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ እነዚህን ዝርያዎች ለመታደግ በወሳኝ ወቅት የደረሰ መሆኑንም ተገንዝበን እንጠቀምበት።

ይህ በሐምሌ ወር አሀዱ ተብሎ የተጀመረና በተለይ በዚሁ ወር በስፋት እየተካሄደ የሚገኝ መርሃ ግብር ከእነግለቱ እንዲቀጥልና ዓላማው እንዲሳካ በግልም፣ በማህበረሰብም እንዲሁም እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ርብርባችን ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ሰላም !!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተሳምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# ካንሰርን - በአሸናፊነት

መልካምሥራ አፈወርቅ

**የመርካቶዋ ጭምት**

የመሀል መርካቶ ልጅ ናት። ውክቢያ ግርግር ከበዛበት፣ የሰዎች አጀብ ከሚታይበት ደማቅ ሰፈር አድጋለች። መርካቶ የበርካቶች መገኛ፣ የብዙሀን ንግድ መናህሪያ ነው። የአካባቢው ጎዳና ጭርታን አያውቅም። ሁሉም በግፊያና ትግል ሲሮጥበት ይውልበታል።

ፍቅርተ አለማየሁ /ስሟ የተቀየረ/ ባህርይዋ እንደሰፈሯ አይደለም። ዝምተኛና ጭምት ነበረች። ለቤቱ የመጀመሪያ ናትና የወላጆቿ ዓይን ያርፍባታል። ከድሀ ቤተሰብ ብትገኝም አባቷ ስለእሷ ያላቸው ግምት ለየት ይላል። አቅማቸው ባይፈቀድም ከእኩዮቿ እንዳታንስ ከፍለው ያስተምሯታል። ጠዋት ማታ እጇን ይዘው ትምህርት ቤት አድርሰው ይመልሷታል።

የዛኔዋ ትንሽ ልጅ አድጋ ትምህርቷን እስክትጨርስ ባህርይዋ አልተለወጠም። ዛሬም ጭምትና ዓይናፋር ነች። ወላጆቿ ጌጥ ውበት ሳያምራቸው ስለእሷ ዋጋ ከፍለዋል። በተለይ አባቷ ቁምነገር ደርሳ እንዲያዩ ምኞታቸው ነበር። ፍቅርተ አላሳፈረቻቸውም። በትምህርቷ በርትታ፣ በጉብዝናዋ ስማቸውን አስጠራች። ዕድሜዋ ከፍ ማለት ሲይዝ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ተመረቀች። ይህኔ ወላጆቿ ደስታቸው ጨመረ። ልፋት ድካማቸው ፍሬ ይዟልና ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ።

ፍቅርተ ትምህርቷ እንዳበቃ በተማረችበት ዘርፍ ስራ አግኝታ ተቀጠረች። እንዲህ መሆኑ ራሷን እንድትጠብቅ፣ ቤተሰቧቿን እንድታስብ ዕድል ቸራት። ከእጇ የገባው ገንዘብ ቁምነገረኛነቷን አጎላው። የቢሮ ሰራተኛ ሆና ደሞዝተኛ ተባለች። ልጅነቷ አበቃ፣ በዝነጣ ቦርሳ አንግታ ስራ መመላለስ ያዘች።

**ሶስት ጉልቻ…**

አሁን ፍቅርተ ውበቷ አብቧል። ወጣትነቷ ከብዙዎች ዓይን እየጣላት ነው። ይህ ዕድሜ ለብዙ ወጣቶች ፈተና ይሆናል። ፍቅርተ ግን የልጅነት ባህርይዋ ከእሷ እንዳለ ነው። ዛሬም እንደትናቱ ጨዋና ጭምት ነች። ይህ ባህርይ ከሌሎች አስመረጣት። እሷን ያሉ ዓይኖች ከዓይኖቿ አርፈው ከውሀ አጣጪዋ ተገናኘች።

ፍቅርተ ትዳር መስርታ ጎጆ ስትወጣ ከቤተሰቦቿ ራቀች። ዛሬ አስራ አምስት ዓመታት ከቆጠረችበት ጥምረት ሁለት ልጆች አፍርታለች። ከባለቤቷ ጋር ተዋደው፣ ተከባብረው ይኖራሉ።

ፍቅርተ በምትሰራበት የመንግስት መስሪያቤት ከበርካቶች ጋር መግባባት ልማዷ ነው። ያየችውን ታከብራለች። የቀረበችውን ትወዳለች። ኑሮና ትዳሯን የምታከብረው ወይዘሮ በሃይማኖት የበረታች፣ በዕምነቷ የጸናች ናት። ጠዋት ማታ ስለሆነላት በጎነት ለአምላኳ ምስጋናን አታጓድልም።

**አንድ ማለዳ …**

ጊዜው የሐምሌ ወር መጀመሪያ ነው። ማለዳው በዳመና ተይዞ ሰማዩ መጥቆር ጀምሯል። ‹‹መጣሁ›› እያለ የሚያስፈራራው ዝናብ ቀኑን ለማክበድ እንዳሰበ ያስታውቃል። ከአልጋ ለመልቀቅ የሚፈትነው አየር ከቤት ለመውጣት አያስመኝም። ፍቅርተ ከሞቀ አልጋዋ የቀሰቀሳት እንደልማዷ ስራ መሄዷ ነበር። ጉዳይዋ ግን ይህ ብቻ አልሆነም። ደርሶ ከብብቷ ስር የሚሰማት ሕመም ሰላም ይነሳት ይዟል።

ቀኝ እጇን ወደ ግራ ብብቷ ሰዳ ቀስ ብላ ዳሰሰችው። አንዳች ነገር ጣቷ ላይ ጎርበጥ ሲል ተሰማት። ደነገጠች። በሃይማኖቷ የጸናች ናትና ቤት ካኖረችው የቤተክርስቲያን ዕምነት አንዱን አንስታ ተቀባባች።

ቢሮ ስትገባ ስለሁኔታው እያሰበች ነበር። እየቆየ የሚጠዘጥዛት ነገር አሁንም አልተዋትም። ስሜቱ እየጨመረ ሲሄድ ለቅርብ ባልንጀራዋ አዋየቻት። ባልንጀራዋ ልብሷን ገልጣ አየችና ድንገት የሚያጋጥም የዕጢ መቆጣት መሆኑን ነገረቻት። ፍቅርተ ለጊዜው እንደመረጋጋት ብላ ስራዋን ቀጠለች።

ፍቅርተ ዕለቱን ከጓደኛዋ ጋር ቤተክርስቲያን ለመሳለም ሄደች። በስፍራው ደርሳም ‹‹ይበጃል›› ያለችውን ሁሉ አደረገች። ዕለተ ዓርብ አልፎ ቅዳሜ ተከተለ። ዕሁድ ማለዳ ገላዋን ታጥባ ልብሷን መልበስ ስትጀምር አንዳች ነገር ጡቷን ሲከብዳት ተሰማት።

ለአፍታ በዓይምሮዋ ብልጭ ያለው ስሜት ፈጥኖ ከውስጧ ተመላለሰ። ግራ ጡቷ ላይ እየጠዘጠዘ ሰላም የነሳት ሕመም የጤና አለመሆኑን ጠረጠረች። ፍቅርተ ከልጅነቷ ጀምሮ ስትሰማው የኖረችው አንድ እውነት በየአጋጣሚው ሲረብሻት ኖሯል። የጡት ሕመም ይሉትን ጉዳይ አጥብቃ ትፈራዋለች። ከዚህ ችግር ጋር አብሮ የሚነሳው ‹‹ካንሰር›› የተባለ ሕመም ደግሞ አደገኛ መሆኑን አሳምራ ታውቃለች።

ፍቅርተ ስለራሷ ብዙ እያሰበች ጡቷን በዝግታ ዳሰሰች። ከላይ ከታች እያለች ጣቶቿን አመላለሰቻቸው። ከዚህ በፊት አይታው፣ ነክታው የማታውቅ ዕባጭ ነገር ከመዳፏ ሲገናኝ ተሰማት። በድንጋጤ ክው እንዳለች በዝምታ ተዋጠች።

**ማግስቱን…**

ዕለተ ሰንበት እንደምንም መሽቶ ነጋ። ሰኞ ቀን ስራዋ ስትደርስ የጀመራት ሕመም ተባብሶ ነበር። አሁን ፍቅርተ ሕመሟን ውጣ የምትደብቀው አልሆነም። እየሆነ ያለውን ሁሉ ለሌሎች ማጋራት አለባት። ሁኔታዋን ያስተዋሉ፡ ችግሯን የተጋሩ ለመፍትሄው ተጣደፉ። አሉ የተባሉ የሕክምና ዶክተሮችን ፈልገው አገናኝዋት።

ለአጠቃላይ ምርመራ ከሀኪም ዘንድ ተገኘች። አሁንም ውስጧ ስለጡት ሕመም የሰማችውን ሁሉ እያመላለሰ ያስጨንቃታል። ከዚህ ቀድሞ በጡቷ ላይ አንዳች ሕመም ተሰምቷት አያውቅም። በእርግጥ አንዳንዴ ራስ ምታት ያስጨንቃታል። ዶክተሩ ምርመራውን አጠናቆ ሊነግራት ሲዘጋጅ የፊቱን ገጽታ በጥንቃቄ ማንበብ ጀመረች።

እሱ ቃል ከማውጣቱ በፊት የሚለውን ገመተች። አሁንም ፊቱ መልካም ነገር አላሳያትም። አስተውላ አየችው። የፈራችው አልቀረም። ዶክተሩ በጡቷ ላይ የሚታየው ውጤት ችግር እንዳለበት የሚያመላክት መሆኑን ነገራት።

**የብርታት ጅማሬ …**

ፍቅርተ ውጤቱን እንደሰማች ራሷን ማጽናናት፣ ማበርታት ያዘች። እስከዛሬ የፈራችው፣ በሌሎች ሲደርስ ያየችው ሕመም ከእሷ ጋር እንዳይሆን እየሰጋች ነው። እንዲህ በተሰማት ጊዜ ዕምነቷን በፈጣሪ ትታ ውስጧን አበረታች። ወዲያው እንደብረት የጠነከረ ጽናት በልቧ ሲፈስ ተሰማት።

ምርመራውን ያካሄደው ዶክተር ያሬድ ከጎኗ ለመሆን የቻለውን አደረገ። ቅንነቱ አግዟት ለቀጣዩ ሂደት አዘጋጃት። የናሙና ምርመራውን ለማካሄድ መፍጠን ነበረባት። ሁኔታዎች ግን እንደታሰቡት አልሆኑም። ይህን ለማድረግ ረዘም ያለ ቀጠሮ ተሰጣት። ፍቅርተ በሁኔታው ብታዝንም ተስፋ አልቆረጠችም። ዶክተር ያሬድ ተመለሺ ባላት ቀን በስፍራው ተገኘች። ሀኪሙ ተጣድፎ የናሙናውን ውጤት እንድትሰጠው ጠየቀ። እንደከፋት ስለቀጠሮው መራዘም አስረዳችው። ውስጡ እያዘነ ለሌላ መፍትሄ ተጣደፈ። ጊዜ አልወሰደም። ዳግም የሕክምና ማዘዣውን ጽፎ ሰጣት።

ከሶስት ቀናት በኋላ ውጤቱን ይዛ ከፊቱ ቀረበች። ዳግም በዶክተሩ ገጽታ የሚያስደነግጥ ምልክት ያስተዋለችው ወዲያው ነበር። እሱ አሁን ይበልጥ እርግጠኛ የሆነበት የናሙና ውጤት ከእጁ ገብቷል። በአንደበቱ ‹‹አዎ ! የጡት ካንሰር ነው›› ለማለት ግን አልደፈረም።

ከሁኔታው ምላሽ ያገኘችው ፍቅርተ ለዶክተሩ እንዳይጨነቅ ነግራ የመጣውን ሁሉ በበጎነት በፀጋ እንደምትቀበል አሳወቀችው። ብርታት ጥንካሬዋን

**ከሶስት ቀናት በኋላ ውጤቱን ይዛ ከፊቱ ቀረበች። ዳግም በዶክተሩ ገጽታ የሚያስደነግጥ ምልክት ያስተዋለችው ወዲያው ነበር። እሱ አሁን ይበልጥ እርግጠኛ የሆነበት የናሙና ውጤት ከእጁ ገብቷል**

ያስተዋለው ሀኪም በሁኔታዋ ተደነቀ። ይህ እውነትም ልቡን ለበጎ አዘጋጅቶ ለሌላ መፍትሄ ከሌላ ሀኪም እንድሄድ መንገድ መራት።

**ከካንሰር ጋር ፍልሚያ …**

ፍቅርተ የቀጣዩን ሀኪም ስም በልቧ እንደያዘች ወደ ፀበል አመራች። ለእሷ ልክ እንደ ሕክምናው የዕምነት ፅናቷ ያስፈልጋታል። ሁለቱንም ጎን ለጎን ሳትለያይ መቀጠል እንዳለባት ወሰናለች።

ባለቤቷ በእሷ ላይ የሆነውን ባየ ጊዜ በእጅጉ አዘነ። እስካሁን ላይሆን ይችላል ብሎ የተጠራጠረበት ጉዳይ አሁን በሕክምናው ዕውን ሆኗል። ይህን ሲረዳ ከጎኗ ሊሆን ተዘጋጀ። በወቅቱ ፍቅርተ ሕክምናውን የጀመረችው ዶክተር እንግዳ ከሚባል ሀኪም ዘንድ ነበር። እሱም እንደቀድሞው ሀኪም በመልካም ትህትና ተቀብሎ አስተናገዳት።

ፍቅርተ በጡቷ ላይ የተከሰተው ካንሰር ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተነግሯታል። እሷ በወቅቱ ስለበሽታው ከመጨነቅ ለመፍትሄው ታደላ ነበር። ስለህመሙ የሚነገሩ፣ መረጃዎችን በመከታተል ግንዛቤ ለመውሰድ ትጥራለች። ሕጻናት ልጆቿ እንዳይጨነቁና ቤተሰብ እንዳያዝን ራሷን ቀድማ ታበረታለች።

**አካልን በስንብት …**

ውሎ አድሮ ወይዘሮዋ ከራሷና ከባሏ ተማከረች። ከሀኪሞች ተነጋግራም ከውሳኔ ደረሰች። ለቀናት ከሆስፒታል ተኝታ በቀዶ ሕክምና ግራ ጡቷ እንዲወገድ ሆነ። ለሴት ልጅ ጡት ማለት የማንነቷ ምልክት፣ የጾታዋ መለያ ነው። ከውበት አልፎ እናትነቷን የምትቸርበት በረከቷ ጭምር።

ፍቅርተ ይህ አካሏ ተቆርጦ ሲወገድ እንደሴት፣ ብሎም እንደ እናት ለአፍታ ‹‹ሸው›› ያለባት ስሜት አልጠፋም። እንዲያም ሆኖ ስሜቱ አብሯት አልቀጠለም። ሁሉን ትታ ፈጣሪን ለማመስገን አልዘገየችም። ለእሷ ሕመሟ ታውቆ ለሕክምና መድረሷ ብቻ ታላቅ ጸጋ ነው። ዛሬም ‹‹ሁሉም ለበጎ ነው›› ባይነቷ ማንነቷን አጽንቷል።

**እንዳያልፉት የለም የ€€ ኬሞ« ፈተና …**

በቀዶ ሕክምና አንድ ጡቷ ከተወገደ በኋላ ቀጣዩ ሂደት የጨረርና የኬሞ ቴራፒ ሕክምና ነበር። ፍቅርተ ይህ አይነቱ ሂደት በእጅጉ ፈትኗት አልፏል። ዛሬ ላይ ሆና ያን ጊዜ ስታወሳው የመድሀኒቱን ክብደት ገድሎ እንደማንሳት ትቆጥረዋለች።

ፍቅርተ ሕክምናውን ስትወስድ በእጅጉ ይደክማት ነበር። የምግብ ፍላጎት ማጣት ማስመለስና ሌሎች ችግሮችም ፈትነዋታል። በዚህ ወቅት ጥፍርና ጸጉር ይሏቸው አብረው እንዳልተፈጠሩ ይከዳሉ። ሰውነት ይዝላል፣ ማንነት ይሸሻል። መልካም ባህርይን ይለውጣል።

በዚህ ፈታኝ ወቅት ከጎኗ የነበሩ ቤተሰቦቿና የመስሪያቤት ባልደረቦቿ ሕመሟን እንድትረሳ ከጎኗ ቆመዋል። በጎዶሎዋ ተገኝተው ሙላት በረከት ሆነዋታል። ‹‹አይዞሽ፣ አለንሽ›› ሲሉ ዕንባዋን አብሰዋል። ይህ ወቅት ከማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ጋር የተገናኘችበት ነበር። ተቋሙ በወቅቱ አስፈላጊ የሕክምናና የመድሀኒት እገዛ አድርጎላታል። የባለሙያ ምክር ባስፈለጋት ጊዜም ከጎኗ ተገኝቷል። በተለይ በዘመነ ኮረና ሶሳይቲው ያለውን አካፍሎ ሕይወቷን መታደጉን ፈጽሞ አትረሳውም።

ፍቅርተ በስምንት ተከታታይ ዙር የወሰደችውን ‹‹ኬሞ ቴራ›› በብዙ ውጣውረድና ፈተና በድል አጠናቀቀች። ይህ ጥንካሬዋ ዛሬን በሕይወት እንድትቀጥል ነገን በተስፋ እንድታስብ ዕድል ቸሯታል። ለዚህ ማንነቷ ከጎኗ የነበሩ የስራ ባልደረቦቿ ከልቧ ውስጥ ልዩ ስፍራ አላቸው። ፍቅርተ ከእሷ ጋር ሕክምናውን የጀመሩ ብዙዎች ዛሬ በሕይወት እንደሌሉ ታውቃለች። ይህን እውነት መለስ ብላ ስታስበው ፈጣሪን ከማመስገን በላይ ቃል የላትም።

**ዛሬና ትናንት …**

አሁን ወይዘሮዋ በሕክምናው ያለፈችበት መንገድ ተቋጭቶ፣ በመልካም ጤንነት ቆማለች። ትናንት የተጎዳ አካሏ ወዝ ተመልሷል፤ የረገፈ ዞማ ጸጉሯ እንደ አዲስ በቅሎ ውበት አላብሷታል።

ስለጡቷ እንዲህ ነው ብላ ካላወጋች ለምን የሚያስብል ምልክት የለባትም። እንደ ቀድሞው ስራዋ ውላ ትገባለች። ዛሬም የባሏ ሚስት፣ የልጆቿ እናት ከመሆን ያገዳት የለም። ደስተኛና ሰላማዊ ሕይወት እየመራች ነው። ፍቅርተ ዘወትር አመስጋኝ ነች። ሁሌም ከአንደበቷ የፈጣሪ ምስጋና አይጠፋም።

ዛሬም በቋሚነት የምትወስደውን መድሀኒት ያለመሰልቸት ትጠቀማለች። አሁን ላይ የሚሰማት ሕመም የለም። አንዳንዴ ከሀኪሞች ስትገናኝ ግን ስላለችበት የጤና ሁኔታ አንድ ነገር እንዲሏት ትሻለች። እስከዛሬ ከተለመደው ምርመራ የዘለለ ስለህመሙ የሚያስረዳትን ሀኪም አላገኘችም። መጠየቅ መወያየት ብትፈልግም ይህ አይነቱ ዕድል ያለመኖሩ በጥያቄ ውስጥ እንድትኖር አድርጓታል።

**መልዕክት ስሴሎች…**

‹‹እኛ ታመን ካልጋ ካልወደቅን በቀር ሀኪም ዘንድ አንሄድም። ማንም ሰው ሕመም በተሰማው ጊዜ ፈጥኖ ሀኪም ቤት የመሄድ ልምድ ሊኖረው ይገባል። ቢቻል ጊዜ ወስኖ በየዓመቱ የጤና ምርመራ ማካሄድ ጥሩ ነው። ውድ ሴቶች ይህ ዓይነቱ ሕመም ቢገጥማችሁ ፈጥናችሁ ተስፋ አትቁረጡ። በሽታው ገዳይ ነው ብላችሁም ቀድማችሁ አትሙቱ። ሁሌም ለመፍትሄው በመትጋት በጥንካሬ መሻገር እንደሚቻል ከእኔ ሕይወት ተማሩ ››

ዛሬ ፍቅርተ የጡት ካንስርን አሸንፋ በድል መራመድ ከጀመረች ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል። አሁንም ውስጧ በታላቅ ተስፋ እንደተሞላ ነው። ነገ ለእሷ ብሩህ ሆኖ ይታያታል። ራሷን ትጠብቃለች፣ በፈገግታ ትውላለች። ፈጣሪዋን ደግማ ደጋግማ ታመሰግናለች ።

# መሠረተ ልማት

## የመስኖ ልማቱ የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ

በኃይሉ አበራ



የኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከፍተኛ መጠን ያለው የስንዴ ምርት እያገኘች ነው። ለአብነትም ዘንድሮ ከ100 /ከአንድ መቶ/ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ በበጋ መስኖ ልማት ብቻ ማግኘት ተችሏል። ይህ የተገኘውም በሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ልማቱን በማካሄድ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በኩልም እንዲሁ የመስኖ ልማቱ በስፋት እየተካሄደ ይገኛል።

ይህ ልማት ግን ሀገሪቱ ካላት የውሃና በመስኖ ሊለማ ከሚችል ሀብት አኳያ ሲታይ ብዙ የሚባል እንዳልሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ያመለክታሉ። በመስኖ መሠረተ ልማት የተከናወነው ተግባር ዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ ብቻ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ሀገሪቱ ያላትን ከፍተኛ ለመስኖ ልማት ሊውል የሚችል አቅም በመጠቀም የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዳ የመስኖ ፍኖተ ካርታ እያዘጋጀች ትገኛለች። ለቀጣይ 30 ዓመታት ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ይህ ፍኖተ ካርታ በየ10 ዓመቱ በተከፋፈሉ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እንደሚደረግ ፍኖተ ካርታውን አስመልክቶ በቅርቡ ከተካሄደ መድረክ መረዳት ተችሏል።

ፍኖተ ካርታው ሀገሪቱ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚዋን የበለጠ በማሳደግ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን እንደሚያስችላት ታምኖበታል። በመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር በኩል የሀገራዊ መስኖ ልማት ተግዳሮቶችን በመለየት እና ባልተቀናጀ መልኩ ይደረጉ የነበሩ የመስኖ ልማት ጥረቶችን የሚያቀናጁ ፣ የዘርፉን አቅም የሚያሳድጉ ፕሮግራሞች በእቅድ ተይዘዋል። ፕሮግራሞቹ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው እና በተለይ የግሉን አቅም የሚያሳድጉ ሥራዎችም እየተዘጋጁ ናቸው።

ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ እና ማኔጅመንት ባለሙያዎች ማህበር ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ጋር በመሆን በዋነኛነት አሁን ያለውን የመስኖ ልማት ካለበት ደረጃ ወደ ተሻለ የመስኖ ትራንስፎርሜሽን ለማሳደግ ያለመ ኮንፍረንስ ተካሂዷል። በመድረኩ ጥናታዊ ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን፤ ከአማካሪ ድርጅቶች፣ ኮንትራክተሮች፣ የምርምር ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች የመስኖ ዘርፉን መሠረተ ልማት ለማሳደግ የሚያግዙ ገንቢ ሃሳቦች እና ጥናቶች ቀርበዋል።

በመስኖና እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ምርምር ዴስክ ኃላፊ አቶ ያሬድ ሙላቱ ፣ በሀገሪቱ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ብዛትና የተመጣጠነ ምግብ /ዳያትሪ/ ፍላጎት ለማሟላት በፈረንጆቹ 2050 በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2022 የተመረተውን እህል መጠን በአራት እጥፍ ማሳደግን የግድ እንደሚል ይገልጻሉ። ለእዚህም በዝናብ ላይ ተመስርቶ የሚመረተውን የእህል መጠን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ መሥራቱ እንዳለ ሆኖ፣ የመስኖ መሠረተ ልማትን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ያስፈልጋል።

ሚኒስቴሩ የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ፕሮጀክቶችን እየነደፈ ሲሠራ መቆየቱን አስታውቀው፣ የመስኖ ፍኖተ ካርታ እያዘጋጀ መሆኑንም አመልክተዋል። ሀገሪቱ በመስኖ መልማት የሚችል አስር ሚሊዮን ሄክታር ያህል መሬት እንዳላት ጠቅሰው፣ እስካሁን የለማው ግን እጅግ ዝቅተኛው መሆኑን ጠቁመዋል።

ለእዚህ ምክንያት ከሆኑት መካከል ተቀናጅቶ አለመሥራት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ የመስኖ ልማት ዲዛይንና ጥናት፣ ኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ ምርምሮችና የመሳሰሉት ተቀናጅተው በእቅድ ካልተመሩ በስተቀር የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አይቻልም ሲሉ አቶ ያሬድ አስታውቀዋል። በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን ኢትዮጵያ በመስኖ ልማቷ የዛሬ አምስት ዓመት የት ትድረስ? የዛሬ 10 ዓመት የት ትድረስ የሚለውን በመያዝ መጓዝ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱ የጎላ ሚና እንደሚኖረውም አመልክተዋል።

ከመስኖ ልማት አኳያ ያለንን የተፈጥሮ ሀብት በመረዳት ረገድ ክፍተቶች አሉብን ያሉት አቶ ያሬድ፣ ሀገሪቱ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ሀብት ቢኖራትም በመስኖ መሠረተ ልማቱ ላይ ሰፊ ተግዳሮቶች እንደነበሩ ጠቅሰዋል። አብዛኛዎቹ ተግዳሮቶችም በሀገሪቱ ከዝናብ ከሚገኘው ውሃ 70 በመቶው በሶስት ወራት ውስጥ ፈሶ እንደሚያልቅ ጠቁመዋል። ይህን ተከትሎም ለዘጠኝ ወራት ያህል የውሃ እጥረት ይከሰታል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሀገሪቱ የተፈጥሮ አቀማመጥ ከፍያለ ስለሆነም ከምታገኘው የዝናብ ውሃ 96 በመቶ ያህሉ ወደ ጎረቤት ሀገራት ይሄዳል። ይህም ትልቁ ተግዳሮት ነው። በመሆኑም በመስኖ ዘርፉ የጎረቤት ሀገራትን ተጠቃሚነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ውሃውን መጠቀም ያስፈልጋል።

በሀገሪቱ በመስኖ ዘርፉ ባሉ ባለድርሻ አካላት በኩልም የግንዛቤ ክፍተቶች መኖራቸውን አቶ ያሬድ ያመላከታሉ። የግብርና ዘርፉ አሁን በያዝነው መንገድ የት ያደርሰናል የሚለው ሲታሰብ እጥረት እንዳለም ጠቅሰው፣ መስኖ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ነው በሚለው ላይ ትልቅ የግንዛቤ እጥረት አለ ሲሉ ይጠቁማሉ። የተቋማት እና ባለድርሻ አካላት የአቅም እጥረት ሌላው ተግዳሮት መሆኑን ገልጸው፣ ከመንግሥት ተቋማት ጀምሮ መስኖ ላይ እየሠሩ የሚገኙ የልማት ድርጅቶች የአቅም እጥረት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የግል ዘርፉ ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት ፕሮግራም ነድፎ፣ ፍኖተ ካርታ ቀርጾ መሥራት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል የሙያ ብቃት እጥረት አለ። ይሄንንም ችግር ለመፍታት ከልማት ድርጅቶች /የልማት ተቋማት/ ጋር በመናበብ ባለሙያዎችን ብቁ በማድረግ በተለይ ተግባር ተኮር እውቀት እና ክህሎት እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ክፍተቶች ይታያሉ። በአሁኑ ወቅትም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ባለድርሻ አካላትን የማቀናጀት ተግባር እየተከናወነ ይገኛል።

በመስኖ ልማት አንዱ ትልቁ ተግዳሮት ያለውን የመስኖ ሀብት በቁጥር አለማወቅ ነው ያሉት ኃላፊው፣ በዘርፉ ላይ በመንግሥት ተቋምም ሆነ በተለያዩ አካላት የተደረጉ ጥናቶች የተለያዩ ሆነው መቆየታቸውን ተናግረዋል። ያልተቀናጁ መረጃዎችን በመያዝ በተደረገው ግምታዊ ዳታ መሠረት የመስኖ ልማቱ በኢትዮጵያ በዚህ ዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ያህል መድረሱን አስታውቀዋል።

የሀገሪቱ የመስኖ አቅምን አስመልክቶ ሶስት ሚሊዮን እና አራት ሚሊዮን የሚሉ ብዙ ግምቶች እንደሚሰጡ አስታውሰው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባካሄዳቸው ጥናቶች ግን ይህ አቅም ወደ 10 ሚሊዮን ሄክታር አካባቢ እንደሆነ ጠቁመዋል። በመስኖ የለማው ግን የዚህ ከሩብ በታች መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ያሬድ ገለጻ፤ ሌላው ትልቁ ተግዳሮት ሥራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በሙሉ አቅም እየሠሩ አለመሆናቸው ነው። አብዛኛዎቹ ከመቶ በታች ናቸው። የውሃ እና የመስኖ ዘርፍ ሌላው አንዱ ትልቁ ክፍተት ቀደም ሲል በየራሳቸው ይካሄዱ የነበሩ ኮንፍረንሶች ያስከትሉት የነበረው የሀብት ብክነት ነው። በመሆኑም የተናበበ ውጤት በማስመዝገብ በኩል ክፍተት አለ።

የአሁኑን ወርክሾፕ ልዩ የሚያደርገውም መሬት ላይ ያለውን ሥራ እየሠሩ ያሉ የልማት ድርጅቶችን፣ አማካሪዎች፣ የግል ዘርፎች፣ ኮንትራክተሮች እንዲሁም የህንፃ እና የመንገድ ግንባታ ሲቪል ሥራ ላይ ያሉ እና የመስኖ ዘርፉንም ማገዝ የሚችሉ ባለድርሻ አካላትን ያሰባሰበ በመሆኑ ነው። የሚቀርቡት ጥናቶችም ተግባር ተኮር የሆኑና አማካሪ ድርጅቶችም ከራሳቸው እይታ በራሳቸው ጫማ ውስጥ ሆነው ለማየት ያስችላቸዋል። የመስኖ መሠረተ ልማት ፍኖተ ካርታ ዝግጅቱም በዋነኛነት እየተሠራ ያለው በሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ነው።

አሁን የሚኒስትሩ አማካሪዎች ፕሮጀክቱን እየመሩ እና ባለሙያዎችን እያስተባበሩ በእቅድ ደረጃ እየተሰራ ይገኛል ያሉት አቶ ያሬድ፣ ባለሙያዎችም ተሳትፎ ያደርጋሉ ብለዋል። በአቅም ግንባታ እና ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ትኩረት ተሠጥቶታል ነው የሚሉት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ቀደም ሲል ትኩረት ላልተሰጠው የግሉ ዘርፍም አቅም ይፈጥር ዘንድ አንድ ፕሮግራም ከዚህ ፍኖተ ካርታ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም በዲዛይን፣ በኮንስትራክሽን፣ መስኖ ላይ ኢንቨስት በማድረግ፣ ፋብሪካዎችን በማቋቋም ጭምር የሚገለጽ ይሆናል። ይህም በፍኖተ ካርታው ይመጣሉ ተብለው ከሚጠበቁትና እንደ ንድፈ ሃሳብ ከተያዙት አምስት ፕሮግራሞች መካከል አንዱ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ 125 ቢሊዮን ኩዩቢክ ሜትር አካባቢ በገፀ ምድሯ ላይ የሚፈስ የውሃ ሀብት አላት፤ አንድ ትሪሊዮን ኩዩቢክ ሜትር ውሃም ከዝናብ ታገኛለች። ከዚያ ውስጥ በወንዞቿ 124 ቢሊዮን ሜትር ኩዩቢክ አካባቢ ውሃ ይፈሳል። ከዚህ ውስጥም 96 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ወይም 80 በመቶው ውሃ ወደ ውጭ ሀገሮች ይሄዳል።

ከዝናብ ከሚገኘው ውሃ አንፃር በመስኖ የምንጠቀመው ከ10 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በታች ነው ያሉት አቶ ያሬድ፣ ይህም ከዝናብ ውሃ ከአንድ በመቶ በታች ነው ይላሉ። የዓለም የምግብና ግብርና ድርጅት /ፋኦ/ 2016 እ. አ.አ በመስኖ ላይ ያካሄደውን ጥናት ዋቢ አድርገው ሲያብራሩም፣ በሀገሪቱ ወንዞች ከሚፈሰው 124 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ፣ ዘጠኝ ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትሩ ብቻ ጥቅም ላይ እንደሚውል አመልክተዋል። ይህም እስካሁንም 10 በመቶ አይሞላም። ከዝናብ የሚገኘውን ውሃ በመያዝ ለመስኖ ልማት ማዋል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር ልዩ አማካሪ ዶክተር ኢንጂነር ውብሸት ዝቅአለ በኮንስትራክሽን ዘርፉ በተለያየ ዘርፎች ይሠራሉ። የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ማህበር የአማካሪ ቦርድ ሰብሳቢም ናቸው። ማህበሩ በዋናነት ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንደሚሠራ ጠቅሰው፣ መድረኩ የመስኖ ልማቱ በፍኖተ ካርታ ታግዞ እንዲመራ ለማድረግ እንደሚረዳ አስታውቀዋል።

ፍኖተ ካርታው ለቀጣይ 30 ዓመታት የመስኖ መሠረተ ልማቱን ማምጣት የሚያስችል መስመር የሚቀረፅበት ነው ሲሉም ጠቁመዋል። በኢትዮጵያ የመስኖ ልማት ላይ እምርታዊ ለውጥ ለማምጣት የተቀረጸ ስትራቴጂክ ፍሬምወርክ መሆኑን ጠቅሰው፣ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉትም አመልክተዋል። የሀገሪቱ የመስኖ ልማት ዘርፍ ያለበትን አጠቃላይ ሁኔታ፣ ዓለም አቀፍ ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎችን፣ በቀጣዮቹ 30 ዓመታት በዘርፉ ሊከናወንና ሊደረስበት የታሰበው በዝርዝር የተመላከተበት መሆኑን አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በሀገሪቱ ለሶስት ወራት የዝናብ ውሃ ይኖራል፤ ለስድስት ወራት ውሃ ያለባቸው፣ የሌለባቸው ቦታዎችም አሉ። ውሃ በሌለባቸው አካባቢዎች መስኖን እና ውሃ የሚቆጥቡ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርታማነትን መጨመር በሚቻልበት መንገድ ላይ በመሥራት ምርታማነቱን በአራት እጥፍ ማሳደግ ይገባል። ፍኖተ ካርታውም በዓመት አራት ጊዜ በማምረት ምርታማነትን ማሳደግ የሚቻልበት አቅም እንዳለ ለማሳየት ያግዛል። የአፈር ባህሪ ሲታይም ውሃ ቶሎ የሚለቅ፣ ውሃ የሚይዝም አለ። ከሚለሙት አትክልቶች አኳያ ሲታይም እንዲሁ ውሃ በጣም የሚፈልጉና የማይፈልጉ አሉ።

የመስኖ ሥራዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ስናይ ውሃ በጣም በሚፈለግባቸው ቦታዎች ላይ የምንጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች አሉ። ውሃ በጣም የሚያጥርባቸው ቦታዎች ላይ ደግሞ ለውሃ ቁጠባ የሚረዱ የውሃ መስኖ ቴክኖሎጂዎች አሉ ሲሉም አመልክተው፣ እነዚህን አራት ነገሮች በማቀናጀት ምርታማነታችንን ከፍ በማድረግ በምግብ፣ ራስን ለመቻል የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ገቢ ለመጨመር፣ የግብርና ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንደሚቻል አስታውቀዋል።

ኢንጂነር ውብሸት ዘርፉ ከባድ የሚባሉ ተግዳሮቶች እንዳሉበትም ጠቁመዋል። ተግዳሮቶቹንም በቅድመ ፕሮጀክት በዲዛይን፣ በማልማት /ዴቨሎፕመንት/ በትግበራ /በኤክስኪዩሽን/ እና በአቅርቦት ማኔጅመንት በኩል የሚታዩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የኤስያ፣ አፍሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅ፣ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ ተሞክሮዎችን በመጥቀስም ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በሰነዱ ለማሳየት መሞከሩን ተናግረዋል።

ከዚህም በአንደኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠችው ባንግላዴሽ 82 በመቶ ውሃዋን ለመስኖ ተጠቅማለች። ፓኪስታን ሁለተኛ ነች፤ 52 ነጥብ 56 በመቶ ተጠቅማለች። ከዚያ በኋላ ያሉት 40፣ 30 ውስጥ ያሉ ናቸው። የእኛዋ ሀገር ዜሮ ነጥብ አምስት ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ ይህም ያስቆጫል።

በመስኖ ልማት በፍጥነት በመጠቀም ከችግር ለመውጣት እና ሕዝቡ የሚጠቀምበትን የመስኖ ዘርፍ ከሕዝብ፣ ከባህል እና ከማህበረሰቡ ጋር አቀናጅቶ መሥራት ይገባል ሲሉም መክረዋል። ሳይንሱም አንዳንድ ጊዜ አርሶ አደሩ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የኖረውን አብሮ አገናዝቦ በተጨባጭ ሥራ ተሰናስሎ እንዲሄድ ካልተደረገ ውጤታማ ላይሆን ይችላል ሲሉም አስገንዝበዋል።

በመቀጠልም ልማቱ ወደ ንግድ በሚሄድበት ጊዜም ወደ ሕዝብ፣ ሕዝባዊ የግል ዘርፍ ፣ እንዲሁም ወደ ግሉ ዘርፍ በደረጃ መግባት አለበት ሲሉ ጠቁመው፣ ይሄንን በየደረጃው በማሳደግም በመጀመሪያው 10 ዓመት፣ በሁለተኛው 10 ዓመት፣ በ3ኛው 10 ዓመት ምን መሥራት እንደሚገባ በዝርዝር በመቅረፅ አምስት ፕሮግራሞች እና 26 ፕሮጀክቶች መቅረባቸውን አመልክተዋል።

ይሄንንም የመስኖና እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ተመልክቶ እና ቅድሚያ የሚሰጠውን ለይቶ እስከ ታህሳስ ወር 2017 ዓ.ም ድረስ እንደሚያጠቃልለውና ይፋ እንደሚያደርግ ግምታቸውን አስቀምጠዋል።

# ስፖርት



## መቻል ከዩጋንዳው ክለብ ኪታራ ጋር የወዳጅነት ጨዋታ ያደርጋል

ዓስማየሁ ግዛው

መቻል ስፖርት ክለብ 80ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ሲያከብር የክለቡን የቀደመ ገናናነት በሚያስታውሱ እና ከአፍሪካ ምርጥ ክለቦች አንዱ ለመሆን የሚያስችሉትን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። በበርካታ ኩነቶች የምሥረታ በዓሉን እያከበረ የሚገኘው መቻል፣ በነገው እለትም አንጋፋና የቀድሞ የዓለም እግር ኳስ ኮከቦች የሚታደሙበትን የወዳጅነት ጨዋታን ከዩጋንዳው ክለብ ኪታራ ጋር ያካሂዳል።

መቻል ከሰኔ 1-2016 ዓ.ም ጀምሮ በክለቡ ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ሰይፉ ጌታሁን እና የመከላከያ ሚኒስቴር የሥነ-ልቦና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጀነራል እንዳልካቸው ወልደኪዳን በሚመራው ኮሚቴ በተለያዩ የምሥረታ በዓሉን እንዲከበር እየሠራ ነው። ከነዚህም መካከል ሕዝባዊ የፓናል ውይይት፣ የሩጫ ውድድር እና የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ክለቡን ለማጠናከር እና ውጤታማ ለማድረግ ታስበው ተካሂደዋል። ሌላው የክብረ በዓሉ አካል የሆነውን እና ትላልቅ የእግር ኳስ ኮከቦች የሚታደሙበትን የወዳጅነት ጨዋታውን የወንዶች እግር ኳስ ቡድኑ በነገው እለት 10፡00 ሰዓት ላይ በአዲስ አበባ ስቴድየም እንደሚያደርግ ይፋ ተደርጓል።

በተጠናቀቀው የ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ አስደናቂ አቋም አሳይቶ በሁለት ነጥብ ልዩነት ዋንጫውን ማንሳት ያልቻለው መቻል፣ የ80ኛ ዓመት ክብረ በዓሉን ለማድመቅ ከዩጋንዳው ክለብ ኪታራ ጋር የወዳጅነት ጨዋታውን



ኢንስትራክተር አብረሃም መብራቱ የመቻል እግር ኳስ ክለብ ቴክኒካል ዳይሬክተር፣

እንደሚያደርግ አሳውቋል። የአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ አሸናፊው ክለብ ኪታራ የወዳጅነት ጨዋታውን ለማድረግ ከትናንት በስቲያ አዲስ አበባ መድረሱም ታውቋል።

ሁለቱ ክለቦቹ ከሚያከናውኑት የወዳጅነት ጨዋታ በፊት አርቲስቶች እና የቀድሞ የመቻል ተጫዋቾች የወዳጅነት ጨዋታ የሚያደርጉ ሲሆን ይህም ለቀድሞ ተጫዋቾች ክብር ተብሎ መዘጋጀቱ ተጠቁሟል። በባለሀብቶችና በመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መካከል እንዲሁ የወዳጅነት ጨዋታ ሲደረግ መንግሥት ለስፖርት የሰጠውን ትኩረት ከግንዛቤ በማስገባት እና የሥራ ኃላፊዎቹ ለስፖርቱ ትኩረት እንዲሰጡና ባለሀብቶችም ያላቸውን አበርክቶ እንዲያጎለብቱ በማሰብ መዘጋጀቱ ተገልጿል።

በጨዋታው ታዋቂና ትልልቅ ስፖርተኞችና የመንግሥት ከፍተኛ በለሥልጣናት የሚታደሙ ሲሆን የስፖርት ቤተሰቡ ጨዋታውን ስታድየም ገብቶ በነጻ መከታተል እንደሚችል አዘጋጅ ኮሚቴው ገልጿል። በዓሉን ለማድመቅና የሀገር ገጽታን ለመገንባት እንዲረዳ የቀድሞ የዓለም የእግር ኳስ ክዋክብት የሆኑት ሁለት ተጫዋቾች ጨዋታውን እንደሚታደሙ ተጠቅሷል። ፖርቹጋላዊው የቀድሞ የማንቸስተር ዩናይትድ ኮከብ ሉዊስ ካርሎስ አልሜይዳ (ናኒ) በጨዋታው ላይ እንደሚገኙ ቀደም ብሎ መገለፁ ይታወቃል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫ ዝግጅት አምባሳደር ተደርጎ የተሰየመው ናይጀርያዊው የቀድሞ ንዋንኮ ካኑም እንደሚታደም ይጠበቃል።

የመቻል እግር ክለብ የቴክኒክ ዳይሬክተር ኢንስትራክተር አብረሃም መብራቱ ክለቡ በዓሉን ሲያከብር በ80 ዓመታቱ በስፖርት ሲያገለግሉ የነበሩ በሕይወት ያሉትንም የሌሉትንም ስፖርተኞች እያወደሰና እያመሰገነ እንዲሁም ለቀጣይ ጠንካራ መሠረት በመጣል መሆኑን ገልጸዋል።

ዋናው የመቻል የሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች የእግር ኳስ ቡድኖች በተመሳሳይ በፕሪሚየር ሊግ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቁ ሲሆን፣ ከ17 ዓመት በታችም አራት ውስጥ ገብቶ ቀጣይ ጨዋታን እየተጠባበቀ ነው። በዚህም ዘንድሮ በእግር ኳሱ የታቀዱ እቅዶች የተሳኩ መሆኑን ቴክኒካል ዳይሬክተሩ አመልክተዋል። ይህም የሆነው የቦርድ አመራሩ በሰጠው አቅጣጫ፣ በአሠልጣኝ ክፍሉ ላይ በተሠራው ጠንካራ መዋቅር እና የተጫዋቾችና አሠልጣኞች የጋራ ህብረት እንደሆነ ገልጸዋል። ክለቡ ለቀጣዮቹ ዓመታት ዘመናዊ እና በታዳጊዎች ላይ ሊከተል ለፈለገው አቅጣጫ ስፖርተኞቹ እና ክለቡ ካላቸው ልምድ እንዲያካፍሉ ታስቦ ነው። ከክለቡ የቦርድ አመራር፣ ከመከላከያ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች እና ስፖርቱ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር የውይይት መድረክም ይካሄዳል። በቀጣይም ከሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ካሉ የሚሊተሪ ክለቦች ጋር የወዳጅነት ጨዋታዎችን ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል።

መቻል ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር እንዲሁ የካፍ ዲ ላይሰንስ የአሠልጣኝነት ሥልጠናን የሚሰጥ ሲሆን በክለብ ደረጃ የመጀመርያው እንደሚሆን ተነግሯል። በዚህም ከዋናው የሁለቱ ቡድን ተጫዋቾች እና የሠራዊቱ አባላት ሆነው የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ሥልጠናን የወሰዱ ይሳተፋሉ። ሥልጠናውን የሚወሰዱት 60 ከ መቶ ከክለቡና 40 ከመቶ ከተለያዩ ክለቦች ተጋብዘው ይሆናል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ያለባትን የግብ ጠባቂ ችግር ለመቅረፍ ባለሙያዎችን ከደቡብ አፍሪካና ዴንማርክ ጋብዞ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዷል።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

## ከኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

## የግብርናው ዘርፍ ንቅናቄዎች ለምርታማነት

ተዋበ ጫኔ

የግብርናው ዘርፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማሳደግ ድርብርብ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ለቀጣዮቹ ዓመታት የሚኖረውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሀገሪቱን ሕዝብ የመመገብና በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ የማስገኘት ሚና ከዘርፉ ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪ የግብርና መዋቅራዊ ሽግግርን እውን የማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ምግብ፣ ግብዓትና የሰው ኃይል የማቅረብ ብሎም በስፋት የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራዎች ከግብርናው ዘርፍ ይጠበቃሉ።

እነዚህን ጥልቅ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ሰፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን በተለይም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ሽግግርን እውን ለማድረግና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመከላከል የሚያስችሉ ሀገራዊ ንቅናቄዎች ተቀርፀው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ። ንቅናቄዎቹ ገበያ ተኮር የሰብል፣ የእንስሳትና ዓሣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ማሻሻል ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው።

ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉት ንቅናቄዎች የመስኖ ስንዴ፣ አረንጓዴ ዐሻራ እና የሌማት ትሩፋት ሲሆኑ በሰብል ልማት፣ በተፈጥሮ ሃብት ልማትና በእንስሳት ዘርፉ ምርታማነት ላይ ከፍተኛ እምርታን አሳይተዋል።

ከውጪ የሚገባውን የስንዴ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና የተቀመጠውን ሀገራዊ ግብ ለማሳካትና ፍላጎትን ለማሟላት በመኸር የስንዴ ልማት ከሚለማው ጎን ለጎን ለመስኖ ስንዴ ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት እየተሠራ ሲሆን ለተከታታይ ዓመታት አበረታች የምርት ጭማሪ ተመዝግቧል። ይህም ለስንዴ ልማት ምርትና ምርታማነት እድገት ከፍተኛ ድርሻን እያበረከተ ይገኛል።

የመስኖ ስንዴ ልማት በ2011 ዓ.ም በ3ሺህ 502 ሄክታር መሬት የተጀመረ ሲሆን ልምዶችን በመቅሰም፣ አሠራሮችን በማዘመንና በማስፋት በዘንድሮው ዓመት 2 ነጥብ 97 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ የተሸፈነ ሲሆን በዚህም 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማሳካት የምርት አሰባሰብ ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሃብት ያላትን ፀጋና እምቅ አቅም በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ዘርፉን የማልማትና የማዘመን ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በእንስሳት ዘርፉ ያለውን እምቅ አቅም ወደ ምርታማነት ለመቀየር በዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የእንስሳትና ዓሣ ምርታማነትን ለማሳደግ አሠራርን ማዘመንና ልዩ ትኩረት መስጠት ላይ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው። ለዚህ ማሳያ ደግሞ የዘርፉን ምርታማነት በማሳደግ ድርሻውን እየተወጣ የሚገኘው የሌማት ትሩፋት ኢኒሼቲቭ አንዱ ነው። በዚህ ፕሮግራም እንቁላል፣ ሥጋ፣ ማር፣ ወተትና ዓሣ ልዩ ትኩረትን አግኝተው እየተሠራባቸው ይገኛሉ። የሌማት ትሩፋት የእንስሳትና ዓሣ ሃብት ምርትና ምርታማነት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣትን ዓላማ አድርጎ በ2015 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጨባጭ ለውጥን እያመጣ ይገኛል።

ከንቅናቄው መጀመር ማግስት ክልሎች ያላቸውን ተፈጥሯዊ ፀጋና እምቅ የእንስሳት ሃብት አቅም በመጠቀም በወተት፣ በማር፣ በሥጋ፣ በእንቁላል እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ላይ በልዩ ትኩረት እየሠሩ ሲሆን በምርታማነት ላይ ተጨባጭ ለውጦችን እያስመዘገቡም ናቸው።

የሌማት ትሩፋት ኢኒሼቲቭ ተግባራዊ መደረግ የእንስሳት ዘርፉ እድገት እንዲያመጣ ከማድርግ ባለፈ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን አብሮ በማካተት እየሠራ ሲሆን በምግብ



ዋስትና፣ ሥርዓተ ምግብ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና የዘርፉን የወጭ ንግድ ግኝት ከማሳካት አንጻር ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን አሳይቷል። የሌማት ትሩፋት ልማቱ ሥራ ዕድል የመፍጠር፣ የገቢ ምርትን የመተካት፣ የወጪ ንግድን የማሳደግና የሥነ ምግብ ዋስትናን ለማሳካት መንገዱን ጀምሯል።

የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግና ዘላቂነት ያለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ትልቅ ድርሻ አለው። ኢኒሼቲቩ የአካባቢን ተፈጥሯዊ ገፅታ ለመጠበቅና ለመንከባከብ በተለይም የደን መመናመንና የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ብሎም የሀገሪቱን የደንና የአረንጓዴ ሽፋን በማሳደግ ንፁሕ አየርና ውሃ እንዲኖር ያለመ ሲሆን በ2011 ዓ.ም ጅማሮውን ያደረገው ንቅናቄው የመጀመሪያውን ምዕራፍ በማጠናቀቅ የሁለተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ዓመት ዝግጅትና ትግበራ ላይ ይገኛል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ በነበሩ አራት ዓመታት በአጠቃላይ 25 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። ይህ ውጤታማ አፈጻጸም በሁለተኛው ምዕራፍ የመጀመሪያ ዓመትም የቀጠለ ሲሆን በዚሁ መሠረት በ2015/16 የተከላ ዘመን 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች መትከል ተችሏል። በዚህም በንቅናቄው ዘመን የተተከሉ ችግኞችን ቁጥር 32 ነጥብ 78 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል። በ2016/17 ዓ.ም የተከላ ዘመን የተያዘውን 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኝ ለማሳካት ይፋዊ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር በፌዴራልና በክልሎች ተጀምሯል።

በአጠቃላይ ግብርናው በተግባር ሰፊ የሥራ ዕድል እየፈጠረና ኑሮን እየለወጠ ሲሆን የ10 ዓመቱን የግብርና ልማት እቅድ ማሳካት እንዲቻል በቀጣይ ንቅናቄውን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም እየተሠራ ይገኛል።